አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# “ልጅነት” በ*ማሕሌትና አለንጋና ምስር*፣ ሥነ ልቡናዊ ንባብ

በ

ቴዎድሮስ አለበል

ሰኔ፣2006 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# "ልጅነት" በማሕሌትና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ
ጥናት


በ

ቴዎድሮስ አለበል



2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# "ልጅነት" በማሕሌትና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ

በ

ቴዎድሮስ አለበል

2006 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| አማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ________________________ | ____________ |

| ፈታኝ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ________________________ | ____________ |
| ________________________ | ____________ |

# ማረጋገጫ

"'ልጅነት' በማሕሌትና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ይህ ጥናት የራሴና አዲስ (oroginal) እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው አካዳሚያዊ ዲሲፕሊን መሰረት የተበጀ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

የጥናቱ አቅራቢ ሥም፡ ቴዎድሮስ አለበል መኮንን

ፊርማ፡ ____________________

የጥናቱ ማሟያ መርሐ ግብር፡ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር

ቦታ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ

የቀረበበት ጊዜ፡ ሰኔ፣ 2006 ዓ.ም

# ምስጋና

ይህን ጥናት እንዳደርግ የፈቀደልኝና በተለያዩ ጉዳዮች የደገፈኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬ ይድረሰው። ሰርክ ከእነዚያ ውብ ግሪካውያን "ሳይረኖች" ዝማሬ የምታድነኝ እግዚአብሔር ሆይ! ምንም ባልነበረበት የሲና ምድረ በዳ ስንዝ፣ በዝግባዎቻቸውና ዘንባባዎቻቸው ልብን በሚያሸፍቱ የሊባኖስ ተራራዎችም ሳልፍ አንተ ከእኔ ጋር ነበርክና መውደዴም ምስጋናዬም ካንተ ነው።

መምህሬና አማካሪዬ ቴዎድሮስ ገብሬ (ረ/ፕ)! እነሆ አንደበቴ ለምስጋና ይከፈት ዘንድ እንደምን ይሆንልኛል? በተጣበበ ሰዓትህ እየመጣሁ ሳስቸግርህ በ"ክፋት" ፊትህን አላከበድክብኝምና ቅንነትህና አዋቂነትህ አሁንም ያብቡ።

ከእናንተ በመሆኔ ሁሌም ደስ የሚለኝ ቤተሰቦቼ (*ጋሼዬና ማማይ*) እናንተን ማመስገን በእንደምንኛ "ዝማሬ" ይገባ ይሆን?! ግን እኮ የእኔ ናችሁ! በቃ! እኔ ራሴን እንዴት አመሰግናለሁ?! የእናንተን ዝማሬስ በ"ባዕዳን" ፊቶች እንዴት እዘምራለሁ? የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሰላማችሁን እንደ ኢየሩሳሌም ቅጽሮች ያጽና። እህቶቼና ወንድሞቼ አሁንስ ደስ አላችሁ?!

## ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምስጋና------------------------------------------------------------------------------------ I

አሕጽሮተ ጥናት------------------------------------------------------------------------ IV

**ምዕራፍ አንድ**

መግቢያ--------------------------------------------------------------------------------- 1

1.1.የጥናቱ ዳራ------------------------------------------------------------------ 2
1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት------------------------------------------------------ 3
1.3.የጥናቱ ዓላማ-------------------------------------------------------------- 3
1.3.1. የጥናቱ አቢይ ዓላማ------------------------------------------------------ 4
1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች------------------------------------------------ 5
1.4.ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች--------------------------------------------- 5
1.4.1. ጥናቱ የሚመልሰው አቢይ ጥያቄ------------------------------------------ 5
1.4.2. ጥናቱ የሚመልሳቸው ዝርዝር ጥያቄዎች---------------------------------- 5
1.5.የጥናቱ ዘዴ---------------------------------------------------------------- 5
1.6.የጥናቱ ጠቀሜታ--------------------------------------------------------- 8
1.7.የጥናቱ ወሰን-------------------------------------------------------------- 8

**ምዕራፍ ሁለት**

ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት-----------------------------------------9

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ---------------------------------------------------------------9
2.1.1. “ልጅነት”--------------------------------------------------------------------9
2.1.1.1. ማኅበረ-ልቡናዊ ዕድገት፤ ኤሪክሰን---------------------------------11
2.1.1.2. ፍሮይዳዊ የሰብዕና መዋቅሮች-------------------------------------15
2.1.1.3. ቋንቋ፣ ልጅነት፣ ላካን---------------------------------------------17
2.1.2. ሥነ ጽሑፍና ስነ ልቡና------------------------------------------------19
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት-------------------------------------------------23

**ምዕራፍ ሦስት**

“ልጅነት” በማሕሌት እና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ-------------------31

3.1. “ልጅነት” በማሕሌት፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ---------------------------------------31

3.1.1. “ማሞ”፤ ማኅበረ ልቡናዊ ማንነትና የአሳዳጊዎች ሚና--------------31
3.1.2. “ስለ ድልድዩ ልጅ ትዝታ” ማኅበረ ልቡናዊ ማንነትና
የአሳዳጊዎች ሚና---------------------------------------------------44

3.2. “ልጅነት” በ*አለንጋና ምስር*፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ-------------------------------46

3.2.1. “ልጅነት”፤ ማኅበረ ባህላዊ ፍንገጣና የSadistic displacement
ማደሪያ በ“ዘላን”--------------------------------------------------------- 44

3.2.2. “ዘላን”፤ የጨቅላነት “ግንትሮሽ” እና የሁለት ሰብዕናዎች መቃየጥ----- 53

3.2.3. “አለንጋና ምስር”፤ “Oedipus complex” እና የልቡና ፍርቅነት ------ 59

ምዕራፍ አራት

ማጠቃለያ----------------------------------------------------------------------------- 68

ዋቢ ጽሑፎች--------------------------------------------------------------------------71

# አሕጽሮተ ጥናት

*ይህ ጥናት ልጅነት በማሕሌት እና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ በሚል የተደረገ ነው። የጥናቱ ዘዴ በይነ-ቴክስታዊ ሲሆን ስልቱ ደግሞ ፍካሬ ነው። ጥናቱ በተመረጡት ቴክስቶች ውስጥ ልጅነት ከሥነ ልቡና ንድፈ ሃሳቦች አንጻር ቢፈተሽ መልካም ነው በሚል ዕምነት የተደረገ ነው። በቴክስቶቹ የተቀረጹ ልጆች ማኅበረ-ልቡናዊና ሳይኮሴክሿል ማንነት፣* Oedipus complex *እና የልቡና ፍርቅነት፣ የጨቅላነት ግንትሮሽ እና የሁለት ሰብዕናዎች መቃየጥ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ሚቶሎጂዎች የተቀዱ መባያዎች ሰብዕናን መርምሮ ለማሳየት ትኩረት የተደረገባቸው ነጥቦች ናቸው። ጥናቱ ወዲህ በቴክስቶቹ ውስጥ የተቀረጹ ገጸ-ልጆች የብቸኝነት፣ የመከዳትና የመጣል ስሜት የሚስተዋልባቸው እንደሆኑ፣ ወዲህ ደግሞ የአሳዳጊዎቻቸው ሚና አፍራሽ መሆኑ፣ የጨቅላነት ሳይኮሴክሿል ዕድገት ፊክሴሽንና* sadistic displacement *ማደሪያዎች እንደሆኑ ተብራርቷል። ስለሆነም፣ በእነዚህና በትንተናው ውስጥ በ"ተዘነቁ" ሃሳቦች ልጆቹ ማኅበረ-ባህላዊ ኃላፊነትን መሸከም የማይችሉ እንደሆኑ ለማጠቃለል ተሞክሯል። በመጨረሻም በቴክስቶቹ ውስጥ ልጆቹ የተቀረጹት፣ ማኅበረ-ባህላዊ ሥርዓቶችና ተፈጥሯዊ ማንነቶች በመኀራበት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።*

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ሥነ ጽሑፍ እንደሙያ መታየት ከጀመረበት ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ የአጠናን ስልቶች ተቀምረዋል፡፡ የከያኒውን ስሜት አጥብቀው ከሚፈልጉት *Romanticism* መራሹ ሂስ እስከ "አፍቃሬ-አንባቢ"ው *Reader-response*፣ በራቸውን ከዘጉ (ቴክስታዊ ንባብን ብቻ ከሚፈቅዱ) *New criticism* እና *Structuralism* ማኼሻዎች በይነ-ዲሲፕሊናዊነትን ቤቴ እስካሉት ትምህርት ቤቶች የሥነ ጽሑፍ ጥናት ተፈትኗል፡፡ አሁን ላይ ግን፣ ቴዎድሮስ ገብሬ (2001፤xi-xii) እንደሚናገሩት፣ ትኩረቱን በበይነ-ዲሲፕሊናዊነት[1] ላይ አሳርፏል፡፡ ወደ ማኅበራዊ ሳይንሶችና የነገረ ሰብዕ መስኮች እየዘለq የየሙያዎችን የሃሳብ አርቅቆቶች ወደ ራሱ ቤት እየሳበ ያለምዳል፤ ይተልምባቸዋል፤ በኪናዊ ጭብጥነትም ያልቃቸዋል፡፡ "ጓዳቸውን" ከሚፈትሽባቸው ሙያዎች ደግሞ አንዱ ሥነ ልቡና ነው፡፡ በርግጥ በአንድ ቴክስት ላይ ሥነ ልቡናዊ ንባብ ማድረግ፣ አንድም ከደራሲው መነሳሳትና አስተሳሰብ፣ አንድም በተደራሲያኑ ላይ ቴክስቱ ከሚያሳድረው ተጽዕኖ አንፃር መመርመር፣ ከአሪስቶትል ጀምሮ በነበሩ ሃያሲዎች፣ የንግግር ጥበብ ማዕምራን(Rhetoricians) እና ፈላስፋዎች ዘንድ የተለመደ ቢሆንም ቅሉ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የእስብ አርቅቆቶቹን ለሥነ ጽሑፍ ጥናት መጠቀም ግን፣ በፍሮይድ የተጀመረ፣ የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው (Habib፤2005፤571)፡፡ የአለማት በጥቅሉም የዩኒቨርሱ ኪን ነው የሚባለው "ዑደታዊነት" በዚህ አካዳሚያዊ ቅንብብ ውስጥም እንዲሁ ነው፤ አካዳሚውም ቢሆን የዩኒቨርሱ አካል ነውና፡፡ ስለሆነም ይህ ሙያ ከፍሮይድ ጀምሮ በ"ተግሳጽና እሰየው ዕደግ" በሥነ ጽሑፍ ቤት ለምዷል፤ አድጓል፤ ዘምኗልም፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም ከ*ማሕሌት* እና *አለንጋና ምስር* በተመረጡ አራት ቴክስቶች የሥነ ልቡና ንድፈ ሃሳቦችን ምቹ በሆነ ስልት በማልመድ፣

---

[1] በይነ ዲሲፕሊናዊነት የሥነ ጽሑፍ ጥናት አካዳሚያዊ እውነታ ነው ብለው አጥብቀው ባቀነቀኑበት ***በይነ-ዲሲፕናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ*** መጽሐፋቸው፣ ቴዎድሮስ ገብሬ፣ በግርጌ ማስታዎሻቸው ላይ ቃሉን ሲፈቱ፣ "ከአንድ በላይ በሆኑ ዲሲፕሊኖች ጥምረትና ውህደት የማሰብ፣ የመጠየቅ፣ የማጥናት እና የመመርመር ልማድ፡፡" (2001፣ xiii) ይሉታል፡፡

ወዲህ እንዴት ባለ ኪነት እንደለመዱ መመርመር፣ ወዲህ ደግሞ በቴክስቶቹ ውስጥ የተጠሩ ሥነ ልቡናዊ ጽንሰ ሃሳቦችን መፈለግ ነው፡፡

አንድን ሥነ ጽሑፋዊ ቴክስት ከሥነ ልቡና አንጻር ስናጠና የምንመለከታቸው ወይም ልናተኩርባቸው የሚገቡ አራት ጉዳዮች እንዳሉ Wellek እና Warren ይናገራሉ፡፡ እነሱም፣ የደራሲው ሥነ ልቡናዊ ጥናት–እንደ አይነትና ግለሰብ፣ የፈጠራ ሂደቱ፣ ሥነ ጽሑፋዊ ስራው ውስጥ የቀረቡ ሥነ ልቡናዊ አይነቶችና "ህጎች" (መሰረተ ሃሳቦች) እንዲሁም በአንባቢ ላይ ያመጣው/ያሳደረው ተጽዕኖ ናቸው (1949፣75)፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ሦስተኛውን ጉዳዬ ብሎ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻና ማግስት ብቅ ባሉት የሥነ ልቡና ንድፈ ሃሳቦች (አብዝቶ በፍሮይድና በኤሪክሰን) ላይ በመመርኮዝ ጥናቱን አኺዷል፡፡

ጥናቱ በአራት ምዕራፎች ተዋቅሮ ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አንድ ስር በመግቢያ የተመሩ ሰባት ንዑሳን ክፍሎች ተደራጅተዋል፡፡ እነሱም፤ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ እና የጥናቱ ወሰን ናቸው፡፡ በምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የተመለከቱ ሲሆን በምዕራፍ ሦስት ደግሞ ትንተናው ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ አራት ጥናቱ የደረሰባቸው ግኝቶች ተመልክተውበታል፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥናት "'ልጅነት' በ*ማሕሌትና አለንጋና ምስር*፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ" በሚል ርዕስ የተደረገ ነው፡፡ መድበሎቹ የአዳም ረታ ስራዎች ሲሆኑ እንደ ቅደም ተከተላቸው በ1981 እና 2002 ዓ.ም የታተሙ ናቸው፡፡ እኔ የተጠቀምኳት *አለንጋና ምስር* በ2004 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ የታተመችውን ነው፡፡ ደራሲው አስቀድሞ ከሌሎች ደራስያን ጋር *አባ ደፋርና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች እና ጭጋግና ጠል* በሚል መድበል ውስጥ አራት አጫጭር ልቦለዶችን በ1977 ዓ.ም ያስነበበን ሲሆን እነሱም "ሲሮኮ"፣ "ድብ ድብ"፣ "ዕብዱ ሺበሺ" እና "ስፊንክስ" ናቸው፡፡ እነዚህ አጫጭር ልቦለዶች በ2002 ዓ.ም በታተመችው *ማህሌት* ውስጥ ተካተዋል፡፡ ከዚያም በ1997 ዓ.ም *ግራጫ ቃጭሎችን*፣ በ2001 ዓ.ም *እቴሜቴ ሎሚ ሽታን*፣ በ2002 ዓ.ም *ከሰማይ የወረደ ፍርፍርን*፣ በ2003

ዓ.ም ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድን እና በ2004 ዓ.ም ሕማማትና በገናን ለአንባቢያን አቅርቧል፡፡

ይህ ጥናት የአዳም ረታ በሆኑት እነዚህ መድበሎች ውስጥ፣ ማሕሌትና አለንጋና ምስር፣ "ልጅነት" በዋና የታሪክ ጉዳይነት የተሳለባቸውን አራት አጫጭር ልቦለዶች በመውሰድ፣ የፍሮይድን የሰብዕና መዋቅሮችና የ"ሳይኮሴክሿል" እና የኤሪክሰንን የማኅበረ-ልቡና[2] ዕድገቶች የሃሳብ አርቅቆቶች እየታገገና እየመዘዘ "ልጅነት"ን መርምሯል፡፡ ወዲህም ደግሞ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶችን በመፈተሽ የተካሄደ ነው፡፡

በአዳም ሥራዎች ላይ የተለያዩ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ከቃኘኋቸው ጥናቶች ውስጥ አብዛኞቹ የሚያተኩሩት ልቦለዶቹ በቀረቡበት የአጻጻፍ ብልሃት ላይ ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ በ"ነገረ ህላዌ"ና ሚት ላይ አተኩረው ጥናታቸውን አቅርበዋል፡፡ በመሆኑም ልጅነትን እንደ ርዕሰ ጉዳይነት ወስዶ ከሥነ ልቡና ንድፈ ሃሳቦች አንጻር ጥናቱን ያቀረበ አላጋጠመኝም፡፡ ስለሆነም በእዚህ ክፍተትና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተመስርቼ ይህን ጥናት አድርጌያለሁ፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማከናወን ያነሳሱኝ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የመጀመሪያውና ዋናው ጉዳይ ከላይ በዳራው ላይ ለማንሳት የሞከርኩት ሃሳብ ነው፡፡ የአዳም ልጆች በተለያዩ አንባቢያን ዘንድ በዘልማድ የሚወሩና ሃሳብ የሚሰነዘርባቸው ከመሆናቸውም በላይ ከጓደኞቼ ጋር ዘወትር የምንከራከርባቸው ናቸው፡፡ አዳም የሚስላቸው ገጸ-ልጆች ማኅበራዊ ፍንገጣ፣ የልቡና መታጎል፣ የአስተዳደግ "ንጥፈት"ና "ግንትሮሽ"[3]

---

[2] The word 'psychosocial' so far has had to serve as an emergency bridge between the so called 'biological' formulations of psychoanalysis and never ones which take the cultural environment in to more systematic consideration (Erikson,1959፡150).

[3] ይህን ቃል ለእንግሊዘኛው *Fixation* አቻ አድርጌ ተገልግየበታለሁ፡፡ Smada ፍሮይድን በመጥቀስ *Fixation*ን የሚያፍታቱት ከአራት ተከታታይ የልቡናዊ ክስተት ደረጃዎች ጋር በማዛመድ ነው፡፡ በደመ-ነፍሳዊ ግፊትና በማኅበረ-ባህላዊና ግብረ-ገባዊ እሴቶች መካከል በሚኖር "ሽብር" (Traumatism) የሚጠነሰሱ፣ በሱፐር ኢጎ ልዕልና በተፈጠረው የደመ-ነፍስ ስሜት በመፀፀትና በማዘን ከግፊታቸው የሚረግቡበት (Regression)፣ እነዚህ ደመ-ነፍሳዊ ግፊቶች ከሰርካዊ-ክሱትነታቸው ታቅበው የሚታፈኑበት/ የሚጨቆኑበት (Repression) በመጨረሻም ከነበሩበት ልቡናዊ ክፍል ለቀው

የሚስተዋልባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም እነዚህን ጉዳዮች ለምን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አላጠናቸውም? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ከራሴ ጋር ስከራከርና ሳወጣ ሳወርድ ከቆየሁ በኋላ ለማጥናት ወሰንኩ፡፡ የተሰሩ ጥናቶችን በምዳስስበት ወቅትም በዳራው ላይ የጠቀስኳቸውን ክፍተቶች በማግኘቴ ርዕሱን አሁን ባለው መልኩ ለመቀንበብ አስችሎኛል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት፣ “Literary Theory and Criticism-ELFo 621” የተባለውን ኮርስ በከፊል ለማጠናቀቅ በሰባት ገጽ የተገደበ አጭር መጣጥፋዊ ሂስ እንድሰራ ታዝዤ ነበር፡፡ የሰራሁትም በዚህ ጥናት ከተመረጡት በአንዱ፣ “ዘላን”፣ ላይ ነበር፡፡ በዚያች አጭር ሂሳዊ መጣጥፍ ላይ የቀረቡልኝ ትችቶች ለዚህ ጥናት እንድነሳሳ አድርገውኛል፡፡ አንደኛው ለቴክስት ምርጫም እጄን ያረዘመ ምክንያት ይመስለኛል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት ተከታዮች አቢይ እና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፤

### 1.3.1. የጥናቱ አቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ አዳም በ*ማሕሌት* እና *አለንጋና ምስር* “ልጅነት”ን በእንደ ምን አይነት *ሥነ* ልቡናዊ እሳቤዎች፣ በተለይም ሰብዕና፣ እንደሳለ በይነ-ቴክስታዊ ንባብ በማድረግ መተርጎም ነው፡፡

---

የሚሰወሩበትና ወደ ጥልቁ የልቡና ክፍል የሚወረወሩበትና ኢ-ንቁ የሚሆኑበት (Predisposition) ሒደት ውጤት ነው (2005፣588)፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት “ገነተረ” የሚለውን ግስ “በደንብ ሳይሆን ላይ ላዩን በሰለ… አልታኘክ አለ፥ አኞ ሆነ… ሃሳቡን አልቀይር አለ፥ እምቢ አለ” በማለት ያፍታታዋል (1993፣503)፡፡ ስለሆነም፣ ወዲህ የምኞቶች እርካታ የሆነ ቦታ ላይ መዶልዶምንና ቀጣይ አለመሆንን፣ ወዲህ ደግሞ ባለበት የዶለዶመ ሁነት ውስጥ ሳይለወጥ ጽኑዕ ሆኖ በህይወት ዘመን ሁሉ መቀጠልን ፣ ወዲህ ደግሞ በሌላ ዘዴ “መስላት”ን ስለሚያመለክት በግሱ አምድ ላይ “-ኦሽ” የሚል ስም መስራች ምዕላድ ጨምሮ ስያሜውን መጠቀም ተገቢ ይመስለኛል፤ እስከዚያው ድረስ! ስለሆነም ከዚህ ጀምሮ በ*Fixation* ፋንታ ***ግንትሮሽ*** የሚለውን እየተጠቀምኩ እዘልቃለሁ፡፡

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ ጥናት ተከታዮች ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡ "ቴክስቱ" የሚጠራቸውን የልጅ አስተዳደግ ጽንሰ ሃሳቦች በመመርኮዝ የልጆችን ማኅበረ-ልቡናዊ ሰብዕና ይተረጉማል፤ የሚስተዋሉባቸውን ሥነ ልቡናዊ ቀውሶችንም ይመረምራል፡፡የፍሮይድን የ"ሳይኮሴክሿል" እስቦች አቀራረብ በመመርመር የተጨቆኑ ፍላጎቶችን ይፈልጋል፤ የተወሰዱ የአጸፋ ስልቶችንም ይተረጉማል፡፡ ባህላዊና ሚታዊ መባያ ጉዳዮች ጭብጡን እንዴት እንደመሠረቱት ይፈክራል፡፡ ሥነ ልቡናዊ ጭብጦች በሚታዊና ባህላዊ አስተማስሎዎች መገንባት ለሥነ ጽሑፋዊ ኪኑ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ይተነትናል፡፡

## 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በዋና እና ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች የተዋቀረ ነው፡፡

### 1.4.1. ጥናቱ የሚመልሰው አቢይ ጥያቄ

የምርምሩ አቢይ ጥያቄ "'ልጅነት' በ*ማሕሌትና አለንጋና ምስር* በእንደምን አይነት ሥነ ልቡናዊ ሁኔታ ተስሏል;" የሚል ነው፡፡

### 1.4.2. ጥናቱ የሚመልሳቸው ዝርዝር ጥያቄዎች

የሚስተዋሉ የ"ልጅነት" ማኅበረ-ልቡናዊ ሰብዕናዎች ምን ምን ናቸው? ምንጫቸውስ ከወዴት ነው? የአሳዳጊዎች ሚና በልጅነትና በጎልማሳነት ሰብዕና ላይ የሚኖረው ተፅዕኖስ ምን ይመስላል? የ"ሳይኮሴክሿል" እሳቤዎችና አቀራረባቸው ምን ይመስላል? አዳም ለልጅ አሳሳል የሚጠቀምባቸው የሥነ ልቡና ጉዳዮች ለሥነ ጽሑፋዊ ኪኑ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ምንድን ነው? እና ሥነ ልቡናዊ ጭብጦቹ የሚረቅቁባቸው መባያዎችስ ምን ምን ናቸው? የሚሉት ምርምሩ የተመሰረተባቸው ዝርዝር ጥያቄዎች ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ውስጥ "የሚጠቆሙት" የጥናቱ አቀራረብ፣ የጥናቱ መተንተኛ ስልት (ቴክኒክ)፣ ጥናቱ የሚከተለው ንድፈ-ሃሳባዊ ቅንብብና የታላሚ ቴክስቶች አመራረጥ ናቸው፡፡

የጥናቱ አቀራረብ “በይነ-ቴክስታዊ” (Inter-textuality)፣ የመተንተኛ ስልቱ ደግሞ “ፍካሬ” ነው፡፡ የሥነ ጽሑፍ ጥናት በበይነ-ዲሲፕሊናዊ ፈር በሚቀናበት በዚህ ወቅት፣ “በይነ-ቴክስታዊ” የመፈከሪያ ዘዴ ዋና የሂስ “ማቅኛ”ና የቴክስቶችን ፍቺ መፈልቀቂያ ሆኗል፡፡ በቴክስቶች መካከል የሃሳብ መሳሳብና የፍቺ መቃለጥ የሚፈከርበት ነው፡፡ እነ *Krishnaswamy* እንደሚናገሩት፣ ቴክስቱ ከሌሎች ቴክስቶች ያስተጋባቸው [በፍቺ ትዕምርታዊነታቸው] እሳቤዎች መኖራቸውን የመመርመሪያ ዘዴ ነው (2004፣154)፡፡ በቴክስቱ ውስጥ መሠረታዊ ሚና ይዞ የሚመጣ ትዕምርት ፍቺውን ይወስናል፡፡ ስለሆነም የዚህን ትዕምርት ፍቺ በሌሎች ቴክስቶች መፈለግና ለታላሚው ቴክስት ማልመድ የግብር ባህሪው ነው፡፡[4]

Barker ዴሪዳን፣ ባርትዝንና ክሪስቴቫን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት፣ ይህ ዘዴ የቀደሙ አስተማስሎዎችን (representations) ካሁን አስተማስሎዎች ጋር በማስተጋምር (Juxtapose በማድረግ) አዲስ የፍቺ ኮዶችን የመፈልቀቅ ሒደት ነው፡፡ ፍችዎች ከተለያዩ ቴክስቶች የሚሰበሰቡበትና የሚመነጩበት ዘዴ ነው፡፡ አንድ ቴክስት ከነጠላ ፍቺ ይልቅ “ህያው” ከሆነው ባህል የፍቺ ስብስቦችን ይጠራል፡፡ ፍቺ አንድ ምንጭ ያለው ሳይሆን በቴክስቶች መሳሳብ የሚገኝ ነውና (2004፣101)፡፡

ስለሆነም ይህ ጥናት “በይነ-ቴክስታዊ” ዘዴን በመጠቀም ታላሚ አጫጭር ልቦለዶቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ (ብሉይና ሐዲስ ሚቶሎጂ)፣ ከግሪክ እና አፍሪካ ሚቶሎጂዎች፣ እንዲሁም ከባህላዊ አስተማስሎዎች ጋር በማናበብ የተደረገ ነው፡፡

በተመረጡት አጫጭር ታሪኮች ላይ ንባብ ለማካኼድ ያገለገሉ ንድፈ ሃሳቦች ከሥነ ልቡና የተገኙ ናቸው፡፡ የኤሪክሰን ማኅበረ-ልቡናዊ፣ የፍሮይድ የ“ሳይኮሴክሿል” የዕድገት ደረጃዎች እንዲሁም የሰብዕና መዋቅሮች ፍካሬው የጠራቸው ሆነዋል፡፡ እነዚህ ንድፈ ሃሳቦች በራሳቸው የሚጠሯቸው ላካናዊ የፍካሬ ልቡና ጽንሰ ሃሳቦችም ተመልክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በምዕራፍ ሁለት በተብጀው ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ውስጥ የፍሮይድ

---

[4] በዚህ አውድ “ሌሎች ቴክስቶች” ስል ፍቺ ያለመድኩባቸው እንደ ብሉይ፣ ሐዲስ፣ የግሪክና የአፍሪካ ሚቶሎጂዎችን ነው፡፡ ታላሚ ቴክስት ስል ደግሞ ለትንታኔ የተመረጡትን፣ ማለትም “ማሞ”፣ “ስለ ድልድዩ ልጅ ትዝታ”፣ “ዘላን” እና “አለንጋና ምስር”ን ነው፡፡

“ሳይኮሴክሿል” የዕድገት ደረጃ እስቦች አልተካተቱም። ምክንያቱም የሰብዕና መዋቅሮቹ በትንተናው ውስጥ ስለሚጠሯቸው ነው።

ጥናቱ ሁለት አይነት የመረጃ ምንጮችን ተገልግሏል። እነሱም ቀዳማይ እና ዳህራይ ናቸው። ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ሁነው ያገለገሉኝ *ማሕሌት* እና *አለንጋና ምስር* ናቸው። ከሁለቱም መድበሎች ውስጥ የተመረጡት አራት አጫጭር ልቦለዶች ናቸው። በቅድመ ምርምር ዳሰሳዬ እንዳስተዋልኩት፣ በ*ማሕሌት* ውስጥ ካሉት አስራ አንድ አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ “ልጅነት”ን ጉዳያቸው ያደረጉ ሦስቱ ናቸው። እነሱም “ማሞ”፣ “ስለ ድልድዩ ልጅ ትዝታ” እና “ሽቦው” ናቸው። የዚህ ምርምር ተተኳሪዎች የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ናቸው። ከ*አለንጋና ምስር* ከተካተቱት አስራ ሰባት አጫጭር ልቦለዶችና ኖቬላዎች ውስጥ “ልጅነት” ላይ ያተኮሩት አራቱ (“ዘላን”፣ “እንጀራዬን”፣ “ከሰማያዊ ወደ ቦቢ”ና “አለንጋና ምስር”) ናቸው። በዚህ ጥናት ተመርጠው የተመረመሩት ደግሞ “ዘላን”ና “አለንጋና ምስር” ናቸው። “ለምን ይህን አደረክ?” ቢሉ፣ አንድም የ“ልጅነት” ሥነ ልቡናዊ እሳቤዎች የገዘፉባቸው በመሆናቸው ነው። አንድም በርካታ አጫጭር ልቦለዶችን ወስዶ ዳሰሳዊ ንባብ ከማድረግ ይልቅ የተወሰኑትን በጥብቅ መመርመሩ ሳይሻል አይቀርምና ነው፤ ሁሉንም ወስዶ በ“ጉድፍ” ከ“ማስዋብ” የሚነሱ እሳቤዎችን በተመረጡት ላይ ብቻ በ“ጥልቀት” ማየቱ ሳይበጅ አይቀርም ከሚል ግላዊ እምነት የተነሳ ነው። ስለሆነም ጥቅም ላይ የዋለው የናሙና ዘዴ “ዓላማዊ ናሙና” (purposive sampling) ነው። መረጃ አገኝባቸዋለሁ ብዬ ያመንኩባቸው *ማሕሌት* እና *አለንጋና ምስር*ም በዚህ ዘዴ የተመረጡ ናቸው።

ዳህራይ የመረጃ ምንጮች ያልኳቸው ደግሞ የጥናቱ ቀጥተኛ ተተኳሪ ያልሆኑ፣ ነገር ግን ጥናቱ ዳር ይወጣ ዘንድ የመረጃ ድጋፍ የሰጡኝን ነው። ስለ ሥነ ጽሑፍ ንድፈ ሃሳቦች (በተለይም ከሥነ ልቡና የለመዱ እንደ ማኅበረ-ልቡና፣ “ሳይኮሴክሿል” እና ፍካሬ ልቡና)፣ ሂሶች፣ ጥናቶችና ሚታዊ ተረኮች (በተለይም የብሉይ፣ የሐዲስ፣ የግሪክና የአፍሪካ ሚቶሎጂዎች) የሚናገሩ መጻሕፍት በዚህ ውስጥ ይመደባሉ።

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

የመጀመሪያውና መሠረታዊው ጠቀሜታ ሊሆን የሚችለው፣ ለምርምሩ መነሳሳት ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረገውና በጥናቱ ዳራ የቀረበውን የጥናቶች ክፍተት መሙላት ነው፡፡ ይህም በዘርፉ ላለው ዕውቀት አንዳች ክፍተትን ሊሞላ ይችላል፡፡ አዳም ረታ በመድበሎቹ ስለጠራቸው የ"ልጅነት" ሥነ ልቡናዊ ጉዳዮች እና ሥነ ጽሑፋዊ ዋጋ እንዴት እንደሰጣቸው ግንዛቤ ሊያስጨብጥ ይችላል፡፡ የሥነ ልቡና ጣጣዎችና ሥነ ጽሑፍ ያላቸውን ትስስር ሊያሳይም ይችላል፡፡ ይህም የሥነ ጽሑፍን በይነ-ዲሲፕሊናዊነት የሚያሳይ ነው፡፡ ስራዎችን ከሥነ ልቡና አንጻር በመፈተሽ በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል፡፡ ምርምሩን መሰረት በማድረግ በርካታ ሙግቶችን ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ይህም ለሌሎች ምርምሮች መነሻ በመሆን የተከፈተውን በር ሊያሰፋ ይችላል፡፡

## 1.7. የጥናቱ ወሰን

ይህ ምርምር በአዳም ረታ *ማሕሌት* እና *አለንጋና ምስር* የአጫጭር ልቦለድ እና ኖቬላ መድበሎች ውስጥ በተመረጡ አራት ታሪኮች ላይ የልጅነት ልቡና አቀራረፅን ብቻ ከ"ማኅበረ-ልቡና" እና "ሳይኮሴክሿል" የዕድገት ደረጃዎች፣ ከሰብዕና መዋቅሮችና ፍካሬ ልቡና(ከላካን) እሳቦች አንጻር በይነ-ቴክስታዊ ንባብ በማድረግ ላይ የተገደበ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

## 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ንዑስ ክፍል የ“ልጅነት” ጽንሰ ሃሳብ እና “ልጅነት”ን ለመመርመር የሚያስችሉ የሥነ ልቡና ንድፈ ሃሳቦች ተዳሰዋል፡፡ ትንተናውን ቀና የሚያደርጉና ተስማሚ የፍካሬ ልቡና እና የማኅበረ ልቡና ጽንሰ ሃሳቦች ተቀንብበው ቀርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከንድፈ ሃሳባዊ ዳራው ጋር ተስማሚ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦች በትንተናው ውስጥም እየተወዳጁ ተካተዋል፡፡

### 2.1.1. “ልጅነት”

“Why study [a] little child?” በሚለው ጥያቄ ሙግታቸውን የሚጀምሩት Jursied አንድ አዋቂ ይህን ጥያቄ የሚመልሰው በየትኛውም የዕድገት ደረጃ የሚገኝን የሰው ልጅ ለማጥናት መነሻዎቹ ስለሚያስፈልጉ እና ግድም ስለሆነ ነው ይላሉ (1954፣1)፡፡ “ልጅነት” በርካታ ጉዳዮችን “ዘንቆ” የሚይዝ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ አካላዊና ልቡናዊ ጣጣዎች እጅጉን የሚመሰረቱበት የሰው ልጅ ዕድገት የመጀመሪያ ክፍል ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሥነ ትምህርትና በማኅበራዊ ሳይንሶች የ“ልጅነት ጥናቶች” (childhood studies) “እየሰለጠኑ”ና እንደ አካዳሚያዊ ዲሲፕሊን እየታዩ ይገኛሉ፡፡ “ልጅነት”ን እንደ ጽንሰ ሃሳባዊ የሥነ ጽሑፍ መተንተኛ መጠቀምም ሆነ ማኅበራዊና ባህላዊ ቅጦቹን መመርመርም ትኩረት እያገኘ ያለና ዘመነኛ ጉዳይም ሆኗል፡፡ በተለያዩ ዲሲፕሊኖች የተለያዩ አንጻሮችን በመታገግ (ለምሳሌ፤ ታሪካዊ፣ ሥነ ልቡናዊ፣ ሥነ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ…) “ልጅነት” በአቢይ ርዕሰ ጉዳይነት ተመርምሯል፡፡ አሁን አሁን ደግሞ የልጅነት ጥናቶች በበይነ ዲሲፕሊናዊ ንባብ እንዲታሹ ይጠበቃል (Kehily፣2009፣1)፡፡ ለዚህም ይመስላል፤ ሥነ ልቡናና ሥነ ማኅበረሰብ ጉዳዩ እያሉ የሚቀባበሉትና አዳዲስ አንጻሮችን እያቀኑ የሚመረምሩት፡፡

Kehily እንደሚሉት “ልጅነት”ን አጥብቆ በመመርመር የሥነ ልቡና እና የሥነ ማኅበረሰብ ዲሲፕሊኖች ላቅ ያለ ሚና አላቸው፡፡ አሁን ያለው የ“ልጅነት” ግንዛቤ

ምንጮችም እነዚሁ ዲሲፕሊኖች ናቸው፡፡ በሥነ ማኅበረሰብ እና የባህል ጥናት እንደ ጽንሰ ሃሳብ ተወስዶ ይጠናል፡፡ በሥነ ትምህርትና በሥነ ልቡና ደግሞ ትኩረቱ "የልጅ ልቡናዊ ዕድገት" ላይ ይሆናል (7-8)፡፡

ጥናቱን በይነ ዲሲፕሊናዊ ማድረግና ከአንድ ዲሲፕሊን ጽንፍ ማላቀቅ ተገቢነቱ የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡ ለዚህም ይመስላል ኤሪክ ኤሪክሰን (Erik H. Erikson) የፍሮይድን "ባዮሎጂካዊ" የ"ሳይኮሴክሿል" ዕድገት ማኅበረሰባዊነትን በማላበስ የ"ማኅበረ-ልቡናዊ" ዕድገቶችን ያቀኑት፡፡ "ልጅነት" በአንድ በኩል የባህል አስተማስሎ፣ የማኅበራዊ ግንባታ ሐቲት (Jenks፣2009፣111 እና Woodhead፣2009፣17) ሲሆን በሥነ ልቡና በኩል ቀዳሚ የሰው ልጅ ማኅበረ ልቡናዊና "ሳይኮሴክሿል" የዕድገት ደረጃ ነው፤ የጎልማሳነት ህይወት የማንነት መሠረቶች የሚተከሉበትም ነው፡፡ ኤሪክሰን ዕድገቱ የሰብዕና ነው ብለው ሞግተዋል፡፡ ሌሎችም (ምሳሌ Walkerdine፣2009፣112) "ልጅነት"ን ለመመርመርና ለመገንዘብ ሥነ ልቡናዊ ንባብ አመቺ ነው ይላሉ፡፡ በሥነ ልቡና "ልጅነት" ከባቢውን የመላመድና "ተፈጥሯዊ" ማንነትን በከባቢው የመግራት ሂደት ነው፡፡ "Childhood in this way became a developmental process in which adaptation to the environment was understood as a natural stage-wise progression towards a rational and civilized adulthood" (ዝኒ ከማሁ)፡፡ ስለሆነም "ልጅነት" "ተፈጥሯዊ" ብቻም ሳይሆን በተለያዩ ማኅበረሰቦች ውስጥ ማኅበራዊ እሴቶች የሚበለፅጉበትና የሚያድጉበት፣ አንድ ራሱን የቻለ መዋቅራዊና ባህላዊ ቅንጣት ነው፡፡ በዚህ ጎኑ የ"ማኅበራዊ ውቅር" (social construction) ጣጣ ይሆናል፡፡ ወዲህ የጨቅላነት ጊዜ ባለው ማኅበራዊ ቅንብብ እና አውድ ውስጥ የሚበጅና የሚሰራ፣ ወዲህ ደግሞ ከ"ባዮሎጂካዊ" አለመብሰል ይልቅ በተለያዩ ማኅበረሰቦች ዘንድ ያለውን መዋቅራዊና ባህላዊ ቅርጽን የሚያጠይቅ ነው (Jenks፣78)፡፡ ከ"ባዮሎጂካዊ" የዕድገት ጽንፍ በተለየ፣ በማኅበራዊ እስቦች የሚቀኑ ሃሳቦች ጉዳይ በመሆኑም ምሁራን "ማኅበራዊ ውቅር" ነው ይላሉ (ምሳሌ Loo፣2012)፡፡ ስለሆነም "ልጅነት" እንደየ ማኅበረሰቡ እሴቶች፣ እንደየዘመኑ መንፈስ የሚቃኝና እስቦች ህያው የሚሆኑበት ማኅበራዊና ባህላዊ ክስተት ነው (Loo፣59)

በሥነ ልቡና "ልጅነት" የሰብዕና ጣጣ እንደሆነ ተመልክተናል። ሰብዕና ደግሞ የማኅበራዊ ስሪት (construction) እና የ"ተፈጥሯዊ" ማንነት ውጤት ነው። በየትኛውም መልኩ ማኅበራዊና ተፈጥሯዊ ጉዳዮች የአንድን ሰው ሰብዕና ይመሠርታሉ። ስለሰብዕና ብዙዎቹ በየራሳቸው መንገድ ብለዋል። በርካታ የሥነ ልቡና የጥናት አንጻሮችም ሰብዕናን በየራሳቸው ፍልስፍና ይመረምሩታል፤ ይተረጉሙታል። የ"ሥነ ትምህርት" ንድፈ ሃሳብ ቀማሪዎች ሰብዕና የከባቢውን አዎንታዊና አሉታዊ ቅጦች በመኮረጅ የሚበለፅግ ማንነት ነው ሲሉ፤ የ"ማኅበራዊ ንቃተ ኅሊና" (social cognitive) ማዕምራን ደግሞ ሰብዕና ግለሰቦች የሚኖራቸው "የረቀቁ አዕምሯዊ አስተማስሎዎች" (mental representations) ውጤት ነው ይላሉ (Darely፣1986፣442 እና 452)። ይሁን እንጂ በጋራ የሚስማሙበት ፍቺ የሚከተለው ነው ብለው ያስረዳሉ።

> Personality is the organized and distinctive pattern of thought and behavior that characterizes an individual's enduring set of adaptations to his or her world. The study of Personality emphasizes how each of us comes to have a unique and characteristic set of ideas, motives, attitudes, emotions, beliefs and values. Personality theories deals with what makes us think, feel, behave and experience life as we do (441).

በሥነ ልቡና ውስጥ ተደጋግመው ከሚነሱ የሰብዕና ንድፈ ሃሳቦች ውስጥ ገናኖቹ የኤሪክሰን "ማኅበረ-ልቡናዊ ዕድገት" (Psychosocial development of human being) እና ፍሮይዳዊው "ፍካሬ-ልቡናዊ የሰብዕና ቅጥ" (Psychoanalytic model of personality) ናቸው (442)። "ልጅነት" የሰብዕና ጣጣ ነው ካልን ልቦለዶቹን ለመመርመር ደግሞ እነዚህ የተመቹ ንድፈ ሃሳቦች ናቸው።

#### 2.1.1.1. ማኅበረ-ልቡናዊ ዕድገት፤ ኤሪክሰን

ኤሪክሰን (1959፣55-99 እና 1963፣222-242) ከልደት እስከ ሞት የሚዘልቁ የማኅበረ ልቡናዊ ዕድገት ደረጃዎችን በስምንት ተከታታይና ተዛማጅ ደረጃዎች ከፋፍለው አቅርበውታል። ከእነዚህ ደረጃዎች መካከል ቀዳሚዎቹ አምስቱ ልጅነትን የሚመለከቱ ናቸው። ኤሪክሰን እያንዳንዱ ደረጃ የራሱ አዎንታዊና አሉታዊ የሰብዕና ውጤቶችን እያስከተለና አንዱ በአንዱ ደረጃ ላይ እየቆመ የሚጓዝ መሆኑንም ያስረዳሉ። እነዚህን ደረጃዎች እንደሚከተለው ጠቅለል አድርጎ መመልከት ይቻላል።

## 1.“አማኒነት ወይም ተጠራጣሪነት” (Trust Vs Mistrust)

ይህ ደረጃ ከልደት እስከ አስራ ስምንት ወራት ጊዜ ድረስ የሚቆይ የማኅበረ ልቡና ዕድገት ነው፡፡ እጅግ አስፈላጊና ለቀጣዮቹ ደረጃዎች በሙሉ መነሻ የሚሆን ሲሆን ልጁ ሙሉ በሙሉ በወላጆቹ ወይም ደግሞ በጠባቂዎቹ (caregivers) ላይ ጥገኛ ነው፡፡ ስለሆነም በሚደረግለት እንክብካቤና ጥበቃ መሠረት ልጁ የሚያበለፅገው ሰብዕና በቅርቡ ያሉ ጓደኞቹንና ወዳጆቹን የሚያምን ወይም ደግሞ የሚጠራጠር ይሆናል፡፡ የመጀመሪያውን በአግባቡ ካበለፀገ የ“ምቹነት” እና የ“ደኅንነት” ስሜትን ይገነባል፡፡ “ተጠራጣሪነት”ን ካዳበረ ደግሞ የ“ፍርሃት” እና “ያለመተማመን” (ዓለም ተለዋዋጭ ናት፤ ልትተነበይ አትችልም የሚል) ስሜትን ያዳብራል፡፡ በዚህም የ“ጨለምተኝነት” ሰብዕና ህልው የሚሆንበት ደረጃ ይሆናል ማለት ነው፡፡

## 2.“ነፃነት” ወይም “ሃፍረት” (Autonomy Vs Shame and Doubt)

ከሁለት እስከ ሶስት አመት ያለውን ዕድሜ የሚሸፍን ሲሆን ህፃናት የ“ራስን መቻል” (Indepen- dence) ስሜት ለማዳበር የሚታትሩበት ወቅት ነው፡፡ ይጓዛሉ፤ ምን መልበስ እንዳለባቸውና ከማን ጋር መጫዎት እንዳለባቸው በራሳቸው ውሳኔ ለመመራት ይሞክራሉ፡፡ በዚህ ድርጊታቸው እሰየው ከተባሉና በወላጆቻቸው አሊያም በጠባቂያቸው ይሁንታን ካገኙ በራስ የመተማመንን ስሜት ያዳብራሉ፡፡ በተቃራኒው በድርጊቶቻቸው ከተነቀፉ የበታችነት፣ የ“ጎዶሎነት” (Inadquancy)፣ በራስ ያለመተማመን ስሜቶችን ያዳብራሉ፡፡ እነዚህም “ማፈርን” ያስከትላሉ፡፡

## 3.“ተነሳሽነት” ወይም “የጥፋተኝነት ስሜት” (Initiative Vs Guilt)

“ቅድመ ትምህርት ቤት” እያሉ የሚጠሩት ይህ ደረጃ ከሶስት እስከ አምስት ዓመት ያለውን ጊዜ ይሸፍናል፡፡ በዚህ ደረጃ ልጆች ያቅዳሉ፤ ከሌሎች ጋር ለመስራት ይነሳሳሉ፤ ጨዋታዎችንና ሌሎች ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ለመምራት ይፈልጋሉ፡፡ ይህን ዕድል እንዲጠቀሙ ነፃነት ከተሰጣቸው የተነሳሽነትና የብሩኅ ተስፋ (Optimism) ስሜቶችን ያዳብራሉ፡፡ የመወሰንና የመምራት ብቃታቸውም ያብባል፡፡ ይህ ሳይሆን በተቃራኒ

እንክብካቤ ቢሰጣቸው ኃላፊነትን የመፍራት፣ ራስን የመጠራጠር እና የተነሳሽነት ውድቀት ስሜቶች ባለቤት ይሆናሉ፡፡

## 4."ትጋት" ወይም "የበታችነት ስሜት" (Industry Vs Inferiority)

ይህ ደረጃ ከስድስት እስከ አስራ አንድ ዓመት ያለውን የዕድሜ ክልል የሚሸፍን ነው፡፡ ልጆች በሚኖራቸው ማኅበራዊ ግንኙነትና ሰርተው በሚያጠናቅቋቸው ጉዳዮች የበላይነት ስሜትን የሚያዳብሩበት ደረጃ ነው፡፡ በተለይ መምህራን በዚህ ደረጃ ለሚኖር ሰብዕና ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ የህይወት ግቦቻቸውንና ዓላማዎቻቸውን ያቅዳሉ፡፡ በዕቅዶቻቸው እሰየውና በርቱ ከተባሉ ግቦቻቸውንና ዓላማዎቻቸውን ለማሳካት በራስ መተማመንን፣ "ትጋትን" እና የተወዳዳሪነት መንፈስን (sense of competence) ያዳብራሉ፡፡ በተቃራኒው የሚደረግላቸው እንክብካቤ ደግሞ የበታችነት ስሜትን እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን ብቃታቸውን ተጠራጣሪዎች ይሆናሉ፡፡ ስለሆነም አቅማቸውን (potential) እንዳይጠቀሙ እንክን ይሆናቸዋል፡፡

## 5."ጽኑ ማንነት" ወይም "መደናበር" (Identity Vs Role confusion)

ከአስራ ሁለት እስከ አስራ ስምንት አመት ድረስ የሚዘልቅ ሲሆን ልጅነት በዚህ ደረጃ ይጠናቀቃል፡፡ ልጆች ሙሉ በሙሉ ከጥገኝነት መላቀቅ የሚጀምሩበት ደረጃ ሲሆን መጪውን ጊዜ በኃላፊነት ለመምራት ማኅበራዊ ግንኙነቶችንና ቤተሰብን ለመመስረት እንዲሁም የራሳቸውን ቤት ይዘው ህይወትን ለማስቀጠል የሚሞክሩበት ደረጃ ነው፡፡ የህይወት አማራጮችን የሚመለከቱበትና የራሳቸውን ማንነት የሚመሰርቱበት ጊዜ ነው፡፡ በእነዚህ ድርጊቶቻቸው አዎንታዊ ምላሽ ከአካባቢያቸው ካገኙ ጠንካራ የእኔነት ስሜትን ያዳብራሉ፤ ጥገኝነትንም የሚንቁ ይሆናሉ፡፡ለኃላፊነትና ለቁጥጥር የሚኖራቸው ስሜትና አቅም ጠንካራ ይሆናል፡፡ ይህ ካልሆነና ከከባቢያቸው "አፍራሽ" አፀፋ ከተመለ-ሰላቸው በራሳቸው እምነት አይኖራቸውም፤ እርግጠኞች አይሆኑም፤ በፍላጎቶቻቸው ምቹነት አይሰማቸውም፡፡ በጥቅሉ በራሳቸውና ወደፊት በሚመጡ ጉዳዮች ሁሉ ተጠራጣሪዎች፣ የተዘበራረቀ ህይወትን የሚመሩ፣ ጨለምተኛ፣ ለውሳኔ የማይቆርጡ ይሆናሉ፡፡ ይህን ደረጃ በአዎንታዊ መልኩ ማጠናቀቅ ግን በማኅበረሰቡ እሴቶችና የመርኖ ደረጃዎች እና ማኅበራዊ ሆኖ የመኖር ብቃትን (fidelity) ይፈጥራል፡፡ ከዚህ

ደረጃ የሚለጥቁት ደረጃዎች የጎልማሳነት እና የእርጅና ናቸው፡፡ አስቀድመን የጠቀስናቸው ደረጃዎች ለሚከተሉት መሠረት በመሆናቸውና ልጅነት በጎልማሳነት ውስጥ የሚንፀባረቅ በመሆኑ እንመለከታቸዋለን፡፡

## 6.“መወዳጀት መቻል” ወይም “ራስን ማግለል” (Intimacy Vs Isolation)

በአማካይ ከአስራ ዘጠኝ እስከ አርባ አመት ድረስ ያለውን የዕድሜ ክልል የሚሸፍነው ይህ ደረጃ ከሌሎች ጋር ጥብቅ ግንኙነት የሚጀመርበት ነው፡፡ ከቤተሰብ አባል ውጭ ከሆነ አካል ጋር የረጅም ጊዜ ዕቅድ ያለው ጥብቅ ግንኙነት የሚመሠረትበት ነው፡፡ ይህን ደረጃ በተሳካ ሁኔታ መጨረስ ከሌሎች ጋር ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይና ትርጉማዊ የሆነ ግንኙነትን ለመመስረት የሚያስችል ብቃትን ይፈጥራል፡፡ ከሌሎች ጋር የሚኖረን ግንኙነትም ምቹነትን ይሰጠናል፡፡ ልብ መባል ያለበት ይህ ደረጃም ሆነ የቀደሙት “ተደጋጋፊ” መሆናቸው ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ለሚፈጠር አዎንታዊ ብቃት ጠንካራ የማንነት ሰብዕና ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደረጃ በአሉታዊ መንገድ የሚጠናቀቅ ከሆነና መወዳጀት ያለመቻል ውድቀት ከተከተለ ታማኝነትንና ቁርጠኝነትን (Commitment)ን የመሸሽ፣ ግንኙነቶችን የመራቅና የመፍራት፣ ብቸኝነትን የመምረጥ ስሜትን ያስከትላል፡፡

## 7.“ትውልድን ማነፅ” ወይም “መስነፍና ከኃላፊነት መራቅ” (Generativity Vs Stagnation)

ይህ ደረጃ የጎልማሳነት ጊዜ ሲሆን በአማካይ ከአርባ እስከ ስልሳ አምስት አመት ይዘልቃል፡፡ በዘመነ-ጎልማሳነት ራሳችንን የማነፅ ስራ በራሳችንና በቤተሰባችን ኃላፊነት ላይ የወደቀ ነው፡፡ በማኅበራዊ ተቋማት ውስጥ መሳተፍ፣ ኃላፊነቶችን መቀበል፣ በስራ ውጤታማ መሆን… በዚህ ደረጃ የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ማሳካት ንቁ የማኅበራዊ ተሳትፎንና ግንኙነት የመፍጠር ስሜትን ያዳብራል፡፡ በጥቅሉ ማኅበራዊ ኃላፊነትን በአግባቡ እንደተወጣና ቀጣዩን ትውልድ ህያው እንዳደረገ ይሰማዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ያለመሳካት ውጤት የልፍስፍስነት፣ ጠንካራ ሰራተኛ ያለመሆን፣ የ“ላሸቀ” ማኅበራዊ ግንኙነትና ተሳትፎ ስሜቶችን ያስከትላል፡፡

## 8.“ሐቀኝነት/ኩራት” ወይም “ፀፀት/ተስፋ መቁረጥ”

## (Integrity Vs Despair)

ይህ ደረጃ ከስልሳ አምስት አመት በኋላ ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ነው፡፡ ያለፉት ደረጃዎች የሚጠቃለሉበትና የሚታወሰቡት ነው፡፡ ባለፉት ደረጃዎች አሉታዊ ስሜትን ያዳበሩ ህይወታቸው በከንቱ እንዳለፈ እና እንደባከነ በማሰብ ይፀፀታሉ፡፡ በመማረርና በመፀፀት ስሜቶች ቀሪ ህይወታቸውን ይገፋሉ፡፡ አዎንታዊ ስሜቶችን ያዳበሩ ደግሞ በስኬታቸው አንዳች የኩራት መንፈስን ይጎናጸፋሉ፡፡ የታማኝነትና እውነታዊነት (Integrity) ስሜትን ያዳብራሉ፡፡ ይህም የደስታ ስሜትን ይፈጥርላቸዋል፡፡

### 2.1.1.2. ፍሮይዳዊ የሰብዕና መዋቅሮች

በፍሮይዳዊያን ሶስት የሰብዕና መዋቅሮች ያሉ ሲሆን፣ በመዋቅሮቹ ውስጥ የሚፈልቁ ክስተቶች በሚያካሂዱት ፍትጊያ የግለሰቡ ማንነት ይፈጠራል፡፡ መዋቅሮቹን ከዚህ እንደሚከተለው እንመ-ለከታለን፡፡

### ሀ. ኢድ (Id)

ይህ ሰብዕና እጅጉን ኢ-ንቁ ልቡናዊ ነው፡፡ ከሌሎች የሰብዕና መዋቅሮች አስቀድሞ በሰው ልጅ ልቡና የሚከትም፣ ለሌሎች መዋቅሮች መፈጠር ምክንያት የሚሆንና በሰፊውና ጥልቁ የልቡና ክፍል “የሚርመሰመስ”፣ የሰው ልጅ በማኅበራዊ ስርዓት ከመተብተቡ በፊት ህልውናው ምሉዕ፣ ኢ-ግብረ ገባዊና ኢ-ማኅበራዊ የሆነ የሰብዕና መዋቅር ነው፡፡ በጊዜ ልደት ልቡናን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠርና ሁሉንም አይነት ደመ-ንፍሶችና ልቡናዊ ግፊቶች የያዘ ኢ-ንቁ ልቡናዊ የሰብዕና አይነት ነው፡፡ ጨቅላው የማኅበረሰቡን ሥርዓት በቋንቋ አማካኝነት ከሚቀላቀልበት ጀምሮ እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ድረስ ተግባሮቻቸው (የኢጎና ሱፐር ኢጎ) በሙሉ በኢድ ግፊት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ወዲህ ኢድን በማገድ፣ ወዲህ ደግሞ ግፊቶቹን በማልዘብ እና ማኅበራዊነትን በማላበስ ህያው እንዲሆን የሚያደርጉ ናቸው (እነ Darely፣1986፣444)፡፡

ተግባሩ ያለምንም ማኅበራዊ ጉዳዮች አለቃነትና ግብረ ገባዊ ማዕቀቦች ተፈጥሯዊ ግፊቶችን ማርካት ብቻ ነው፡፡ ይህም ማኅበራዊ ልሽቀትን ለማስከተል የሚታትርና በራሱ በግለሰቡ ላይም እርካታን በመፈለግ በሚያደርገው ልቡናዊ ሽኩቻ ጉስቁልናን

የሚያስከትል ነው፡፡ ለራስም ሆነ ለሌሎች ምቾት የሚሰራ አይደለም (እነ Guerin፣2005፣157)፡፡ ኢድ ግለሰባዊም ሆነ ማኅበረሰባዊ ጉዳቱ ከባድ በመሆኑ ይህን ጉዳይ ለማረቅ ሌሎች የሰብዕና መዋቅሮች ይጠነሰሳሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ "ኢጎ" (*Ego*) አንዱ ነው፡፡

## ለ. ኢጎ (Ego)

ሁለቱን የሰብዕና አይነቶችን (*Id* እና *Superego*ን) ለማመጣጠን የሚጥር የሰብዕና መዋቅር ነው (Josselyn፣1964፣23)፡፡ በማኅበራዊው ዓለምና ከዚህ ስራት ውጭ ሆኖ በሚገዳደረው *Id* መካከል መሃከለኛ በመሆን የሚሰራ ነው፡፡ የማኅበራዊውን ዓለም እና የኢ-ግብረ ገባዊና ኢ-ማኅበራዊ ዓለም የስሜትና የ"ግንኙነት" ጡዘቶችን አመጣጣኝ የሰብዕና መዋቅር ነው፡፡

> This is the rational governing agent of the psyche. Though the ego lacks the strong vitality of the id, it regulates the instinctual drives of the id so that they may be released in nondestructive behavioral patterns. And though a large portion of the ego is unconscious, the ego nevertheless comprises what we ordinarily think of as the conscious mind (Guerin et al,157).

የኢጎ አብዝቶ መሰልጠን፣ የኢድ ግፊቶች ኢ-ሞራላዊ እና ኢ-ማኅበራዊ እንደሆኑ እያወቀ እንዲተገብሩት ያስገድዳል፤ አብዛኛው መዋቅሩ በኢ-ንቁ ልቡና ውስጥ የሚያድር ነውና፡፡

## ሐ. ሱፐርኢጎ (Superego)

በንቁ ልቡና ውስጥ የሚከትም፣ አዘውትሮ ማኅበራዊ ጉዳዮች ባህል፣ ወግና ልማድ በዕለታዊ የኑሮ ዘይቤ ላይ እንዲሰለጥኑ የሚሰራ ነው፡፡ በመሆኑም ሰዎች በ"ማመዛዘን የላቀ"ና ግብረ ገባዊ የሆነ ጥብቅ ሰብዕና እንዲኖራቸው ብሎ የሚሰራ ነው፡፡

> ሱፐር ኢጎ የኢድ ተቃራኒ ነው፡፡ ኢድ የልቡና ደመ-ነፍሶቻችንንና ፍትወታዊ "ቅንዝራችን"ን (libido) እንዳይገለጡ የሚቃወምና ማኅበራዊ-ውጉዝ የሆኑ ፍላጎቶችንና ምኞቶችን እርካታ ብቻ ህያው ለማድረግ የሚታትር የሰብዕና አይነት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ከማኅበረሰቡ ስምምነቶች ውጭ የሆኑ ምኞቶች የታቆሩበት ነው፡፡ ሱፐር ኢጎ የእነዚህን ግፊቶች

> ባህላዊ አይታሰቤነት ለማጽናት የሚሰራና የኢድን ምኞቶች ለማኮላሸት ሲል ንቁ የሆነ የሰብዕና መዋቅር ነው (Tyson፣2006፣25)፡፡

የኢድ ግፊቶችን አንድም ተመጣጣኝ የእርካታ ምንጭ እንዲያገኙ በኢጎ በኩል ዕርቅን ይፈልጋል፤ አንድም ደግሞ ራሱ እጁን አርዝሞ የኢድን ፍላጎቶችና ምኞቶች ያኮላሻል፡፡ ማኅበራዊ ቅቡልነት የሌላቸው ጉዳዮችን (እንደ ፍትወታዊ ስሜቶች፣ ጠብ አጫሪነትና ኦዲፐሳዊ ደመ-ነፍስ/Oedipal instinct ያሉ) በኢ-ንቁ ልቡና ከትመው እንዲፀኑ ይታገላል፡፡ ፍሮይድ፣ የዚህ ሰብዕና ዕድገት የቤተሰብ ወይም የአሳዳጊ ተፅዕኖ ውጤት ነው ብለው ይሞግታሉ፡፡ ማኅበረሰቡ ጥሩ/መጥፎ፣ ጽድቅ/ኩነኔ … ብሎ የደነገጋቸውን ስራቶች በማክበርና ባለማክበር በሚኖር ቅጣት (punishment) እና "በጎ" ይሁንታ (reward) የሚበለፅግ ነው (እነ Guerin፣158)፡፡

### 2.1.1.3. ቋንቋ፣ ልጅነት እና ላካን

ላካን፣ "ልጅነት" ማኅበራዊ ጉዳዮችና "ተፈጥሯዊ ፍላጎቶች" ፈር የሚይዙበት እንደሆነና የዚህ ፈር ቀያሽና አበልጻጊ ደግሞ ቋንቋ እንደሆነ ሞግተዋል፡፡ ጨቅላው በቋንቋ አማካኝነት ማኅበራዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ማስተማሰል የሚጀምርበትን ደረጃ "Symbolic Order" ብለው ይጠሩታል፡፡ ይህ ደረጃ ማኅበራዊ ሥርዓቶች፣ ንጽረተ ዓለሞች፣ እምነቶች፣ በአጠቃላይ የ"ተፈጥሮ" ተቃርኖዎች በቋንቋ አማካኝነት ተቀምረው (ታምረው) ለጨቅላው የሚቀርቡበትና ጨቅላውም ማኅበራዊውን የትዕምርት ጉዞ የሚቀላቀልበት ነው፡፡ የግለሰቡ ማንነትም በእነዚህ ማኅበራዊ ስራቶች ላይ ይወድቃል፡፡

> The symbolic is the domain of culture, all the rules and symbolic meanings which exist 'out there' before I ever come along, especially, in Lacan's view, as a particular structure of signifiers, the Other. [… This is] the shift from Being into Meaning as growing up, development from nature into culture, or in Lacan's terms, from the real to the symbolic. When I was born I was absolutely and completely myself, immune to any distinction between myself and the world. Entering the circle of Meaning, of language, which is the possession of other people, I begin to have a meaning (Easthope, 2003፡90-91).

በዚህ ማኅበራዊነቱ፣ ቋንቋ፣ በጨቅላው ሰብዕና ላይ ተፅዕኖው ከ"ተፈጥሮ" በተቃራኒ ነው የሚሉት ላካን፣ ግለሰቡ ቋንቋውን አይፈጥርም፤ ቋንቋው ግለሰቡን ይፈጥራል እንጂ። አስቀድሞ ከቤተሰቦቹ ጋር ቋንቋ ነበር፤ ከእሱ ጋር ግን አልነበረም ብለው እንደሚሞግቱ Grosz ይናገራሉ (1998፣97)።

የጨቅላው ወደ ቋንቋ መሸጋገር በማኅበራዊ ግንኙነት ስርዓት ውስጥ የእሱን "ቦታ"(Position) እንዲፈልግ ያስችለዋል፤ ያስገድደዋል (ወንድ/ሴት፣ አባት/እናት፣ ባል/ሚስት፣ ጎረምሳ/ኮረዳ፣ ወንድም/እህት ...) (እነ Krishnaswamy፣2004፣52)። በዚህ ሂደት ውስጥ ተፈጥሯዊ ፍላጎቶቹ የሚላሸቁበት ጨቅላው በማኅበረቡ ዘንድ ፀያፍ የሆኑና የ"ሚናቁ" ጉዳዮችን ከንቁ ልቡናው አስወግዶ ወደ ጥልቁና "አይረኬው" የአዕምሮ ክፍል ይወረውራቸዋል። ንቁ ልቡናውም የእሱ ማንነት ሁኖ ብቅ ይላል። በመሆኑም፣ በቋንቋ አማካኝነት ሁልጊዜም ቢሆን "ፍላጎቶች"ና "ምኞቶች" ሊሟሉ እንደማይችሉ ይማራል፤ እሱም በቀቢጸ-ተስፋ እስከመጨረሻው ከንቃተ ህሊናው ያስወግዳቸዋል። ይህም በቋንቋ አማካኝነት የሚመጣ የመጀመሪያው የስሜት መጨቆን ነው።

ቅድመ ልሳን ፍላጎቶች በቋንቋ አማካኝነት ከንቁ ልቡና እንዲሰወሩ ተደርገው በኢ-ንቁ ልቡና ውስጥ ሲታቆሩ እንደ "ጠፍ ገሞራ" (dormant volcano) ናቸው፤ ዝግ ሆነው አጋጣሚውን ሲያገኙ የሚፈነዱ፣ መውጫ ቀዳዳን የሚጠብቁ፣ በጥልቁ የልቡና ክልል ውስጥ የ"ሚፋጁ" ከሰርካዊው ንግግር ጋር እየታከኩ ብቅ የሚሉ፣ ለዘላለም ምንጫቸው የማይደርቅባቸው። በላካን (በThom ውስጥ እንደተብራራው)፣ እነዚህ ፍላጎቶች በቋንቋ አጠቃቀም "ታከው" ብቅ ይላሉ። ላካን፣ የያቆብሰንን(Jakobson) "ሜታፈር"ና "ሚቶኒሚ" የእስብ አርቅቆቶች ከፍሮይዳዊያን "እመቃ" (condensation) እና የ"ቅጅዎች ፍለሳ" (displacement) ጋር አዛምደው በመመርመር የቋንቋ አጠቃቀሞች የኢ-ንቁ ልቡና "ደመ-ነፍሳዊ" (instinctual) ግፊቶች ብቅ የሚሉባቸው እንደሆኑ ሞግተዋል (2003፣44-50)።

"ልጅነት" በቋንቋ አማካኝነት የሚበለፅግ ማንነት ሲሆን እጅግ የፀነኑና ኢ-ግብረ ገባዊና ኢ-ማኅበራዊ ፍላጎቶች፣ ማንነቶችና በጥቅሉ ሰርካዊውን ህይወት የ"ሚንቁ" የኢ-ንቁ ልቡና እስቦች ደግሞ ከቋንቋ አቅም በላይና በሰርካዊው የልሳን ተራክቦ ህያው የሚሆኑ ባለመሆናቸው በ"እመቃ" እና የ"ቅጅዎች ፍለሳ" በሰርካዊው ህይወት ውስጥ

ጎልዮታቸውን ያገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ በ“metaphor” እና “metonomy” የቋንቋ አጠቃቀሞች የሚሆን ነው፡፡ ላካን፣ ሜታፈርን ከ“እመቃ” ሚቶኖሚን ደግሞ ከ“ቅጅዎች ፍለሳ” ጋር አጎዳኝተው የኢ-ንቁ “ደመ-ነፍሳዊ” ፍላጎቶች ከሰርካዊው ሥነ ልሳናዊ የትዕምርት ሂደት ጋር እየለዘቡ የሚከሰቱባቸው ናቸው ብለው እንደሞገቱ ምሁራን ይናገራሉ (ምሳሌ፡-Thom፣2003፣36፤ Grosz፣1998፣98-101)፡፡ “ልጅነት” የኢ-ንቁና ንቁ ልቡና እስቦች ህያው የሚሆኑበት የዕድገት ደረጃና የሁለቱ ድንበር ደግሞ በ“አማሪዎች ጥምረት” (Chain of Signifiers) የሚፀና እንደመሆኑ እነዚህን የላካን ንድፈ ሃሳባዊ ቅምሮች (Metaphor እና Metonymy) በትንተናው ከግምት ማስገባቱ የሚከፋ አይሆንም፡፡ የ“ልጅነት” እሳቤንም ለመፈከር የተመቹ ናቸው፡፡

እንደ ላካን፣ በማኅበራዊና ባህላዊ ስራቶች፣ በስራቶቹ ገደቦች ሊቦርቁ ያልቻሉ “ደመ-ነፍሳዊ” ፍላጎቶች በመታመቅ (condensed በመሆን) ወይም ደግሞ በ“መፍለስ” በኢ-ንቁ ልቡና እና በንቁ ልቡና መካከል ያለውን “መርማሪ መስመር” (censorship) ያልፋሉ፡፡ አዕምሯዊ አሰራሩም ህልውናው በዚሁ ላይ ይመሰረታል፡፡ የተጨቆኑ ፍላጎቶች ወደ ንቁ ልቡና እንዳይደርሱ የሚከለክላቸውን መስመር አልፈው ለመገለጥ በሚያደርጉት ሽኩቻ አልሆንልህ ሲላቸው በህልም፣ አንድም፣ የ“latent-dream thoughts” ምስሎች፣ ትዕምርቶችና ሌሎችም በ“manifest dream content” እጅግ ታምቀው፣ ነገር ግን በርካታ አሃዶችን ከመጀመሪያው የህልም አይነት በመጥራት፣ አንድም፣ እነዚህ ምስሎችና ትዕምርቶች ለቅጅዎቻቸው(for their derivatives) ቦታቸውን በመልቀቅ አሊያም በቦታቸው ተመሳሳያቸውን በመላክ ወደ ንቁ ልቡና ለመድረስ እንደሚሞክሩ ሁሉ (በፍሮይዳዊያን)፣ በላካናዊያኑ ደግሞ በሁለቱ የቋንቋ አጠቃቀሞች መስመሩን ጥሰው ያልፋሉ (እነ Wolfreys፣2006፡100)፡፡ ስለሆነም “ልጅነት”ን ከእነዚህ የቋንቋ አጠቃቀሞች አንፃር መፈተሽ ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡

### 2.1.2. ሥነ ጽሑፍና ሥነ ልቡና

የሥነ ጽሑፍ ጥናት በርካታ ሙያዎችን የሚነካካ እንጂ በሩን ዘግቶ ራሱን ያገለለ አይደለም፡፡ የበርካታ ዲሲፕሊኖችን ድንበር እየጣሰ መሠረተ ሃሳቦቻቸውንና ንድፈ ሃሳቦቻቸውን በሚስማማው መልኩ ያለምዳል (ቴዎድሮስ፣ 2001፣ xi-xii)፤ እነሱም ተውሰው ያለምዳሉ፡፡ በተለይ የበይነ-ዲሲፕሊናዊነት ጥናት ትኩረት እያገኘ ከመጣበት

20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በ"አውሮፓውያን" ፍልስፍናና ሥነ ጽሑፋዊ ንድፈ ሃሳቦች ላይ "ልቆ" የነበረ ሲሆን፣ የመዋቅራውያንና ቋንቋ መራሹ የፍካሬ ልቡና ንቅናቄ (በጃኩዊስ ላካን)፣ በ70ዎቹና 80ዎቹ በአዲስ መልክ ብቅ ያለው ማርክሲሳዊ ሂስ እና የ"deconstructionist"ኦች የሂስ ጉዞ በዲሲፕሊኖች መካል የተበጁ ድንበራትን በማፍረስ ወደር አልነበራቸውም፡፡ በተለይም ዘመነኛ በይነ-ዲሲፕሊናዊ የንድፈ ሃሳብ ንቅናቄዎችና የጥናት አስማሪዎች "De-"፣ "Post-"፣ "Anti-" ወ.ዘ.ተ. በሚሉ ቅመራዎች ቀዳሚ የየዲሲፕሊኖች ንድፈ-ሃሳቦችንና ፍልስፍናዎችን እየከለሱና የተበጁ ድንበሮችን እየናዱ ጥናቶችን በይነ-ዲሲፕሊናዊ እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል (Klein,2005፡4-5)፡፡

እንኳን በይነ-ዲሲፕሊናዊነት ጥናቶቻችንን በሚንጥበት በዚህ ዘመን ቀርቶ፣ ሥነ ጽሑፍና ሥነ ልቡና ከግሪካውያኑ ማዕምራን (ከእነ አሪስቶትል) ጀምሮ ሲተሳሰሩ፣ አንዱ ባንዱ ላይ አሻራውን ሲያሳርፍ እዚህ የደረሱ እጅግ "ተቃላጭ" ዲሲፕሊኖች ናቸው፡፡ ከተመሳሳይ ማህፀን፣ ሰብዓዊ ልቡና፣ የሚቀዱ መሆናቸውን የበይነ-ዲሲፕሊናዊነት አቀንቃኝ ማዕምራን (ምሳሌ Parkin-Gounelas፣2001፣x) የሚሞግቱላቸው እነዚህ ዲሲፕሊኖች፣ በርካታ የግንኙነት ቅርፆች አሏቸው፡፡ የፍካሬ ልቡና ጽንሰ-ሃሳቦችን በሥነ ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ መጠቀም እና የኢ-ንቁ ልቡና አሰራርን ለማሳየት መሞከር አቢዩ ጉዳይ ነው፡፡ እንደነ ዌሌክና ዋረንም፣ የሥነ ጽሑፍ ሥነ ልቡናዊ የአጠናን ሂደት በ"አፍአዊ" (Exstrinsic) አንጻር ውስጥ የሚዘልቅ ሲሆን ተዛምዷቸው በአራት ጉዳዮች ላይ የሚገራ ነው፡፡ ዳሩ ግን የሚፀነው በሥነ ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ የሚገኙ ሥነ ልቡናዊ አይነቶችንና መሠረተ-ሃሳባዊ ህግጋትን እየፈለቀቁ መተንተን ነው ይላሉ (1949፣75)፡፡ በፍካሬው ሂደት የሥነ ጽሑፋዊ ኪን ዋጋን እንዴት እንዳመጡም መመርመር ሊሳት የማይገባ ጉዳያችን (ዬ) ነው፡፡

የበይነ ዲሲፕሊናዊነት አቀንቃኞች (ምሳሌ Parkin-Gounelas)፣ በሁለቱ ዲሲፕሊኖች መካከል የነበረው ድንበር መናድ የጀመረው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሥነ ልሳን አብዮት መቀጣጠል እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በድህረ ዘመናዊነት "discourse" ደግሞ ይህ የድንበር ጣጣ የሚያስጨንቅ ጉዳይ ሳይሆን ይልቁንም ሁሉም የእኔ በሚሏቸው ወላዊ ጉዳዮች ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ ይናገራሉ (2001፣x)፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ፣ ፍሮይድ ፍካሬ ልቡና የነበረውን የህክምና ዕውቀት ሙያዊ ድንበር ለማፍረስ የሚያስችል እና በይነ ዲሲፕሊናዊነቱን የሚስብ መንገድ አድርገው ይመለከቱት እንደነበር የሚያስረዱት Moran፣ ፍካሬ ልቡና እንቅጩን በሚያስተናብሩ ገሃድ ወሰኖች የተቀነበበ ሳይሆን የኢ-ንቁ ልቡና ንቃቶች የሆኑትንና በሁሉም አይነት የሰብዓዊ እስቦች፣ ስሜቶችና ባህሪ ላይ የሚያሳድሯቸውን ተፅዕኖዎች ሁሉ ይመለከታል ብለው ይሞግታሉ፡፡ እጅጉን ደግሞ ፍካሬ ልቡና እንደ ሥነ ጽሑፋዊ ሂስ መሠረታዊ የ"ነገረ-ፍካሬ" (Hermenutics) ግብር ነው ይላሉ፡፡ "ለምን ቢሉ?"፣ የኢ-ንቁ ልቡና እስቦች ክሊኒካዊ በሆነ አካሄድ የሚደረስባቸው ሳይሆኑ በንቁና በቅድመ ንቃተ ልቡና ባህሪዎቹ እና በቋንቋ አጠቃቀም በህልሞች፣ በ"አፍ ስቻ" (slips of tongue) እና በ"ነፃ ቅንጅት" የሚጋለጡ በመሆናቸው እንደሆነ ይሞግታሉ (2002፤96-97)፡፡

የቀደምቱ የፍካሬ ልቡና ሂስ "ቴክስቱን" የደራሲው የኢ-ንቁ ልቡና ምኞቶች፣ የማይነጥፉ ተፈጥሯዊ ፍላጎቶች እና የልቡና መታጎልን ማስቀየሻ (neurosis sublimation) እንደሆነ "የሚደሰኩር" በመሆኑ የሥነ ጽሑፍን መብት እጅጉን ተጋፍቷል፤ በተለይም የፍሮይዳዊያን፡፡ ይሁን እንጂ በኋለኛው የፍካሬ ልቡና ዘመን፣ ላካን፣ የሥነ ጽሑፍንና የፍካሬ ልቡናን የ"ጌታ-ሎሌ" ግንኙነት እስብ አቃንተው፣ የሥነ ጽሑፋን የተረክ መዋቅር ተመርኩዘው፣ አንድም፣ የቴክስቱን ሥነ ልቡናዊ ብልሃት፣ አንድም፣ የግለሰቡን የ[ገጸ ባህሪያትን] አዕምሯዊ አሰራር መመርመር እንደሚቻል አሳይተዋል (Moran፤99)፡፡

ሥነ ጽሑፍንና ሥነ ልቡናን ስናስተሳስርም ሥነ ጽሑፍ ከልቡና ነቅቶ በአዕምሮ የሚመነጭ እና አፋዊ ስለሆነ ብቻም አይደለም፤ የኢ-ንቁ ልቡና ትዕምርቶች፣ ፍላጎቶችና ግፊቶች በአጠቃላይ የእስቦች የአገላለጽ ስልቶችና ምኞቶች የሚገኙበት ስለሆነም ጭምር እንጂ፡፡ እነዚህ ሥነ ልቡናዊ እውነታዎችም ቢሆኑ ህያው ስለሚሆኑበት ብቻም አይደለም፡፡ እንደነ ዌሌክና ዋረን ሥነ ልቡናዊ እስቦች (ይልቁንም ኢ-ንቁ ልቡናዊ) ከሥነ ጽሑፍ ጋር ዝምድና የሚፈጥሩት ኪናዊ ተጣምሯቸው እና ውህደታቸው ሲሰምር እና እነሱም በዚህ አይነት የታሪክ መዋቅር ውስጥ ለመገኘት ሲፈቅዱ ብቻ ነው (88)፡፡ ከዚህ ከፍ ሲልም፣ ሥነ ጽሑፍና ሥነ ልቡና፣ በሠው ልጆች ማንነት፣ በትዕምርት የአፈጣጠርና የአጠቃቀም ብቃታቸው ላይ ሁሉ ያገባኛል የሚሉ

ዲሲፕሊኖች ናቸው፤ “Literature and Psychology […] are concerned with human motivations and behavior and with man’s capacity to creat and use symbols. In this process, both have become involved in the study of the subjective side of man.”(Edel,1961፡96)፡፡ ወዲህ ግላዊ ማንነቶች ላይ ጥናታቸውን ያነጣጥራሉ፤ ሥነ ጽሑፍ ገፀ-ባህሪያትን እንደ ግለሰብ እንጂ እንደ ስብስብ ወስዶ አይጨፈልቅምና፡፡ ወዲህ “ወላዊ”ና ግለሰባዊ ጉዳዮችን በትዕምርት ለመመርመር የሚሞክሩ ናቸው፤ ሥነ ጽሑፍ ፍቺንና የኪናዊ ዋጋን፣ ሥነ ልቡና ደግሞ የልቡናዊ መታጎሎችን (Psychical Disorder) ምንጭ ለመፈለግ፡፡ ስለሆነም ዝምድናቸው ከፍ ያለ ነው፡፡

Abrhams እንደሚሉት፣ የተከለከሉ፣ በተለይም ፍትወታዊ ፍላጎት፣ ከነባራዊው/ ሰርካዊው የሰው ልጅ አኗኗር ጋር ወደ ግጭት ስለሚገቡና ስለሚጨቆኑ ወደ ኢ-ንቁ ልቡና አልፈው በዚያ ይታቆራሉ፡፡ ንቁ ልቡናም እነዚህን የሰርክና ማኅበራዊ ጉዳይ “ተጋፊዎች” በ“ego” አማካኝነት ከሰርካዊው ህይወት በመጋረድ ይጨቁናል፡፡ በኪናዊ ስራዎች ውስጥ የሚስተዋሉና እነዚህን የተጋረዱ (Mask የተደረጉ) “ተጋፊዎች” የሚያሳኩባቸውና የኢ-ንቁ እና ንቁ ልቡናን ሰብዕናዊ አሰራር ተመጣጣኝ የሚያደርጉባቸው ስልቶችም እንዳሉ ይጠቁማሉ (1999፣247-249)፡፡ ይሁንና አንድን ቴክስት በሥነ ልቡና መነጽር ስናነብና ስንፈክር ከእነዚህ ሰርካዊ ዑደቶች (የንቁ ልቡና ማኅበራዊ ገዢነት) ጀርባ መሄድ እንደሚገባ Eagleton ይመክራሉ (2008፣153)፡፡

በርግጥ ባለብዙ የፍካሬ አማራጮች ባለቤት የሆነውን ሥነ ጽሑፍ ለመመርመር አንድን አንጻር ብቻ መጠቀም ተገቢ ያልሆነና አቅም የሚያሳጣ ነው የሚሉት እነ Guerin፣ ከአንድ በላይ አንጻሮችን “እያቃለጡ” በመጠቀም በሥነ ጽሑፋዊ ስራው ውስጥ የሚመጡ ጭብጦችን ማግኘት “ኮዶችንም” መፍታት የተሻለ እንደሆነ ይመክራሉ፡፡ ሥነ ልቡናዊ አንጻር በዚህ በኩል የ“ነገረ ኪን” ጥናት ብቁነት ጥያቄን የሚያጭር ቢሆንም፣ የስራውን ጭብጣዊና ትዕምርታዊ ሚስጢሮችን ለመፍታት ግን በርካታ ጥልቅ ፍንጭዎችን ሊያስገኝ የሚችል እንደሆነም ያስረዳሉ (2005፣153)፡፡ በሀገራችንም፣ በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ጥናቶች የሥነ ልቡና ንድፈ ሃሳቦችን መታገኒያ አድርገው ተሰርተዋል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ሊወዳጁ ይችላሉ ብዬ ያመንኩባቸውና

ባደረግኩት የቤተ-መጻሕፍትና የበይነ-መረብ ዳሰሳ ያገኘኋቸውን ከዚህ አስከትዬ ለመቃኘት እሞክራለሁ፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ከጥናቴ ጋር በቅርቡ የሚወዳጁ ነገር ግን ለየቅል ዓላማን ያነገቡና ያሳኩ፣ በሩቁ ደግሞ የሚጠራሩ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች፣ የጉባዔና የጆርናል መጣጥፎች ተቃኝተዋል፤ ልዩነታቸው፣ መወዳጀታቸው እና መጠራራታቸውም ተጢኗል፡፡ ጥናቶቹን በሁለት መልኩ ቅኝት አድርጌባቸዋለሁ፡፡ በመጀመሪያ የምመለከታቸው በማነሳቸው ምክንያቶች ጥቅል ምንነታቸውን ብቻ ጠቁሜ የማልፋቸው ስድስት ጥናቶችን ነው፡፡ ከእነዚህ ተከትለው የመጡ ሁለት ጥናቶችን ግን እጅጉን በመወዳጀታቸው ሒሳዊ ቅኝት አድርጌባቸዋለሁ፡፡

አስቀድሜ የምጠቁማቸው በደራሲው የአጻጻፍ ብልሃት ላይ የተሰሩ ሦስት ጥናቶችን ነው፡፡ እነሱም፤ "ውስጣዊ ግለወግ÷ እንደወረደ እና ሕልም በትረካ ብልሃትነት፤ በ'ኤልዛቤል'" በሚል ርዕስ *ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም አስራ ሁለተኛው አመታዊ ጉባኤ* በቴዎድሮስ ገብሬ 1992 ዓ.ም የቀረበ መጣጥፍ፣ "Narrative techniques of Adam Reta's *Gracha Qachiloch*: Stream of Consciousness in focus" እና "Stream of Consciousness as Reflected in *Adefris* and 'ke' Lijitwa'" በሚሉ ርዕሶች፣ እንደቅደም ተከተላቸው፣ ህይወት ዋለልኝ በ2012 እና እንደሻው ለተራ በ2005 እ.ኤ.አ. ለውጭ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቧቸው ጥናቶች ናቸው፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ የአጭር ልቦለዷን የትረካ ብልሃቶች ከአቀራረባቸውና ከሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳቸው አንጻር የመረመሩ ሲሆን፣ ውስጣዊ ግለወግ፣ እንደወረደና ሕልም የሥነ ልቡና ማዕምራን የሰው ልጅን አዕምሮ አሰራር ለማወቅ እና ኢ-ንቁ ልቡናን ለማጥናት የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች እንደሆኑና በዚች ተረክ ውስጥም በላቀ መልኩ ጥቅም ላይ እንደዋሉ አስረድተዋል፡፡ ህይወት የገለፃ ስልትን በመጠቀም ጥናቷን ያቀረበች ሲሆን በ*William James* የ"እንደወረደ" ምልከታዎች ላይ አተኩራ ንድፈ ሃሳቧን አበጅታለች፡፡ *ግራጫ ቃጭሎች* የ"እንደወረደ" ጽሑፍ ነው ከማለት ይልቅ ደራሲው ብልሃቱን

የፈተነበትና በርካታ የእንደወረደ ገፅታዎችን፣ ለምሳሌ፡- "ውስጣዊ ግለወግ"፣ "ነፃ ቅንጅት"፣ "Authors distance"፣ "simulation through language" እና "Mechanical key words"፣ በአንጼ የተጠቀመበት ነው ማለት ሳይሻል አይቀርም ትላለች፡፡ በብዛት ውስጣዊ ግለወግን የተጠቀመ ቢሆንም ቅሉ ያን ያህል በብልሃቱ የላቀ እንዳልሆነና በአግባቡ ጥቅም ላይ ውሏል ለማለት እንደማትደፍር ገልፃለች፡፡ የእንደሻው ለተራ ጥናት ንፅፅራዊ ገለጻ በማድረግ ከአደፍርስና ከ"ከልጅቷ" የተሻለ "እንደወረደ"ን የተጠቀመ ማን ነው? በሚለው ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የሁለት ደራሲዎችን ስራዎች የተለያዩ ዘውጎች መርጦ በማነጻጸር፣ የ"እንደወረደ" ብልሃት ሚናዊና ወጥ ሆኖ ከአደፍርስ በተሻለ በ"ከልጅቷ" ታሪኩን ያለጣጠቀ እንደሆነ፣ በአደፍርስ ግን እንደ አማራጭ እንጂ በዘለቄታዊነት እንዳልቀረበና ከእንደወረደ ይልቅ፣ "ውስጣዊ ግለወግ" ሚናውን እንደወሰደ ሞግቷል፡፡ በ"ከልጅቷ" ውስጥ ከሚመጡ አንጓማሽ የ"እንደወረደ" ስልቶች ውስጥም "ነፃ ቅንጅት"፣ ሰርካዊ ስርዓትን የሚገዳደሩ የቋንቋ አጠቃቀሞች እና የንቁ ልቡና ሁኔታና ውጭውን ለመገንዘብ የሚደረጉ ግፊቶች አቢዮቹ እንደሆኑ ገልጿል፡፡ በርካታ ማኅበራዊ ጉዳዮችና ጭብጦች በ"እንደወረደ" ብልሃት ታሽተው እንደቀረቡና አብዝቶ በ"ከልጅቷ" ከዘመነኛ እና ፍልስፍናዊ ጭብጦች ጋር ለመወዳጀት ምን ያህል ሚናው የላቀ ብልሃት እንደሆነ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ እንደ ህይወት ሁሉ፣ ብልሃቱ ምንም ጉድለትና እንከን ልናወጣለት የማንችለው ዘመነኛና ወጥ እንደሆነና የሀገራችን ጸሐፍትም ኪናዊ ስራዎቻቸውን ለማቅረብ በራሳቸው መንገድ ቢጠቀሙበት የተሻለ ስራን ሊያስገኝ እንደሚችል በመምከር ሃሳቡን ቋጭቷል፡፡

በመሆኑም የእኔ ጥናት ከሦስቱ ጥናቶች በሚያተኩርበት ርዕሰ ጉዳይም ሆነ በቴክስት ምርጫ፣ እንዲሁም ሊያሳካው ባለው ዓላማ ይለያል፡፡ "እንዴት ቢሉ?" አንድም ይህ ጥናት የ"ልጅነት"ን ጭብጦች በማኅበረ-ልቡናዊና በፍሮይዳዊ የስብዕና መዋቅሮች መነጽር የሚፈልግ እንጂ የትረካ ብልሃቶችን የሚመረምር አይደለምና፡፡ አንድም በቴክስት ምርጫ እና በተጠቀምነው ስልትና ዘዴ እንለያያለን፤ ህይወት ቴክስታዊ የትንተና ዘዴን ከገለጻ ስልት፣ እንደሻው ደግሞ ቴክስታዊ ዘዴን ከንፅፅራዊ ስልት ጋር በማዋሃድ የተጠቀሙ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ "በይነ-ቴክስታዊ" ንባብን ይጠቀማል፡፡ ስለሆነም ጥልቅ ዳሰሳ አላደረኩባቸውም፡፡

ከእኔ ጥናት ጋር በተሻለ የሚቀርበው የማንያዘዋል እንደሻው ጥናት "የአዳም ልጆች ንፅፅር" በሚል ርዕስ በ"ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዜና መጽሔት" ቁ.5 ውስጥ በአራት ገጾች የቀረበ መጣጥፍ ነው፡፡ ማንያዘዋል ለጥናቱ ከመረጣቸው ሶስት አጫጭር ልቦለዶች ("ድብ ድብ"፣ "ማሞ" እና "ሽቦው") ውስጥ "ማሞ" በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተተ በመሆኑና የገፀ- ልጆችን ሥነ ልቡናዊ ሁኔታ ለማሳየት መሞከሩ ከእኔ ጥናት ጋር ያማሳስለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ማንያዘዋል ለጥናቱ ምንም አይነት ሥነ ልቡናዊ የንድፈ ሃሳብ ቅንብብ የተጠቀመ ባለመሆኑና በትንታኔ ማሄጃነት "ንፅፅራዊ ገለጻ"ን መጠቀሙ ከእኔ ጥናት ይለየዋል፡፡ ወዲህ የእኔ ጥናት የልጆቹን ልቡናዊ አቀራረፅ ከተለያዩ ቴክስቶች ፍቺዎችን በማልመድ የሚደረግ ነው፡፡ ወዲህ ልጆቹን በማነጻጸር የሚደረግ ንባብ አይደለም፡፡ ስለሆነም በዘዴ፣ በስልት፣ በቴክስት ምርጫና ርዕሰ ጉዳዮን አስፍቶ በማንበብ ይህ ጥናት እንደሚለይ ልብ ይሏል፡፡

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር በሩቁ የሚጠራራው የአክሊሉ ደሳለኝ ሲሆን "Existentialism in the Selected Creative Works of Adam Reta" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. በ2010 ለውጪ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ ምንም እንኳ የተመረጡ *የማሕሌት*፣ *አለንጋና ምስር* እና *እቴሜቴ ሎሚ ሽታ* ቴክስቶችንና *ግራጫ ቃጭሎችን* ከ"ነገረ-ህላዌ"(Existentialism) አንጻር ቢፈትሽም በጥልቀት አልቃኘሁትም፡፡ "ለምን ቢሉ?" አንድም ይዘነው ከተነሳነው መከራከሪያ እስከ ርዕሰ ጉዳይ አተኩሮ፣ ከዘዴ እስከ ቀነበብነው ንድፈ ሃሳብ ድረስ ልዩነታችን ሰፊ ነውና ነው፡፡ ፍልስፍናና ሥነ ጽሑፍ የጋራችን በሚሏቸው ጉዳዮች ላይ አተኩሮ የተሰራው የእሱ ጥናት ሥነ ጽሑፍና ሥነ ልቡና የጋራችን በሚሏቸው ላይ ከተመሰረተው የእኔ ጥናት ይለያልና ነው፡፡

እንዳለጌታ ከበደ "አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች" በሚል ርዕስ በ2004 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት በከፊል ማሟያነት የሰራው ጥናት ሌላው የሚጠቀስ ነው፡፡ እንዳለጌታ ከ*ማህሌት* "የአበቦች ታሪክ"ን፣ ከ*አለንጋና ምስር* "የድንች መዋስዕት"ን እና የሌሎች ደራስያንን ስራዎች አካቶ የሰውን ልጅ ረቂቅ ባህሪ መሰረት በማድረግ እንደተቀረፁና ሰዋዊ ትዕምርትን ሚናቸው አድርገው፣ አሊጎሪካል የአጻጻፍ ስልትን ተከትለው የቀረቡ እንደሆኑ ተንትኗል፡፡

በመሆኑም ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ተመሳሳይ መድበሎችን በመምረጣችን ብቻ ሲሆን ከመድበሎቹ ውስጥ በመረጥናቸው ቴክስቶችና በተከተልናቸው ንድፈ ሃሳባዊ ቅንብቦች እንዲሁም ዘዴ እንለያያለን፡፡ የሌሎች ደራስያንን የአጫጭር ልቦለድ መድበሎችንም በማካተቱ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ ስለሆነም አላተኮርኩበትም፡፡

በቅርብ የሚዛመዱትና ሒሳዊ ቅኝት ያካሄድኩባቸው የታደሰ ሺበሺ "ሚቶሎጂያዊ ጥናት *እቴሜቴ ሎሚ ሽታ* እና *ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ* በተሰኙ የአዳም ረታ መድበሎች" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በ2005 ዓ.ም. የቀረበ ጥናት እና የቴዎድሮስ ገብሬ "*Mahilet*: A Laboratory of Stylistic Experimentation" መጣጥፍ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች፣ አንድም ፍቺን ከሌላ ቴክስት፣ ሚት፣ ያለመዱ ናቸው፡፡ አንድም በሚታዊ መባያ መር ትንተናቸው የሥነ ልቡና፣ በተለይም የፍካሬ ልቡና፣ የሃሳብ ቅምሮችን ይጠራሉ፡፡ ስለሆነም ሒሳዊ ቅኝቴ አተኩሮባቸዋል፡፡

በ67 ገፆች የተሰናዳው የታደሰ ጥናት፣ በመረጣቸው መድበሎች ውስጥ የተደራጁ ሚቶሎጂያዊ ጉዳዮች ለሥነ ጽሑፋዊ ስራው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መመርመር በአቢይ አላማነት፣ የሚታዊ ጉዳዮችን አቀራረብ፣ የአዳምን ሚቶ ከያኒነት እና የሚያነሳቸውን ጭብጦች መመርመር ደግሞ በንዑስ አላማነት ይዞ የተነሳ ነው፡፡ የምርምር ጥያቄዎችም ከአላማዎች ጋር የተሳሰሩ ሲሆኑ የሚለዩት የመጠይቅ ቃላትና ሥርዓተ ነጥብ በመጠቀማቸው ብቻ ነው፡፡ ጥናቱን ያካኼደበት ዘዴ "ቴክስታዊ ትንተና" ሲሆን፣ ለትንተናው የሚያግዘው ንድፈ ሃሳባዊ ዳራም አበጅቷል፡፡ ስለ ሚት ምንነትና አመጣጥ፣ ስለ በይነ ዲሲፕሊናዊነቱና ስለ ሚቶ ኪን ሰፊ ማብራሪያ ከሰጠ በኋላ የሚትንና የሥነ ጽሑፍን ግንኙነት አስፍሯል፡፡ በሚትም ሆነ በሥነ ጽሑፍ የኢ-ንቁ ልቡና ሁኔታዎች እና ማኅበራዊ ውጉዙነት የሚደርስባቸው በትዕምርት የሚቀመሩ ሃሳቦች ወደ ፍቺዎቻቸው [የምንጠጋው] በጥልቅ ፍካሬና ትርጓሜ እንደሆነም አስረድቷል፡፡ ሚታዊ ቋንቋና ገላጭነቱ (ከሰው ልጅ ምናብ የሚረቁና የሚጸኑ እሳቤዎችንና ክስተቶችን በሰርካዊ ልማድ የመቀየር አቅም እንዳለው፣ ደራሲዎች ያሻቸውን መናገር እንደሚያስችላቸው)፣ ሳታየር፣ አስተኔ ደራሲ፣ ሚስጢራዊ የቋንቋ

አጠቃቀም፣ ትንቢት፣ ርዕይ፣ ህልም፣ አስማት፣ "አርኬታይፕ" የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦችን በንድፈ ሃሳባዊ ቅንብቡ ተመልክቷል፡፡

የታደሰ ትንተና በሦስት አቢይ ጉዳዮች ላይ ያረፈ ነው፡፡ የመጀመሪያው የ"ተቃራኒዎች መቃለጥ" ነው፡፡ አዳም ሰርካዊ የሆነውን የሚት ትልም ማዋቀሪያ፣ የተቃራኒ ስሜቶችን መዋሃድ፣ ለሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎቹ የትልም ማዋቀሪያነት እንደሚገለገልባቸው አሳይቷል፡፡ "አሞራ፣ እንደልዕለ ሰብዕ ተራዳኢ" በሚለው የትንታኔ ክፍሉ፣ በተለይም *ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ*፣ "አሞራ" ለዘመናዊ ሥነ ልቡና ተጋዳሊ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት እንደሆነና አሮጌውን "ኑረት" በመናቅ ወደ አዲስ ህይወት እንዲሸጋገሩ እንደሚያደርግ ተንትኗል፡፡ በመጨረሻው የትንተናው ክፍል "ሚታዊ ጉዳዮች በልጆች ጨዋታ" የሚል ርዕስ አበጅቶ "እቴሜቴ የሎሚ ሽታ" የሚለው የልጅነት ጨዋታ *እቴሜቴ ሎሚ ሽታ* የተሰኘውን መድበል እንዴት እንዳዋቀረ ተመልክቶበታል፡፡

በማጠቃለያው፣ አዳም፣ ለሥነ ጽሑፋዊ ስራዎቹ ማደራጃ ሚቶሎጂን እንደሚጠቀም፣ ሚታዊ ቋንቋን፣ ምናባዊ ደራሲና ምትሃት የአጻጻፍ ብልሃቶችን ለሃሳቡ ማሄጃነት እንደሚገለገልባቸውና ሚታዊ ትዕምርትን ለሥነ ጽሑፋዊ መዋቅርና ጭብጥ ማበልጸጊያነት እንደሚያውላቸው አሳይቷል፡፡ የቀደሙ ሚቶችን ዳግም ልደት እያጎናፀፈና እያዘመነ የሚጽፍና በአዲስ ንጽረት ለአንባቢያን እንካችሁ የሚል በመሆኑ ሚቶ ከያኒ እንዲሆን አስችሎታልም ይላል፡፡ እንደ ወሲብ እና ጾታ ያሉ ጉዳዮች ተደጋግመው የሚመጡ በመሆናቸው ከ"ነገረ ወሲብ" እና "ነገረ ፆታ" አንጻር ቢጠኑ መልካም እንደሆነም ጠቁሟል፡፡

በዚህ ጥናት ርዕሱ ከዓላማው፣ ሁለቱም ደግሞ ከዘዴውና ንድፈ ሃሳባዊ ቅንብቡ ጋር የ"ሰሉ" ናቸው፡፡ በተለይም የተገለገለበት ዘዴ ማንበቢያ ጉዳዮችን ከቴክስቱ እንዲመዝ የሚመክር በመሆኑና ይህን በማድረጉ ጥናቱን ጥብቅ አድርጎታል፡፡ ሚታዊ ጭብጦችንና አቀራረባቸውን ከውስጣቸው ጠልቆ ለመመርመርም ሚትና ሥነ ጽሑፍ የጋራችን በሚሏቸው ጉዳዮች ላይ ተመስርቶና ሚትን ከሥነ ልቡና ጋር እያወዳጀ፣ በተለይም የገፀ ባህሪያቱን ወቅታዊ ስሜትና ሥነ ልቡናዊ ማንነት በመመርመር ትንተናውን አድርጓል፡፡ ወዲህ አላማዎቹ በሙሉ መሳካታቸውና ከማጠቃለያው ጋር መስመራቸው፣ ወዲህ ደግሞ ቴክስቶቹ ለሌሎች ጥናቶች ክፍት የሆኑባቸውን (የሚጠሯቸውን)

የዕውቀት መስኮች ("ነገረ ወሲብ" እና "ነገረ ፆታ") መጠቆሙ አሁንም ጥንካሬዎቹ ናቸው፡፡ በጥቅሉ፣ ወዲህ የቋንቋ አጠቃቀሙ፣ ከቀደምት ጥናቶች ላይ መመስረቱ እና ከእሱ የሚለዩበትን ድንበር መዘርጋቱ፣ በንድፈ ሃሳባዊ ቅንብቡ ውስጥ ለመጡ ጽንሰ ሃሳቦች ግልፅ ማብራሪያ መስጠቱ፣ ወዲህ የዓላማ፣ የምርምር ጥያቄ፣ የዘዴ፣ የጭብጥና የማጠቃለያ ውህደት ገዝፎ መታየቱ የጥናቱ ጥንካሬ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እንከኖችም አልጠፉም፡፡ በጥልቀት ከዳሰሳቸው ስራዎች ውስጥ የአክሊሉ ዘዴ ምን እንደሆነ አለመጠቆሙ እና የአዳምን ሚቶ ከያኒነት ለመመርመር በአላማውና በምርምር ጥያቄዎቹ አካቶ በግኝቱም ማረጋገጡ የአዲስነት (Orginality) ጥያቄ የሚያጭር መሆኑ ("ለምን ቢሉ?" አስቀድሞ ቴዎድሮስ ገብሬ በ"*Mahilet*: A Laboratory of Stylistic Experimentation" በተሰኘ ጥናታቸው የደራሲውን ሚቶ ከያኒነት በመጠቆማቸው ነው) እንደ ችግር የተመለከትኳቸው ናቸው፡፡

የታደሰ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚወዳጀው የአንድ ደራሲ ተመሳሳይ ዘውግ ስራዎችን በመምረጣችን (መድበል አላልኩም) እና ትዕምርታዊ ጉዳዮችን እንደ ሥነ ልቡናዊ ማንነት መፈከሪያ መገልገላችን ነው፡፡ በትንታኔው የ"አሞራ" መገለጥና መለየት ከኢ-ንቁ ልቡና ወደ ንቁ ልቡና መሸጋገርን ለመፈከር ሲጠቀምበት እኔ ግን በንቃተ ልቡና ውስጥ ያለን ሽግግር ለማሳየት ነው የተገለገልኩበት፤ ከአንድ ማኅበረ-ልቡናዊ ማንነት ወደ ሌላ ማኅበረ-ልቡናዊ ማንነት መሸ ጋገርን፡፡ ፍቺ ለመፈለግ በሌሎች ቴክስቶች ላይ መባዘንን የግብር ባህሪው ያደረገውን ዘዴ (በይነ-ቴክስታዊን) በመጠቀሜና ዋና መዳረሻየንም የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ሚቶሎጂንና ሌሎች "ተስማሚ" የክርስቲያን ቴክስቶችን፣ በደጋፊነት ደግሞ የግሪክና የአፍሪካ ሚቶሎጂን በመጠቀሜ ጥናታችን ይለያያል፡፡ በአላማ፣ ይዘነው በተነሳነው የመሞገቻ ሃሳብ እና ንድፈ ሃሳባዊ ቅንብብ አንጽሮታችን ለየቅል ነው፡፡ በ"እኛ ቤት" ሲለምድ ያላስተዋልኩትን የኤሪክሰን ማኅበረ-ልቡናዊ ዕድገትም ለጥናቱ በሚስማማ መልኩ ማልመዴ ከእዚህ ጥናት ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ጋርም እንዲለይ አድርጎታል፡፡ የእሱ ሥነ ልቡናዊ እይታ ዋና አላማው ሳይሆን በተጓዳኝነት የጠራው ነው፡፡ ፍካሬያችንን በምናሄድባቸው መድበሎችም እንለያያለን፡፡

በመጨረሻ የምቃኘው፣ የቴዎድሮስ ገብሬን "*Mahilet*: A Laboratory of Stylistic Experimentation" የተሰኘ መጣጥፍ ነው፡፡ ይህ መጣጥፍ በ2013 እ.ኤ.አ. *Reading Contemporary African Literature: Critical Perspectives* በሚል ስብስብ ውስጥ የታተመ ነው፡፡ በመጣጥፉ ውስጥ ቴዎድሮስ የተመለከቷቸው "ግልገል ብላሽ"፣ "ማሕሌት"፣ "ሳምራዊው" እና "ኤልዛቤል" የተሰኙትን አጫጭር ልቦለዶች ነው፡፡

አዳም በስራዎቹ የሰው ልጅ ማንነቶችን፣ ሁኔታዎችንና "መደናገሮችን" የሚጠሩ ጭብጦችን፣ እንደ ብቸኝነት፣ መነጠል፣ የሰብዓዊነት "መንጠፍ" እና የሰብዕና "አለመዋሃድን" የሚቀምር ጸሐፊ እንደሆነ፣ የሚስላቸው ገፀ-ባህሪያትም ብዙ ጊዜ ራሳቸውን መሆን ያቃታቸው (ለራሳቸው ባይተዋር የሆኑ)፣ ቤተሰባቸውንና ልማዳዊ ማንነታቸውን ያጡ እንደሆኑና "ጊዜ-ስፍራ-አዕምሮ" በአዲስና ፈጠራዊ በሆነ የአገላለፅ ቅጥ እንደሚቀርቡባቸው ያስረዳሉ፡፡ ከፍ ብዬ በጠቀስኳቸው የጥናቱ ታላሚ ቴክስቶች በአይነታቸው የበዙ ስልቶች፣ እንደ ተራኪ የመብዛት፣ የታሪኮች ካሉበት ያለመቀጠልና የዓረፍተ ነገሮች መበጣጠስ፣ የታሪክ መዋቅር "መዘበራረቅ" የተለመደውን የአማርኛ ኪን በአተራረክ የተጋፈጡ ናቸው ይላሉ፡፡ የቃላት አለቦታቸው መግባት ፣ ዘይቤዎች ባልተለመደ ቅጥ መምጣታቸው፣ ቅፅበታዊና የማይቀጥል ወግና የተበጣጠሱ ምልልሶች መዋቀራቸው እንዲሁም ያልተለመዱ እንደ ስዕል (chart) ያሉ ኪኖች የለመዱባቸው በመሆናቸው አዲስ ስልትን ይዘው የመጡ ናቸው ብለው ይሞግታሉ፤ በተለይም "ማሕሌትን"ና "ሳምራዊው"ን ለዚህ ማሳያነት ይጠቅሳሉ፡፡ ከተለምዷዊ ውጭ የሆኑ ምሰላዎችና ዘይቤዎች ላቅ ያሉ የደራሲው ኪናዊ አጠቃቀሞች እንደሆኑና የአንባቢውን አስተሳሰብ የተፈታተነበትና "አሳታፊ-ንባብ" (Participatory Reading) እንዲኖር ያደረገበት እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ወዲህ ሚታዊ ጉዳዮች የተራኪውን ጉዞ እያበጁ ታሪኩን እንደሚያደራጁ እና የጊዜና የቦታ አዛማጅ (የመቼት ቅንብብ) ሆነው እንደሚያገለግሉ፣ ወዲህ እንደ "ኤልዛቤል"ና "ሳምራዊው" ያሉት ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱና ተመሳሳይ ሰብዕና የተሳለባቸው እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ በተለይ "ማሕሌት" በሚታዊነቷ የላቀችና በዘመነኛ ኪን ሰርካዊ የሆነውን በፈጠራዊ ሚት (Mythopoeia) ስራን የማዋቀር ስልት የበለፀገች እንደሆነች ሞግተዋል፡፡ በ"ማሕሌት" ዋና ጉዳዩ ስዕል ቢሆንም፣ "ሥነ ጽሑፍ-ስዕል-ሙዚቃ"

የተዋሃዱበትና ከቃሉ አመራረጥ (“ማሕሌት”) ጀምሮ ይህን ታሳቢ እንዳደረገና የ“ኪን” ሌላ ስም እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

እስጢፋኖስ የማሕሌትን ኢ-ንቁ ልቡናዊና የጠለቁ ሚስጢሮቿን ተገንዝቦ እንደሚስላት ጠቁመው፣ የቴክስቱ ሚስጢርም ያለው የማሕሌት ሚስጢሮች ለእስጢፋኖስ መገለጣቸው ላይ እንደሆነ መርምረዋል፡፡ ይህ መገለጥ ሚታዊ እንደሆነ፣ ወዲህ በሐዲስ ኪዳን ሚታዊው ተጋዳሊ እስጢፋኖስ የሰማያት በሮች ተነቅለውለት ሚስጥራትን እንዳየ፣ ወዲህ ደግሞ በማሕሌት ልብ ውስጥ ተገዞ ሚስጢራዊ ማንነቷ ይገለጥለታል፤ ይህ ደግሞ በኪናዊ አዕምሮው ውስጥ የኪንን ሚስጢራዊነት መገለጥ እንዳስተማሰለ ይሞግታሉ፡፡ ወዲህ የማሕሌት ከልማዳዊው ወደ ዘመናዊው ቅጥ መቀየር የእስጢፋኖስን የኪን ፍልስፍና፣ ወዲህ የማሕሌትና የእስጢፋኖስ ግጭት በልማዳዊውና በዘመናዊው የኪን ስልት መካከል ያለውን ግብግብ እንደሚያሳይና የማሕሌት አሸናፊነት “ኪን” ከያኒውን እንደምትመራው የሚያሳይ ነው ይላሉ፡፡ ወዲህ  ይህ ግብግብ የርዕዮተ ዓለም ጣጣ እደሆነና ከልማዳዊው ወደ ዘመናዊው ኪናዊ ርዕዮት መሸጋገርን እንደሚጠራ ይሞግታሉ፡፡

ቴዎድሮስ በመጣጥፋቸው ጽንሰ ሃሳቦችን ከትንተና ጋር በማዋሃድ፣ የቴክስቶቹን መዋቅርና አደረጃጀት ደግሞ ሚታዊ ጉዳዮችን ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥራት ተርጉመዋል፡፡

የእኔና የቴዎድሮስ ጥናት ሚታዊ ጉዳዮችን እንደመባያ በማዋል፣ የደራሲውን ተመሳሳይ መድበል በመጠቀምና በአተናተን ዘዴ (“በይነ-ቴክስታዊ”ና ፍካሬ) ይመሳሰላሉ፡፡ በንድፈ ሃሳባዊ አተኩሮ፣ በቴክስት ምርጫና በርዕሰ ጉዳይ ደግሞ እንለያያለን፡፡

በመሆኑም፣ እነዚህ ክፍተቶችና ሌሎች ጉዳዮች ይህን ጥናት ለማከናወን እንደ መነሻ ሆነው አገልግለውኛል፤ ርዕሱንም አሁን ባለበት መልኩ ለመቅረፅ አስችለውኛል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# "ልጅነት" በማሕሌት እና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ

## 3.1. "ልጅነት" በማሕሌት፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ

የ"ልጅነት" ጉዳዮች አጥብቀው ከሚነሱባቸው አጫጭር ልቦለዶች ውስጥ "ማሞ" እና "ስለ ድልድዩ ልጅ ትዝታ" ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በቴክስቶቹ ውስጥ የልጆች ማኅበረ-ልቡናዊ ማንነት፣ "ልጅ" የመሆን ቀውሶችና የአሳዳጊ (የወላጅ) ሚና በርዕሰ ጉዳይነት፣ የተለያዩ የማኅበረ-ልቡናዊ ዕድገት ደረጃዎች እሳቤዎች በጭብጥነት እና የባህልና ሚታዊ አስተማስሎዎች በጭብጥ ማበልፀጊያነት ተዋቅረዋል፡፡ በሁለቱ ቴክስቶች ውስጥ የምናስተውላቸው የልጅነት የሰብዕና እስቦች፣ በአሳዳጊዎቻቸው የተለያዩ የአስተዳደግ ዘይቤዎች ምክንያት በሁለት ጽንፎች የቆሙ ናቸው፡፡ ስለሆነም ሁለቱን ቴክስቶች "ጨፍልቆ" ከማየት ይልቅ ለየብቻ መፈተሹ ተገቢነት አለው፡፡

### 3.1.1. "ማሞ"፤ ማኅበረ ልቡናዊ ማንነትና የአሳዳጊዎች ሚና

በዚህ አጭር ልቦለድ አምስት ገፀ ባህሪያት ያሉ ሲሆን ታሪኩ ግን በዋናነት የምናሴ ነው፡፡ ምናሴ የአስራ አንድ አመት ልጅ ነው፡፡ የምናሴ ታሪክ በ"ተለመደው" የአማርኛ አጫጭር ልቦለዶች የአጻጻፍ ብልሃት የማይሄድ፣ በድንገት ከነበረበት የማይለጥቅና አንባቢን ቆም ብሎ እንዲያሰላስል የሚጋብዝ ነው፡፡ በ"ተለመደው" አተራረክ መጨረሻ ላይ እናገኘዋለን ብለን የጠበቅነውን የታሪኩ ክፍል መሃል ላይ ልናገኘው እንችላለን፡፡ አንባቢም ታሪኩን በራሱ እየሰራ እንዲገነዘብ ይገደዳል፡፡

የምናሴን ማኅበረ ልቡናዊ ማንነት ስንመረምር የምናገኘው በፍርሃት፣ በመጠራጠር፣ "እኔ ከንቱ ነኝ" በሚል ስሜት፣ በራስ ባለመተማመን እና ነገሮችንና ክስተቶችን በጥቅል "መፈረጅ" የተገነባን ሰብዕና ነው፡፡ ይህን ማንነቱን ለማንበብ ሁለት ጉዳዮችን እናነሳለን፡፡ እነሱም፤ የአሳዳጊዎቹን ማንነትና ያስከተለውን ሰብዕና እና ሰብዕናዊ ማንነቱን ለማሳየት የዋሉና ትንተናውን ፈር የሚያሲዙ፣ የጭብጥ ፍቺዎችን የተሸከሙ፣ ባህላዊና ሚታዊ አስተማስሎዎች ናቸው፡፡

### *ሀ. የአሳዳጊዎች ማንነት እንደ የ"ልጅነት" መገንቢያ*

ምናሴ በሁለት ማንነቶች ያለፈ ገጸ-ልጅ ነው፡፡ የመጀመሪያው አስቀድሞ (በትውስታ ከሚያስገባቸው የታሪኩ ክፍሎች) ከእናቱ ጋር የነበረው ሰብዕና ነው፡፡ ከአንድ አመት በኋላ እናቱ በካንሰር በመሞቷ ምክንያት በእንጀራ እናቱ የአስተዳግ ዘይቤ ደግሞ ሌላ ሰብዕናን ያዳብራል፡፡ "እናት" የወለደች ሴት ከወለደችው ጋር ባላት የተዛምዶ ግንኙነት የምትጠራበት ቃል፣ የመሪነት፣ የአሳዳሪነት፣ የሞግዚትነት፣ የደግነት፣ የሩህሩህነትና የፍቅር ተምሳሌት ናት (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣1948፣225 እና የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር መዝገበ ቃላት፣1993፣325)፡፡ እናት ልጇ በሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ፍቅርን፣ ርህራሄን፣ የማስተካከያ እርምቶችን በደግነትና በምክር የምትሰጥ ፍጡር ናት፡፡ ማኅበረሰቡም "እናት የሌለው ተንዳጅ እርሻ የሌለው ጠላ ወዳጅ" የሚል ብሂል አለው፡፡ አንድም መመኪያ ሳይኖር፣ አንድም ስራ ሳይሰራ የሚፈልጉትን ነገር ማግኘት አይቻልም ሲል ነው፡፡

ምናሴ እንዲህ አይነት እናት ነበረችው፡፡ የእሱን "መልካምነት"ና የወደፊት ብሩኅ ተስፋ የምትናፍቅና የምትመኝ ብሎም የምታበረታታ እናት፡፡

> "ይኸው !"
>
> "ምኑ?" ከእጁ ቀልባ፡፡
>
> አልጋ ላይ ወጥቶ በፍስሐ ተንከባለለ፣ በደረቱ ተኝቶ ወደ እርስዋ እያየ፡፡
>
> "ወደ ሶስተኛ ክፍል አለፍኩ" አላት፡፡
>
> "አትስመኝም እንዴ?"
>
> እንደዚያ ቀን ስትስቅ አላያትም…… የምትስቅ እናት…… ከአንድ አመት በኋላ በልብ ድካም ሞተች፡፡ ትንሽ፣ ትንሽ እንደ ሕልም ትዝ ይለዋል…… እናቱን በደንብ አያውቃትም፤ ግን ልጅዋ ሲያሸንፍ በደስታ የምትፍነከነክ እናት፡፡
>
> "ቢያድግ ልጄ ዶፍተር ይሆናል" ትል ነበር እናቱ፤ ፈገግታዋን እንደ ሕልም ትንሽ ትንሽ ያስታውሳል (*ማሕሌት*፣1981፣101)፡፡

ምናሴ አስቀድሞ በእናቱ ሲያድግ ለሚያደርገው ነገር ይሁንታ ይሰጠው ነበር፡፡ ልጇ ሲያሸንፍ "እሰየው" የምትለው፣ የምታበረታታው፣ ሌላ ተስፋንና መሆን ያለበትን

በፍቅር የምትነግረው ነበረች። በዚህም ምናሴ ያዳበረው ሰብዕና በራስ መተማመንና ለሌላ ስራ መትጋትን ነው። ይህ ሰብዕና አሁን ታሪክ ብቻ ሆኗል። አሁን አሳዳጊው የእንጀራ እናቱ ናት። የእንጀራ እናት ደግሞ ከተጠቀሱት አባባሎች በተቃራኒ የምትገለጽ አሳዳጊ ናት። የምናሴ የእንጀራ እናትም ከእዚህ ማኅበራዊ እውነታ የራቀች አይደለችም። በእንጀራ እናቱ የአስተዳደግ ዘይቤና የግል ባህሪ ምናሴ ፈሪ፣ ተጠራጣሪ፣ በራሱ የማይተማመን፣ ትጋትና ወኔ የሌለው ሆኗል። ከመሰሎቹ ጋር እንዲጫዎት የማይፈቀድለት፣ በእንጀራ እናቱ ታዝዞ በሚሰራው ስራ ይሁንታን የማይቸረው ልጅ ነው። በዚህ "አፍራሽ" ምላሽ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን የማይወጣ፣ ከአቻዎቹ የሚያንስ አድርጎ ራሱን የሚያስብ፣ በራሱ የማይተማመንና ተጠራጣሪ ሆኗል። ጥሩም ይሁን መጥፎ በእያንዳንዱ ሥራው ፍርሃትን የሚሰንቅ ሆኗል።

> "ለቡና ማፍያ ይህችን ይዘህ ካልመጣህ ነገርኩህ! ወጥህን ማሞቅ፣ ወጥህን መስራት ተለማመድ፤ ላንተ ማን ይጨማለቃል?....። በደንብ ለቅመህ ይዘህ ና አለበለዚያ እራትህን አታገኛትም።" (96)

ምናሴ "አፍራሽ" ምላሽ የሚሰጠው ከስራው መልስ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም በትዕዛዙ ውስጥ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ የተጨመረበት ነው። ይዞት እንዲመጣ የታዘዘውን እንጨት ሲለቅም እንኳ ይህ ማስጠንቀቂያ ልቡናውን ያውከዋል፤ ይህን እያሰላሰለ በነፃነት አይሰራም።

> ዋናው ነገር ግን፣ የሰበሰባትን እንጨት ቶሎ ቶሎ አስሮ መሄድ ነው። አልያ ራት የለም። አልያ ቁጣና እሳት ነው። (101)

የምግብ ቅጣት፣ ድብድባና ፊት መነሳት የአሁኑ የልጅነት ህይወቱ መገለጫዎቹ ሆነዋል። ይህ የተስፋ ማጣት ሰብዕና መዳበርና በራስና በከባቢው አለመተማመን ካስከተለበት ልቡናዊ ቀውስ ውስጥ እስቦችንና ሁነቶችን ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ በ"ጥቅል መፈረጅ" ነው። እንጀራ እናቱን ከሚፈራባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንደኛው ጥርሰ ፍንጭት በመሆኗ ነው፤

> ፍንጭት ጥርስ ይፈራል፤ እንጀራ እናቱ ፍንጭት ጥርስ አላት። (101)

ለምን ጥርሰ ፍንጭት ይፈራል? ብለን ስንጠይቅ በቀጥታ መልስ አናገኝም፡፡ ይልቁንም ታሪኩን በርጋታ ስናጤን የእንጀራ እናቱ የፍርኃት ተምሳሌት ትሆናለች፡፡ በዚህም ጥርሰ-ፍንጭቶችን ሁሉ ሲፈራ እንመለከታለን፤

> የፊት ጥርሷ የወለቀ ሒሩትን ሲያያት ፍንጭት መስላው ፈርቶአት ነበር፡፡ አዲስ ጥርስ ማብቀል ስትጀምር ተጠጋት፡፡ (102)

እነዚህ ጥቅል ፍረጃዎች ነገሮችን አመዛዝኖ የመመልከት አቅምን የሚያዳክሙ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የእንጀራ እናቱ ከማኅበራዊ እሴቶች ያፈነገጠች ናት፡፡ ይህን ማኅበራዊ "ፈንጋጭነቷን" ከሚያጸድቁ ምክንያቶች መካከል አባቱ ለንግድ በሄደበት ቅፅበት "ውሽማ" መያዟ ነው፡፡ ይህ ድርጊት ከማኅበረሰቡ መለየትን የሚያስከትልና የማኅበራዊነት መላሸቅን የሚያመለክት ነው፡፡ የእሷ ሰብዕና መላሸቅ ለእሱ ሰብዕና መፍረስ የራሱ ድርሻ እንደሚኖረው ልብ ይሏል፡፡ የእሷ ሰብዕና በሚከተለው መንገድ ተመስሎ እናገኘዋለን፡፡

> ፀሐይም÷አርጋው በማታውቀው ፍጥነት÷ ቁልቁል እየተምዘገዘገች÷ መንደራቸውን ምሽት ጭር እያደረጋት ነው፡፡ (98)

ይህን አስረጅ ልብ ብለን ብንመለከተው የእንጀራ እናቱን ከባህሉና ከማኅበራዊ ስራቱ የ"መውደቅ" ሚስጢር የሚመስል ነው፡፡ በተፈጥሯዊ ስርዓቷ ተለዋዋጭ ባህሪ የሌለባት "ፀሐይ" ተለውጣ አዲስ ሰዋዊ ባህሪን ተላብሳለች፡፡ የፀሐይ የማይለወጥ ባህሪ የባህሉና የማኅበራዊ ስራቱ ጽኑነት ተምሳሌት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የፀሐይ መለወጥና ከተፈጥሯዊ ባህሪ መውደቅ የእንጀራ እናቱ ከማኅበራዊነት መውደቅን ያስተማስላል፡፡ የእንጀራ እናቱ ከማኅበራዊነት የወደቀችው "ዘማዊ" በመሆኗ ነው፡፡ ባሏ ወደ ሩቅ ሀገር ለንግድ በሄደበት ወቅት ፍትወታዊ ፍላጎቷን ለማርካት ወንድወሰን የተባለ ውሽማ ትይዛለች፡፡ ከአንድ በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር ፍትወት መፈፀም (ዘማዊነት) ደግሞ በባህሉ የተወገዘ ነው፡፡

ማኅበራዊነትን አጽንቶ ማቆየት በሚሳናቸው ቤተሰቦች ማደግ የሚያሳድረው ተፅዕኖ "አፍራሽ" እንደሆነ በንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ውስጥ ተመልክተናል፡፡ ምናሴ በእንደዚህ አይነት ሁነት ውስጥ ያደገ ነው፡፡ ስለሆነም ማኅበራዊ ኃላፊነትን መሸከም የማይችልና ማኅበራዊ ስራቱን የመጠበቅ ግብረ ገብ  የሌለው ሆኖ ተስሏል፡፡

በሌላ በኩል የ"ፀሐይ መግባት" ቆየት ብዬ በአስተማስሎ ምልከታዬ እንደማነሳው የ"መጥፎ ዕድል" ትዕምርት ነው፡፡ እነዚህን ሰብዕናዎች በሚታዊና ባህላዊ መባያዎች እንደሚከተለው "ማሰር" ይቻላል፡፡

### ለ. ሚታዊና ባህላዊ አስተማስሎዎች እንደ ሰብዕና መፈከሪያ

በዋናነት የምናሴን ሰብዕና ለመመርመር የሚያስችሉና የእስካሁኑን ሐተታ የሚያስሩ የታሪኩ ውቅሮች ባህላዊና ሚታዊ አስተማስሎዎች ናቸው፡፡ በአቢይነት የሚከተሉትን አስተማስሎዎች ሳነሳ ጊዜ-እናት እና ድህረ-እናት (ጊዜ-የእንጀራ እናት) ልቡናዊ ማንነቶችን የሚያሳዩ በመሆናቸው ነው፡፡

የመጀመሪያው የሰብዕና መፈከሪያ አስተማስሎ በጥንድ ተቃርኖ (binary oppositions) ላይ የተመሰረተ ነው፤ "ነጭ/ጥቁር"፡፡ በመጀመሪያው ጥንድ የመጡት በሰማይ ላይ ጨለማውን ለመሸሸ ወደ ማደሪያቸው በነፃነት የሚበሩ "አሞራዎች" ናቸው፡፡ እነዚህ አሞራዎች ነጫጮች ናቸው፡፡

> ከዛፎቹ ከፍ ብሎ ብዙ ነጫጭ አሞራዎች ወደ ደቡብ ሲወርዱ ተመልክቶ እንጨት መልቀሙን አቆመ፡፡ ነጫጭ ላባዎቻቸው በምትጠልቅ የፀሐይ ጨረር ቅልት ብለዋል፤ በሰልፍ ሆነው ክንፋቸውን ሲያራግፉ ያምራሉ፡፡ (*ማሕሌት*፣99)

በዚህ አስረጅ ውስጥ "ወፎች"[5]፣ "ነጭ" እና የ"ፀሐይ መጥለቅ" የጊዜ-እናትና ድህረ-እናት ሰብዕናዎች የተገነቡባቸው ባህላዊነት እና ሚታዊነት ያላቸው ማስተማሰያዎች ናቸው፡፡ ጉዳያቸው ሚታዊነታቸው አሊያም ደግሞ ባህላዊነታቸው ሳይሆን የልጅነት ሰብዕናን በረቀቀ መልኩ፣ ጭብጥነቱን ማሳየት ነው፡፡ "ወፎች" በአፍሪካ፣ በግሪክ፣ በሮማን እና በክርስቲያን ሚቶች ተደጋግመው ተጠቅሰዋል፡፡ በሚታዊነታቸው የአማልክት ምሳሌዎች፣ የመላዕክቱ መገለጫዎች ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ በኦዲሴ አቴና በጥንብ አንሳና በ"ስዋሎው" ተሰውራ ተገልጣለች፡፡ የወፎች መነብኘት የሙታን መናፍስት እንደመገለጥ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በግዞት ያለ ሰውንም ያስተመስላሉ፡፡ የፍቅር ተምሳሌት ሆነውማል፡፡ ለዚህም የፍቅር አማልክት፤ የሶሪያዋ አስትራቴ፣ የባቢሎኗ አስቴር(*Ishtar*)፣ የግሪኳ አፍሮዳይትና የሮማዋ ቬኑስ አፍቃሬ-ርግብ በመሆናቸው

---

[5] ቀጥሎ በመጣው የታሪኩ ክፍል አሞራዎችን ወፎች እያለ ደጋግሞ ስለተጠቀመ ነው (ገጽ 99፣ 100)፡፡

እናስታውሳቸዋለን (Ferber,2007፡26,61-62)፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርግብ አምሳል ሆኖ በኢየሱስ ላይ አርፏል (ማቴ 3÷16)፡፡ የኢትዮጵያ [ኦሮሞዎች] ፈጣሪ፣"ዋቃ"፣ ሰዎች ሚኞች እንደሆኑ እንዲነግሩ ወፎችን ይልካል፡፡ በካምባ ኬንያዎችም የሞትን "ጸናንነት" እንዲነግሩ ይላካሉ፡፡ በጥቅሉ፣ በአናንግ ናይጄሪያውን፣ በዞሳ ደቡብ አፍሪካውያንና በኮንጎዎች ዘንድ በሰማያውያንና በምድራውያን መካከል ያሉ መላዕክት ተደርገው ይታሰባሉ (Lynch,2004፡18-19)፡፡ ስለሆነም ወፎች አንድም በዘላለማዊ መናፍስት ማደሪያነታቸው የመልካምነት ተምሳሌቶች፣ አንድም ደግሞ የወፎቹ ተገልጦ መለየት የግዞት እና የሙታን መናፍስት፣ አንድም መገለጣቸው የብሩኅ ተስፋና ጤናማነት ተምሳሌት ነው፡፡ እነዚህ ወፎች ደግሞ ነጫጮች ናቸው፡፡

"ነጭ"ም የራሱን ትዕምርታዊ ፍቺ ይዞ የገባ ነው፡፡ በጥንት ሮማውያን የቄሳር አገልጋዮች ለታማኝነታቸው ምልክት ይሆናቸው ዘንድ ነጭ ይለብሱ ነበር (Ferber፣234)፡፡ በክርስቲያን ሚት አገልጋዮችና መላዕክት ደስታን ለመግለፅ ነጭ ይለብሳሉ (ራዕይ 4÷4፣ ዮሐንስ 20÷12፣ መክብብ 9÷8)፡፡ ዙፋኑና የዙፋኑ ባለቤትም ነጭ ነው (ራዕይ 20÷11፣ መኃ 5÷10)፡፡ የጽድቅና የብቃት ምሳሌም ነው (ዳዊት 37÷6፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 5÷5)፡፡ በአብዛኛው የሰሜኑ የሀገራችን ክፍልም የደስታና መልካም ክስተት ተምሳሌት ነው፡፡ ለዚህም ነው በክብረ በዓላትና ደስታን በጠሩ አጋጣሚዎች አበውና "እመው" ነጭ የሚለብሱት፡፡ እነዚህ ሚታዊ መባያዎች በታሪኩ ውስጥ የጊዜ-እናት ሰብዕናን እና ማንነትን የሚያስተማስሉ ናቸው፡፡ የብሩኅ ተስፋ፣ የታማኝነት፣ የኃላፊነት ስሜት ሰብዕናው መባያዎች ናቸው፡፡ የተረጋጋ መንፈስና የትጋት ባለቤትነቱን አስታዋሾች ናቸው፡፡ ከማኅበራዊ እኩይ ማንነቶች፣ ከጥላቻና ከበቀል ርቆ በፍቅር የተገነባ ማንነቱን ልብ ይሏል፡፡ የእነዚህ ነጫጭ ወፎች ቆይታ ግን አጭር ነው፡፡ ወደየጎጆወቻቸው እየበረሩ ስለነበር ወዲያው ይለዩታል፡፡ ይህም፣ አንድም የወፎች መለየት ከ"አሮጌው" ወቅት ጋር ይዛመዳል (Ferber፣209-11)፡፡ የወፎች መገለጥ የአዲስ አመት መጀመሪያንና የፍቅር ወቅትን ይጠራል (213፣ መኃልየ 2÷11-12)፡፡ አንድም አዲስ አመትና "ልደት" በፀሐይ መውጣት፣ የአመቱ ማርጀት እና "ሞት" በፀሐይ መጥለቅ ይመሰላሉ፤ ቀን ማለት ህይወት፣ እያንዳንዱ ቀን የሚጠናቀቀው ደግሞ በእንቅልፍ ነውና (Ferber፣209-11፣ ሉቃ 23÷44)፡፡ የፀሐይ መጥለቅና የወፎች መለየት የምናሴን ያለፈው ብሩኅነትና በራስ የመተማመን ስሜት አለመቀጠልና የቀጣይ

"ዕጣ ፈንታ" ጥሩ አለመሆንን እና "ግዞት"ን ይጠቁማሉ፡፡ ወዲህ ምናሴ በእንጀራ እናቱ ያዳበራቸው እነዚህ ሰብዕናዎች ተከታታይ በሆነው የማኅበረ ልቡናዊ ዕድገቱ ቀጣይ የሚኖረው ሰብዕና ማኅበራዊ ኃላፊነትን መወጣት የማይችል እንደሚሆንና ብቸኝነትን እንደሚያዳብር፣ ወዲህ ደግሞ በእናቱ ህልው የሆነው ማንነቱ ብዙም ሳይቆይ ወደ ተስፋ ቢስነት መቀየሩ ከነጫጭ ወፎች ቀጥለው፣ ወዲያው፣ የመጡት የቁራ አሞራ ሰልፈኞች መስለውታል፡፡

> <u>ባለፉት ነጫጭ ወፎች ፋንታ የሚያንቋርሩ ቁራዎች ወደ አንድ ግዙፍ ግራር በኩል ልቦናውን ሳቡት</u>፡፡ <u>በሰማይ ላይ ጥቋቁር መስቀል</u> መስለው እየበረሩ በጫካው ከፍታ ተዋጡ (*ማሕሌት*፣100)፡፡ [አጽንኦቱ የእኔ ነው]

በነጫጭ ወፎች ፈንታ የተተኩት ቁራዎች ናቸው፡፡ የሚበሩት ደግሞ ጥቁር መስቀል ሰርተው ነው፡፡ "ቁራ" ባህላዊ ተምሳሌትነቱ ምንድን ነው? የ"መስቀሉ" ጥቁር መሆንስ? ማኅበረሰቡ "የቁራ መልዕክተኞች" የሚል ብሂል አለው፡፡ ተልዕኮውን የማይፈፅምና መልዕክትን ይዞ የሚጠፋ፣ የማይመለስ ሲል ነው፡፡ ተስፋ የማይደረግ፣ የሚረሳ ሲል ነው፡፡ ተቅበዝባዥም ሲል ነው፡፡ ይህ ብሂል አይሁዳዊ ሚትነት አለው (ዘፍ 8÷7)፡፡ "ቁራ" በኖኅ ዘመን ለብስራት መመረጡን ዘንግቶ መልዕክቱን ሳይፈፅም በመቅረቱ ተመሳሳይ ትርጉሞች ተሰጥተውታል፡፡ በኢሳያስ 34÷11 "ባዶነት" ማኅደር፣ ቁራ ደግሞ ኃዳሪ ሆኖ ተስሏል፡፡ በ1ኛ ነገስት 17÷4 ቁራዎች በኮራት ፈፋ ኤልያስን ለተወሰነ ጊዜ ቢመግቡትም ዘላቂ መጋቢዎች አልሆኑም፡፡ ምግብ ፍለጋም ወደ ሰራፕታ ሲሄድ እናስተውላለን፡፡ ይህም ጊዜያዊነትን የሚያስተማስል ነው፡፡ የምናሴን ጊዜ እናት አለመቀጠልን ያስተማስላል፡፡

ቁራ ጥቁር ነው፡፡ "ጥቁር"፣ በአመዛኙ ተስፋ ያለመኖር ምሳሌ ነው፤ ቴክስቱ በበቀለበት ማኅበረሰብ ዘንድ፡፡ ዛሬ በሀገራችን አብዛኛው ማኅበረሰብ ዘንድ የሀዘን መገለጫ ተደርጎ እንደሚወሰድ ልብ ይሏል፡፡ በሚትም፣ ብዙውን ጊዜ፣ የሚታወቀው በአፍራሽነቱ ነው፡፡ የረሃብ፣ የጥፋተኝነት፣ የኃዘን፣ የመጥፎ ዕድል… ምሳሌም ሆኗል (Ferber፣27-28)፡፡

ይህ ቁራ መስሎ የመጣው በአጭሩ የምናሴ የጊዜ-እንጀራ እናት ሰብዕና ነው፡፡ ምናሴ አንድም የ"*ሱፐር ኢጎ ረሃብ*"ና ማንነትን ማጣት፣ አንድም የጨለምተኝነትና በራስ ያለመተማመን፣ አንድም ኃላፊነትን ያለመወጣት ሰብዕና ባለቤት ሆኗል፡፡ ቁራዎች

የሰሩት መስቀልም ጥቁር ነው፡፡ “መስቀሉም” ቢሆን በሐዲስ ሚቶሎጂ ከሚታወቅበት የግብር ባህሪው የተቃረነ ፍቺ ይዞ የመጣ ነው፡፡ “ለምን ቢሉ?” መስቀል አንድም የብርሃን ማደሪያ ነው፤ የተሰቀለበት፣ ኃዳሪው፣ ብርሃን ነውና (ዮሐንስ 8÷12)፡፡ አንድም ወደ ብርሃንነት ተለውጧል፤ ንግስት ኢሌኒ ለሶስት መቶ አመት ተቀብሮ ከነበረበት አስቆፍራ ባገኘችው ጊዜ አብርቷልና፡፡ አንድም የዘላለም ህይወት፣ የኃይል፣ የፈውስ ምልክት ነው፤ “መስቀል ኀይልነ መስቀል ጽንዕነ መስቀል ቤዛነ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ” እንዲል (ገብረሥላሴ፣2000፣364)፡፡ ቁራዎቹ የሰሩት መስቀል ግን የጨለምተኝነት፣ የመከራና የሞት እሰቦችን ይዞ የመጣ እንጂ የኃይል፣ የብርሃንና የፈውስ ምንጭ ሆኖ አይደለም፡፡ ወዲህ ይህ መስቀል የእንጀራ እናቱ ምሳሌ ነው፡፡ የእንጀራ እናቱ የብርሃን ምንጭ አለመሆኗን ያስተማስላልና፡፡ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን በሚወጣበት መንገድ አላሳደገችውምና፣ ወዲህ የመከራ ምንጭ፣ ወዲህ ደግሞ ከዕውቀት የራቀች ናት ሲል ነው፡፡ ብርሃን የዕውቀት፣ የዘላለማዊነትና የጽድቅ ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳልና፡፡ ከእውቀት ውጭ በመሆኑ የእግዚአብሔር ህዝብ ጠፍቷል (ሆሴዕ 4÷6)፡፡ የ“ጠፋ” ህዝብ መኖሪያው ጨለማ ነው፡፡ ይህ የ“ጠፋ” ህዝብ ከጨለማ ወደ ብርሃን ተመልሷል፤ “በጨለማ የሄደ ህዝብ ብርሃን አየ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው” እንዲል (ኢሳ 9÷2)፡፡ የዚህን ብርሃን ዕውቀትነት የሚያጠይቅልን ጳውሎስ የሕግ አዋቂ በመሆኑ በጨለማ ላሉ በዕውቀት ብርሃን እንዲመራቸው፣ ሕጻናትንና ሰነፎችን [አላዋቂዎችን] እንዲያስተምር መታዘዙ ነው (ሮሜ 2÷19-20)[6]፡፡ “ጥቁር” የጨለማ ምሳሌ ሲሆን፣ በግሪክ እና በሮማውያን ባለቅኔዎች የብቸኝነት፣ የፀጥታ፣ የማይታይ አደጋ ጊዜ፣ የብርሃን ፍቅርን የሚነጥቅ… ተደርጎ ተስሏል (Ferber፣137)፡፡ ይህም የምናሴን ቀጣይ ሰብዕና ያስተማስላል፡፡ የሰብዕና ዕድገት በተከታታይ ደረጃዎች የሚበለፅግ እና ቀዳሚው ለቀጣዩ መነሻ፣ ቀጣዩ ደግሞ ለቀዳሚው ማሳረጊያ እንደመሆኑ ምናሴ ያበለፀገው ሰብዕና ብቸኝነትን፣ ማኅበራዊ ኃላፊነትን መሸከም ያለመቻል እና በራስ ያለመተማመን ስሜት ነው፡፡ ይህም ትውልድን ማኅበራዊ ከማድረግ፣ ከማስተማርና ባህልን ከማበልፀግ ይልቅ ለስራ የማይተጋና ለማኅበረሰቡም አዲስ ነገር የማይፈጥር “መኻን” የሆነ የጎልማሳነት ህይወትን የሚመራ እንደሚሆን ያጠይቃል፡፡

[6] መክብብ 2÷16፣ ዳዊት 4÷6፣ 90÷8፣ 104÷2፣ 119÷105፣ ኢሳያስ 42÷6፣ 2ኛ ቆሮንጦስ 4÷6፣ ዮሐንስ 1÷9፣ የሐዋርያት ስራ 13÷47፣ ማቴዎስ 5÷14 ይመልከቱ፡፡

የሁለተኛው “ጥንድ”(ጥቁር) መልክ ይዘው እንደ ሰብዕና መባያነት የመጡት በጠመዝማዛ ወንዝ ላይ የሚንሳፈፉ “ዳክዬዎች” ናቸው።

> … ጥቋቁር ዳክዬዎች የወንዙን ጠመዝማዛ ተከትለው እየሳቁ ቁልቁል ወረዱ። ይንሳፈፉበት ወደ ነበረው አግጣጫ ጠጠሮች ወርውሮ ውሃውን አንቦጫረቀ፤ ወንዙ የፈጠራትን ትንሽ ሐይቅ የተረበሸ ደለል ጭቃ ቀባት (ማሕሌት፣99-100)። [አጽንኦቱ የእኔ ነው]

በዚህ አስረጅ ከላይ በጠቀስኳቸው መባያዎች ውስጥ የዳሰስኩትን “ጥቁር” አልደገመውም፤ ሚናው አልተለወጠምና። ይልቁንም አጽንኦት ስለሰጠኋቸው ብቻ እላለሁ። “ዳክየ”፣ “ወንዝ” እና “ሐይቅ” መባያ ጉዳዮች ናቸው።

### *“ዮርዳኖስን መሻገር”*

> … Crossing [rivers] is often symbolically important. […] Travelling up or down rivers might also mark changes in symbolic states.
>
> (Ferber,170)

ከFerber በተዋስኩት ጥቅስ ልንዝ ብፈልግ ምናሴን በቀጥተኛ ብሂሉ አላገኘውም። “ለምን ቢሉ?” አንድም ወንዙን ለመሻገር፣ አንድም ወንዙን ተከትሎ ወደ ላይ ወይም ወደ ታች ሲሄድ አልተመለከትነውምና ነው። ዳሩ ግን በዳክዬዎቹ በኩል አገኘዋለሁ። ወንዝን መሻገር ወይም አለመሻገር፣ ከምንጬ ተከትሎ ወደ ማረፊያ ሐይቁ ቁልቁል መውረድ ወይም ወደ ምንጬ ለመድረስ ዳገቱን መጓዝ የራሱ መወክልነት ያለው ዘይቤ ነው። ለእስራኤላውያን ዮርዳኖስን መሻገር (ኢያሱ 3÷14-17)፣ አንድም ለአራት መቶ ሰላሳ ዘመናት በግዞትና በባርነት ከነበረቡት ምድር ወደ ርስት ሀገራቸው ከነዓን መግባት ነው። አንድም “የነፍስ ሞት”ን ድል ነስቶ ዘላለማዊ ወደሆነው ሰማያዊ ርስታቸው የመሸጋገር ተምሳሌት ነው፤ በጽድቅና የመኖር ተምሳሌት። ይህም የልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይሉን ስራቶችና ማኅበረ-ባህላዊ ማንነታቸውን በመጠበቅ የሚያገኙት ነው። ወንዙን አለመሻገር “ሞት”፣ መሻገር ደግሞ ህይወት ነው። ወንዝ ያጡትን የመፈለግ ጉዞ ምሳሌም ነው፤ የግሪኩ የወንዝ አምላክ “አልፌየስ” (Alpheus) ድንግሏን “አሬቱሳ” (Arethusa) ከሲሲሊ ለመፈለግ ወደ ወንዝ ተቀይሮ ፈሷልና (Manser፣14)። ወንዝ ማረፊያው ሐይቅ ነው። “ሐይቅ” ደግሞ በአመዛኙ የአደገኛ እና የባዕድ ቦታ ትዕምርት

ነው። የአማልክት መፈጠሪያም ማደሪያም ነው። የግሪኳ "አፍሮዳይት" ከሐይቅ "አረፋ" ተወልዳለች (21)። ሆሜርም የአማልክት መገኛቸውና ማደሪያቸው ከሐይቅ ነው ብሎ ያምናል። ይህ ቢሆንም ቅሉ በሥነ ጽሑፍ "ልደት" እና "ሞት" የሚራራቁ ባለመሆናቸው ከጽሑፎች በአንድነት ይፈለቀቃሉ (Ferber፣179-80)። ሐይቅ የህይወት መገኛ፣ የህይወት ማብቂያ ተምሳሌትም ነው፤ ወንዝ በሐይቅ ውስጥ ያንቀላፋልና። በሌላ በኩል ዳክየዎችም የራሳቸውን የዘይቤ ፍቺ ይዘው የገቡ ናቸው። Manser የሆላንዳዊውን አንደርሰንን ተረቶች በተነተኑበት፣ "ዳክየ" የተፈጥሯዊ ብቃት ማነስ ምሳሌ ናት ይሏታል (480)።

ምናሴ ወንዙን አይሻገርም። ተመስጠው በወንዙ ላይ ተንሳፈው ወደ ሐይቁ ቁልቁል በሚወርዱ ዳክየዎች ላይ ነው። አንድም የተሳካ ማኅበራዊ ሽግግር አለማድረጉን፣ አንድም የማኅበራዊነት ሰብዕናው መውደቅ፣ አንድም የወንዙ ወደ ባዕድ እና አደገኛ ክልል መፍሰስ የምናሴን ማኅበራዊ ቅቡል ያልሆነ ሰብዕና እያዳበረ መሄድን፣ አንድም ሐይቅ "መገኛ" እንደ መሆኑ ሰብዕናው በእንጀራ እናቱ ምክንያት እንደ አዲስ መወለዱን ያጠይቃል። ሞትም ልደትም በሐይቁ ውስጥ አሉ። በዚህ አስተማስሎ ደግሞ ሐይቁ የእንጀራ እናቱ ትሆናለች ማለት ነው። ወዲህም ወንዝ የንግግርና የህይወት "ተቃልጦአዊ" ፍሰትን ያስተማስላል (Ferber፣170)። ወዲህም ይህ "ተቃልጦአዊ" ፍሰት የእንጀራ እናቱን በግብረ-አካላዊና ሥነ ልቡናዊ አፍራሽ ተፅዕኖ የተሞላ የአስተዳደግ ዘይቤንና ወደ እሷ የ"ወደቀ" ሰብዕና መኀተትን (በዘማዊነቷ ከማኅበረ-ባህላዊና ግብረ-ገባዊ እሴቶች ማፈንገጧን ልብ ይሏል) ይጠራል፤ ወንዙ የባዕድ ተምሳሌት ወደ ሆነው ሐይቅ ይፈሳልና። ወዲህም ከምንጩ ጀምሮ እስከ ሐይቁ ድረስ ያለው የወንዙ ፍሰት የሰውን ልጅ ህይወት ያስተማስላል (172)። ወዲህም የወንዙ ጠመዝማዛነት የአስተዳደጉን ወጥነት ያለመኖር፣ በዚህም የዕድገት ደረጃዎችን በአፍራሽና በስኬት-አልባነት መጨረስ ይጠራል። ቁልቁል መውረዳቸው የስኬት መላሸቅን ይነግራል። ቁልቁል መውረዳቸው ከመልካቸው ጋር የተገናኘም ይመስላል፤ ጨለምተኝነት። ተሻለን የወንዙ ምንጭ ላይ ሳይሆን መዳረሻው ላይ ነው የምናገኘው። ስለሆነም "ባዕድ" ሰብዕና ማዳበሩን ልብ ይሏል።

የሐይቋ አስቀድሞ "ንፁሕነት" እና ለወንዙ ምንጭ መሆን የምናሴን ቀዳሚ መልካምና ጊዜ-እናት ሰብዕና፣ የወንዙ ፍፃሜ እና የሐይቋ መረበሽና መደፍረስ የጊዜ-እናት ሰብዕና "መንጠፍ"ና የጊዜ-እንጀራ እናት ሰብዕና መግዘፉን ይጠራል፡፡ ዳሩ ግን የጊዜ-እናት ሰብዕና ጨርሶ አልነጠፈም፡፡ የተከታታይ ደረጃዎች መመጋገብም ሐይቋ ለወንዙ ባላት የገባሪነት ዑደት ተመስሏል፡፡ የወንዙና የሐይቋ ግንኙነት ተፈጥሯዊ ሂደትን የተከተለ ነው፡፡ ከሐይቋ የሚተነው ውሃ ተመልሶ የወንዙ ገባሪ ወይም/እና ምንጭ ሆኖ ሐይቋን ከመንጠፍ ይታደጋል፡፡ ይህ ሁነት የሚያጠይቅልን የጊዜ-እናት ሰብዕና ጨርሶ አለመንጠፍን ነው፡፡ ይህን ሃሳብ በወፎቹ ሁነትም መደገፍ ይቻላል፡፡

> ወፎቹን ለመቁጠር ወደ ሰማይ ቀና አለ…
>
> አንድ ቦታ ቆመው የሚያራግቡ ትናንሽ ቢራቢሮዎች ይመስላሉ፡፡ ሁለት … ሦስት … አራት … (*ማሕሌት*፣99) [አጽንኦቱ የራሴ ነው]

ከመራቃቸው የተነሳ "ወፎቹ" የሚታዩት "ቢራቢሮ" መስለው ነው፡፡ Ferber እንደሚናገሩት፣ "ቢራቢሮዎች" ለጸጋና ለቸርነት በሚላኩ መላዕክት ይመሰላሉ፡፡ በፀደይ (ጥቅምት) ብቅ የሚሉ የመልካም ጊዜ አብሳሪዎች ናቸውና ስለሚመጣው ጊዜ የሚኖርን መልካም ምኞት ያስተማስላሉ (38)፡፡ ስለሆነም ያ የወደፊት የመልካም ጊዜ ተስፋ፣ ያ የቸርነት ጊዜ አሁን እንደራቀ፣ ነገር ግን በሩቁ በናፍቆት እንደሚታይ ልብ ይሏል፡፡ ከወጨጫ ተራራ ወደ እሱ የሚነፍሰውም ንፋስ ማኅበረ-ልቡናዊ ሰብዕናው ከማኅበራዊነት የሚነጥል "አደገኛነቱን" የሚያሳይ ነው፡፡

## *"ተራራ ወ ንፋስ"*

> ***"ወደ ተራራው እንዳትወጡ ጫፉንም እንዳትነኩ ተጠንቀቁ ተራራውንም የነካ ፈፅሞ ይሞታል፡፡"***
>
> **ዘጸአት 19÷12**
>
> ***"ነፋስህን አነፈስህ÷ ባሕርም ከደናቸው፡፡"***
>
> **ዘጸአት 15÷10**

"ተራራ" እና "ንፋስ" በሚቶሎጂ ተደጋግመው የሚነሱና ከልዕለ ተፈጥሮ ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ "ተራራ" በአፍሪካና በግሪክ ሚቶሎጂ የልዕለ ተፈጥሮ ማደሪያ፣

አደገኛና አስፈሪ ቦታ ነው። ብዙዎቹ የግሪክ አማልክት በኦሊምፐስ ተራራ ከትመዋል። አፖሎ ከሄሊኮን፣ አርጤምስና ዲዮኒሰስ ከሲጢሮን ይበሩ ነበር (Lynch፣75 እና Ferber፣131)። በአይሁድ ሚትም ተራራ የእግዚአብሔር ማደሪያና የተቀደሰ ቦታ ነው። “ኮሬብ”፣ “ሲና”፣ “ሖር”፣ “ሞሪያም”፣ “ፋራን”፣ “ታቦር” እግዚአብሔር ያደረባቸው፣ የተገለጠባቸውና ለ“ስጋውያን” (“Mortal” ለማለት ነው) አስፈሪና አደገኛ ቦታዎች ናቸው።[7] በብሉይ ሚቶሎጂ ማርያም ከ“ሊባኖስ”፣ “አማና”፣ “ሳኔር”ና “ኤርሞን” ተራራዎች እንደም-ትገለጥ ትንቢት ይነገራል (መኃ 4÷8)። “ተራራ” የሕግና የቃል ኪዳን መገኛ ነው (ዘጸ 24÷12፣32÷15)። “ስጋውያን” በተራራ ላይ ተቀስፈዋል፤ አሮን በ“ሖር”፣ ሙሴ ደግሞ በ“ናባው” ተራራዎች ሞተዋል (ዘኍ 33÷39፣ ዘዳ 32÷49-50)። የሙታን መናፍስት ተገልጠውባቸዋል፤ “ስጋውያን” ደግሞ በተራራ ላይ ከፍርሃት የተነሳ ተጨንቀዋል (ማቴ 17÷1-7)።

“ንፋስ” የአማልክት መገኛ፣ የቁጣቸው መገለጫና የቅጣት በትር ሆኗል። በግሪክ አስትራዮስ (Astraios) ከነፋስ ተወልዷል። አሪስታዮስ (Aristaios) በሞቃታማው የሰሜን ንፍቀ ክበብ ክረምት ለአርባ ቀናት የላከውን ቀዝቃዛ ንፋስ እንዲወስድና ከመከራ ፊቱን እንዲያዞርለት ዚየስን ተማፅኖታል። እነ ኦዲሴ ከነፋሳት አለቃ ኤሎስ (Aiolos) የተሰጣቸውን የታሸገ ንፋስ በመክፈታቸው ወደ ኢታኬ (Ithake) ያደርጉት የነበረው ጉዞ ተስተጓጉሎባቸዋል፤ ወደ ኋላም ተመልሰዋል (Ferber፣27፣38፣127፣202)። ንፋስ በብሉይና በሐዲስ ሚቶሎጂ የእግዚአብሔር ቁጣ መገለጫ፣ የጥፋትና የመከራ በትር ነው።[8] የባዶነትና የወናነት ተምሳሌትም ነው (ትንቢተ ኤርሚያስ 5÷12፣)። የህይወት መገኛም ነው (ኢዮብ 33÷4)።

የምናሴ ታሪክ የሚጀምረው “ተራራን” ሰዋዊ ባህሪ በመስጠት ነው። “የወጨጫ ተራራ ቁልቁል ያየዋል” (ማሕሌት፣96)። ተራራ ለስጋውያን አስፈሪና አደገኛ መሆኑን ስናጠይቅ የግሪካውያኑ አማልክት ማደሪያ “ኦሊምፐስ” እና የብሉይ ሚቶሎጂውን “ሲና” በመጥቀስ ነው። የሚያድሩባቸው የመናፍስት መሪዎች ናቸው፤ ህግን የሚያስተምሩ፣

---

[7] ዘጸ 3÷1-6፣19÷11-13፣ ዘዳ 33÷2፣ ዘኍ 20÷23-29፣ ማቴ 14÷23፣15÷29፣17÷1-7፣ ሉቃ 21÷37።

[8] ኢዮብ 1÷19፣9÷17፣ ኢሳያስ 40÷7፣ ዮናስ 4÷8፣ ማርቆስ 6÷4።

ትዕዛዛቶቻቸው እንዲከበሩ የሚተጉ፣ ይህ ካልሆነ ግን ቅጣታቸው "ዘግናኝ" የሆነ፡፡ "ተራራው" የማኅበረ-ባህላዊው ስርዓት አስተማሳይ ሆኖ ነው የመጣው፡፡ በርግጥ "አባዊ" በሆነ ማኅበረሰብ እያንዳንዷ ማኅበራዊ ስርዓት የምትወከለው በአባት ቢሆንም ቅሉ፣ የተሻለ አባት ባለመኖሩ፣ ይህን ሚና ወስዳ የመጣቸው የእንጀራ እናቱ ናት፡፡ ስለሆነም በአሳዳጊነቷ ትዕዛዛትን በሻረ ጊዜ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ቅጣት እንደምታደርስበት ጠቅሻለሁ፡፡ ናዳብና አብዩድ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በማፍረሳቸው በሲና ምድረ በዳ እንደሞቱ (ዘኁልቁ 3÷4)፣ ምናሴ በእንጀራ እናቱ "ትዕዛዜን አልፈፀምክም!" በሚል ቅጣት ከማኅበራዊነት ሰብዕናው ተለየ፤ ማኅበራዊ ኃላፊነትን የማይወጣና ትጋት የሌለው ሆነ፡፡

እነሆ ከእሷ የሚወጣው ቅጣት ሁሉ የአፍራሽ ሰብዕና ሰሪ እንደሆነ ከተራራው በሚወርደው ነፋስ ተመሰለ፤ "ከወጨጫ ተራራ ቁልቁል በሚንደፋደፍ ነፋስ÷ዛፎች ወደ መኻል ከተማው አግጣጫ ይሰግዳሉ" (*ማሕሌት*፣98)፡፡ የቅጣትን ትዕዛዝ የተሸከመው ነፋስ በፈርኦንና በሰራዊቱ ቀይ ባህርን እንደከደነባቸው፣ እንዲሁ የእንጀራ እናቱን ትዕዛዛት መሠረት ያደረጉ ቅጣቶች ያን የብሩኅ ተስፋና የትጋት፣ የመተማመንና ራስን የመቻል ሰብዕናውን አጨለሙት፡፡ በራሱ የማይተማመንና ፈሪ (106)፣ በብቃቱ የሚጠራጠር አደረጉት፤ በሰራው ስራ "ምን ትል ይሆን?"፣ ሲል እንሰማዋለንና (103)፡፡ *ሎይስ ታይሰን* እንደሚያስረዱት፣ ይህ ሰብዕና ግላዊ ማንነትን ጠብቆ ከማቆየት የሚያግድና በሌሎች ሰዎች በቀላሉ የማንነት ሚና መነጠቅን የሚያስከትል ነው፡፡

> *Insecure or unstable sense of self*– the inability to sustain a feeling of personal identity, to sustain a sense of knowing ourselves. This core issue makes us very vulnerable to the influence of other people, and we may find ourselves continually changing the way we look or behave as we become involved with different individuals or groups (2006,16-17).

ከዚህ በተጨማሪም የጥፋተኝነትና የበታችነት ስሜት አዳብሮም እንመለከተዋለን፡፡ "ደሞ ብዙ የለም ይለኛል፡፡ ሌላው ከየት አመጣ?" ትለኛለች ብሎ ሲጨነቅ እንሰማዋለን (ማሕሌት፣103)፡፡ ሰርክ ከሌሎች በማሳነስ የምታሳድርበት ሥነ ልቡናዊ ቅጣት ትዝ ይለዋል፡፡ ይህም "ራስን ዝቅ አድርጎ የመገመት ስሜት"ን (Low self esteem)

እንዲያዳብር አድርጎታል፤ "እኔ የማልደነቀ-ውና ክብር የማይሰጠኝ ከሌሎች ስለማንስ ነው!" የሚል ስሜት (Tyson፣16-17)፡፡

### 3.1.2. "ስለ ድልድዩ ልጅ ትዝታ"፤ ማኅበረ ልቡናዊ ማንነትና የአሳዳጊዎች ሚና

እንደ "ማሞ" ሁሉ በቴክስቱ ገፀ-ልጅ ሆኖ የተሳለው ዳዊት ሰብዕናው የሚገነባው ሁለት የተለያዩ የአስተዳደግ ዘይቤዎች በሚከተሉ ወላጆቹ ነው፤ በእናቱና በአባቱ፡፡ በእናቱ የሚደርስበት "አጻፋ"ና በአባቱ የሚያገኘው "ይሁንታ" የሰብዕናው መሠረቶች ናቸው፡፡ የዳዊት ሰብዕና በተወዳዳሪነት፣ በእልኸኛነት፣ ፍራትን በመናቅ፣ በ"ቀናተኛነት" እና በዓላማው ቆራጥነት የተገነባ ነው፡፡ ይህ ማንነት በአሳዳጊዎቹ ሚና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

እንደ "ማሞ" ሁሉ "ወንዝ" መሻገር በዚህ ቴክስት ውስጥ የሚመጣ መባያ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ሚታዊ ሚናው ከላይ ባነሳሁት የሚጸና እንደመሆኑ በዚህ ንዑስ ክፍል አልደግመውም፡፡ ከወንዙ በላይ በተዘረጋው ቧንቧ "እየተንጨዋለሉ" ወንዙን መሻገር ዳዊት ከሰፈሩ ልጆች ጋር የሚያደርገው ውድድር ነው፡፡ ለዚህ ውድድር እናቱ እና አባቱ ተቃራኒ አቋም አላቸው፡፡ በዋናነት የሚወደዳረው ደግሞ ከእሱ በዕድሜ ከሚበልጥ ተስፋዬ ከተባለ አንድ የቂስ ልጅ ጋር ነው፤

> "ዳዊት! ዳዊት! በዚህ ቧንቧ ላይ ትሔጅያለሽ?"
>
> "እንዴት?" አልኩት ተስፋዬን፡፡
>
> "በእጅሽ እየተንጨዋለልሽ"_ በድልድዩ ስር ከሚፈሰው ወንዝ ላይ በጣም ዕርቆ የተዘረጋ ቧንቧ አሳየኝ፡፡ (*ማሕሌት*፣187)

ይህን ከማድረጉ በፊት ወንዙን ያጠናል፡፡ ይሁን እንጂ እናቱ የምትሰጠው ምላሽ ከወንዙ እንዲርቅና እንዲፈራ፣ በተፈጥሮና በከባቢው እንዲጠራጠር የሚያደርግ ነው፡፡

> ከዓመት ወይም ከሁለት ዓመት በፊት ከእናቴ ጋር ገበያ ይመስለኛል ÷ ደርሰን ስንመለስ የወንዙን ምሥጢር ለማየት ጎን ያለውን መገደቢያ በሁለት እጄ ይዤ ወደ ላይ እየተሳብኩ ወደ ታች ለማየት ስሞክር÷

> 'እንዴ! እንዴ ጋኔን ይምታህ ደሞ?... ሁለተኛ እንዳላይህ፡፡ ምኑ ደስ ይላል? የጋኔን ቦታ እኮ ነው' ካለችኝ ወዲህ እስክጠግብ ድረስ ብንጓም÷ አይቼው አላውቅም፡፡ (187)

እናቱ ልማዳዊ አመለካከትን ተከትላ ልጇን ካለበት የውድድር መንፈስ ለማራቅ ትጥራለች፡፡ "ጋኔን"፤ "መልከ ጥፉ"፣ "እኩይ"፣ ለሰው ልጅ ጥፋት የሚተጋ መንፈስ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ እናቱ የምታስፈራራው በዚህ መንፈስ ነው፡፡ ይህ የእናቱ ድርጊት ከባቢውን እንዲጠራጠርና ከራስ መተማመኑ ዝቅ እንዲል የሚያደርገው ቢሆንም ቅሉ፣ አባቱ ከዚህ ስሜት እንዲወጣ ያደርገዋል፤

> "አሁን ታዲያ ምን አስበሃል?" አለኝ፡፡
>
> "ምኑን?" አልኩት፡፡
>
> "ቧንቧውን ስለ መሻገር፡፡"
>
> ቀና ብዬ አየሁት፡፡ ይሥቃል፡፡ ትከሻዬን ነቀነቅሁ፡፡ 'ምንም' እንደማለት ዐይነት፡፡
>
> "ልጁን ነገ አትገጥመውም?"
>
> "እንዴት?"
>
> "በቧንቧው እንደምትሻገር አሳየው፡፡" (191-2)

ማኅበረሰቡ በ"አባዊ ስርዓት" የጸና በመሆኑ የአባት ትዕዛዞች ከእናት ይልቅ ይጸናሉ፡፡ እናትም ብትሆን ብዙውን ጊዜ "ቆይ! ለአባትህ ሳልናገር!" ስትል ትሰማለች፡፡ ከእናቱ ትዕዛዝና ማስፈራሪያ ይልቅ የአባቱን ይሁንታ ይከተላል፡፡ በዚህም ዳዊት ወንዙን በቧንቧው ላይ "ተንጨዋሎ" ሲያልፈው እንመለከታለን፤

> ድልድዩ አጠገብ ጫጫታ መኖሩን ስለ ሰማ መሰለኝ ተስፋዬ እየሮጠ መጣ፡፡ ብዙ ተማሪዎችና ዐላፊ መንገደኞች ተሰብስበው ድልድዩን ስሻገር ይመለከቱኛል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ተሻገርኩ፡፡ (192)

ይህ የተወዳዳሪነት፣ የማሸነፍ፣ የትጋት ስሜት ከአባቱ የአስተዳግ ዘይቤ የመነጨ ነው፡፡ ወንዙን መሻገር "ዮርዳኖስ"ን መሻገር ነው፡፡ ከነበረበት ማንነት ወደ ማኅበራዊ ሥርዓቱ መቀላቀል ነው፡፡ "ተፈጥሯዊ/ደመ-ነፍሳዊ" ማንነቱ በማኅበረ-ባህላዊ ስራቱ እና በግብረ ገብ እሴቶች "መጠመቅ"ና የማኅበረሰቡ ልጅነትን መቀዳጀት ነው፡፡

በዳዊት ሰብዕና ላይ አሻራቸውን ከሚያሳርፉ እናት አባቱ ውጭ ተስፋዬም የራሱን ሚና ይዞ ተስሏል፡፡ "አባዊ ስርዓቱን"፣ በጥቅሉም ማኅበረ-ባህላዊ አስተሳሰቦችን ወክሎ የዳዊትን ሰብዕና ይገነባል፡፡ እንደማኅበረሰቡ፣ ባህሉና ሥርዓቱ የሚያገላቸውንና የሚያርቃቸውን ያርቃል፡፡ ማኅበረሰቡ መጥፎና ጠቃሚ ያልሆኑ፣ የሰውን ልጅ ፈታኝ ሁነቶችና ድርጊቶች በሰይጣን እንደሚመስል ሁሉ እሱም አፉን ለስድብ የሚከፍተው "ሰይጣን" በማለት ነው፡፡ "ጥሩዋም መጥፎዋም ለእርሱ ያልጣመችው ነገር ከሆነች የሰይጣናም ስራ ወይም ፍርሃት ናት" (183)፡፡ ማኅበረሰቡ ባልተስማማበትና በማይደግፈው መንገድ መሄድ ክፉ መንፈስ አድርጎ በሚያስበው "ሰይጣን" ይመስለዋል፡፡ ጀግንነትን እንጂ ፍርሃትን በማያበረታታ ማኅበረሰብ ፈሪ መሆንም ያሰድባል፤ ከክብር ያሳንሳል፡፡ ይህን የማኅበረሰቡን አቋም ሚና ወስዶ የተሳለ ገፀ ባህሪ ነው፤ ተስፋዬ፡፡ አንድም ለጊዜውም ቢሆን የተስፋዬ የበላይነት ማኅበራዊ ስራቶች በተፈጥሮ ላይ ያላቸውን ልዕልናና የልዕልና ፍላጎት ይመስላል፡፡ አንድም ዳዊት ከተስፋዬ ጋር በተወዳዳሪነትና በአሸናፊነት መስተካከሉ የባህልና የ"ተፈጥሮ" ማንነቶች በልጅነት ሰብዕናው ውስጥ መጎራበትን ይጠራል፡፡ አንድም የተስፋዬ ዕድሜ ከዳዊት መብለጡ ማኅበረ-ባህላዊው ስራት ግለሰቦችን ቀድሞ መጠበቅን (ቅድመ ልደት) እንደሚጠራ ልብ ይሏል፡፡

በሌላ በኩል ፍትወታዊ ፍላጎት በድልድዩና በመደገፊያው ስዕላዊ ሆኖ ቀርቧል፡፡ መሰላል፣ ምድር፣ ሰማይ፣ መውጣት፣ መውረድ፣ ተራራ፣ ድልድይ፣ መብረር፣… እጅግ ዘረ መላዊ ትዕምርቶች እንደሆኑና ከሰው ልጅ ፍትወታዊ አዕምሮት ጋር የተቆራኙ እንደሆኑ ያስረዳሉ (Freud፣1920፣62-63)፡፡ በቴክስቱ ውስጥ የቀረበው "ስዕላዊ" ገለጻ የዳዊት ፍትወታዊ ፍላጎት ነው፡፡ "… የወንዙን ምስጢር ለማየት ጎን ያለውን መገደቢያ በሁለት እጄ ይዤ ወደ ላይ እየተሳብኩ ወደ ታች ለማየት ስሞክር …" (*ማሕሌት*፣187)፡፡

## 3.2. "ልጅነት" በ*አለንጋና ምስር*፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ

በዚህ ንዑስ ክፍል የ"ዘላን"ና የ"አለንጋና ምስርን" የ"ልጅነት" ማኅበረ-ልቡናዊና "ሳይኮሴክሿል" ሰብዕናን እመረምራለሁ፡፡ በማያያዝም የ"ልጅነት" ማንነቶች በወጣትነት እና ጎልማሳነት ዘመን ያሳደሩትን ተፅዕኖ ለመተርጎም እሞክራለሁ፡፡

### 3.2.1. "ልጅነት"፤ ማኅበረ-ባህላዊ ፍንገጣና የ*Sadistic displacement* ማደሪያ በ"ዘላን"

> Thus sadism would correspond to an aggressive component of the sexual instinct which has become independent and exaggerated and, by displacement, has usurped the leading position.
> (Freud,1905,158)

የፍሮይድን ሃሳብ ወደ አማርኛ ብናለምደው፣ "በሌሎች የስሜት መጨቆን መደሰት (Sadism) ጤናማ ያልሆነ ፍትወታዊ ደመ ነፍስ ሲሆን ቦታውን በሌላ ተመሳሳይ አካል በመተካት የሚገኝ የ"ጎነ" እርካታ ነው" የሚል ይሆናል፡፡ በዚህ ሃሳብ ወደ ልቦለዷ ታሪክ መዝለቅ ይቻላል፡፡ የልቦለዷ የታሪክ ባለቤት ተሻለ አደፍርስ ነው፡፡ እናቱ ስሙን ያወጣችለት በፍቅር የምትንገበገብለት አባቱ፣ አደፍርስ፣ ፍትወታዊ ፍላጎቱን ካደረሰ በኋላ ጥሏት በመሰወሩ ከአባትህ ብትሻል ብላ ነበር፡፡ ተሻለ በዚህ ልቡናዊ ቀውስ ውስጥ ባለች እናቱ በማደጉ የእናቱ በሰዎች ስሜት መደሰት (Sadistic Displacement) የአጻፋ ስልት ታላሚ ነው፡፡ የእናቱ አደፍርስን የመበቀል ኢ-ንቁ ልቡናዊ ግፊት የሚያርፈው በእሱ ላይ ነው፡፡

> "የት አደርክ?"
>
> ዝም፡፡
>
> "ሆድህን ልትሞላ ነው የመጣኸው አይደለም?"
>
> ክርኑን አከከ…… አይኖቹ ተቅለበለቡ…… የሚመልሰው ጠፋው…… ሳትረበሽ ፊቷን ዞር አድርጋ አየችው……እሱም ትክ ብሎ አያት……ከንፈሮችዋን መጠጠች፡፡ ይሄ ነገር--ከንፈር ሲመጠጥ……ሲሰማ አንጀቱ ውስጥ የተደበቀ ውርደት ሳይፈልገው ይቀሰቀሳል፡፡ ሊሸከመው የማይችለው እርግማን ይሰማዋል፡፡ በመደናገጡ፣ እርዳታም በማጣቱ፣ በመውደቁ የሳቀችበት መሰለው፡፡ እየሮጠ ወጣ…… (*አለንጋና ምስር*፣28)፡፡

የመጀመሪያው የቀናተኝነቷ ምልክት "የት አደርክ?" የሚለው ነው፡፡ አደፍርስ ለጊዜያዊ መጠቀሚያ አድርጓት በመሄዱ በቀሏን ወደ ልጇ ያደረገችው ብርቱካን፣ ተሻለ የመጣው ለጊዜያዊ ጥቅም ፍለጋ እንደሆነ እንድታስብ አድርጓታል፤ ሆድህ ስለጎደለ እንጂ

አትመጣም ነበር ስትል፡፡ ወይም በምናቧ ውስጥ ተሻለ የለም፡፡ "ከንፈሯን ስትመጥም" እንመለከታለን፡፡ ከእናቱ ፍቅር በማጣቱና በጥላቻ ማደጉ ተሻለን ፈሪ፣ እረዳት የሌለውና በውድቀቱ ሌሎች (የመጀመሪያዋ "ሌላ" እናቱ እንደሆነች ልብ ይሏል) የሚደሰቱበት አድርጎ እንዲገነዘብ አድርጎታል፡፡ እዚህ ላይ ሁለት ሰብዕናዎች በተሻለ ላይ ልቀው ይታያሉ፡፡ የመጀመሪያው የ"መተው"፣ የ"መጣል" ፍራት (fear of abandonment) ነው፡፡ ይህ ስሜት የተፈጠረበት ሰው "የሚቀርቡኝና የሚወዱኝ ሰዎችም ቢሆኑ ለእኔ አይጨነቁም" የሚል አስተሳሰብን ያዳብራል (Tyson፣16)፡፡ ሁለተኛው የ"መከዳት ፍራት" (fear of betrayal) ነው፡፡ በዚህ ስሜት ውስጥ የሚኖር ሰው፣ የሚወዳቸው ጓደኞቹን፣ በጥቅሉ በአቅራቢያው ያሉ ወዳጆቹን፣ ሁሉ ይጠራጠራል፡፡ አያምናቸውምም፡፡ ከፊታቸው ዘወር ሲል የሚያሙትና የሚስቁበት ይመስለዋል፡፡ እንደማይዋሹትም እርግጠኛ አይሆንም (ዝኒ ከማሁ)፡፡ ከላይ ባቀረብኩት አስረጅ ውስጥ፣ በአሳዳጊው ምክንያት፣ ተሻለ እነዚህን ሰብዕናዎች ማዳበሩን እንመለከታለን፡፡

እናቱን በግልፅ እንደሚፈራትም ይናገራል (*አለንጋና ምስር*፣42)፡፡ ምክንያቱም አስተዳደጓ አካዊና ሥነ ልቡናዊ ጫና ያለበት በመሆኑ ነው፡፡ ትገርፈዋለች (30)፡፡ በነገር ትጎሽምጠዋለች፡፡ የሚከተለው አስረጅ ይህን ያሳያል፤

> "እኔ የማድረው የኪራይ ገንዘብ እየለቀምኩ ነው…… እንደ አባቱ እርኩስ ነው" 30)፡፡
>
> … ብርቱካን የአባቱን <u>የአደፍርስን ፎቶግራፍ ከተሰቀለበት ምስማር ላይ አውልቃ ተሻለን በሩጫ ተከተለችው፡፡</u>
>
> <u>"የእዚህ ሽንት አይደለህም መጀመሪያውኑስ</u>……እ……እ ጠብቀኝማ <u>እኔ ብርቱካን አይደለሁም አንተን ካልገደልኩ"</u>
>
> … <u>የያዘችውን ፎቶግራፍ በእሱ አቅጣጫ አምዘግዝጋ ወረወረች</u>……ለጭቃ መከላከያ ግቢው ውስጥ የተደለደለ <u>በድንጋይ የተሰራ እግር መንገድ ላይ ተሰባበረ……</u> (33)፡፡ [አጽንኦቱ የእኔ ነው]

በመጀመሪያው ጥቅስ ውስጥ የተቀናጁት ሁለቱ ዓረፍተ ነገሮች አገባባዊ ዝምድና (contiguity order)[9] የላቸውም፡፡ የመጀመሪያው ኢ-ንቁ ልቡናዊ በሆነ ክስተት ሥነ

---

[9] ይህ የቋንቋ መታጎል ሥነ ልቡናዊ በሆኑ ትውክቶች አማካኝነት የሚፈጠር ነው፡፡ የኢ-ንቁ ልቡና ግፊቶች ከንቁ ልቡና ጋር በሚያደርጉት ሽኩቻ አማካኝነት የሚፈጠር "አገባባዊ መታጎል" (contiguity disorder) ነው፡፡ የሥነ ልሳናዊ አሃዶችን አግድሞሻዊ ግንኙነት (አገባብን) ጠብቆ

ልቡናዊ ተፅዕኖ እንዲያድርበት ያደረገችበት ነው፡፡ ቀጥሎ የመጣው ሁለት ሚናዎችን ይዟል፡፡ የእናቱን ማንነት እና በልጁ ላይ የሚያሳርፈው "የልቡና መታወክ"፤ ከላይ ታይሰንን ጠቅሼ ያሰፈርኳቸው ፍርሃቶች ናቸው፡፡ ይህ ቢሆንም ቅሉ የዓረፍተ ነገሮቹ አገባብ የቋንቋውን ስርዓት የተከተለ አይደለም፤ አጣማሪ የሚያስፈልገው ነውና፡፡ የእናቱን ሥነ ልቡናዊ መታወክም በእዚህ የተዛነፈ አገባብ መመርመር ይቻላል፡፡ የኪራይ ገንዘብና የአባቱ እርኩስነት አገባባዊ ዝምድና የላቸውምና፡፡

በመጀመሪያው አጽንኦት ውስጥ ብርቱካን ለዱላ የተጠቀመችበት የአደፍርስን ፎቶግራፍ ነው፡፡ ፎቶግራፉን ያመጣችው ከተሰቀለበት ሚስማር አውልቃ ነው፡፡ ይህ ድርጊት ብርቱካን ተሻለን የተከተለችው ተፈጥሯዊ "ሴትነቷን" ይዛ እንደሆነ ያጠይቃል፡፡ የበቀል ምንጩ የፎቶግራፉ ከሚስማሩ መውለቅ ነው፡፡ ወደ ተሻለ የተወረወረው ደግሞ ባለቀዳዳው ፎቶግራፍ እንጂ የቆመው ሚስማር አይደለም፡፡ ባለቀዳዳው ፎቶግራፍ ቦታውን ለቋል፤ ከቆመው ሚስማር ተለይቷል፡፡ ስለሆነም ቀዳዳው የሚሰቀልበትን (የሚሞላውን) አጧል፡፡ እዚህ ላይ ሚስማሩ አደፍርስ እንደሆነ አስበን እንለፍ፡፡ ሌላው "ሚስማራዊ" ሚና ያለው ደግሞ ተሻለ ነው፡፡ ባለቀዳዳው ፎቶግራፍ የተወረወረው ወደ ተሻለ ነው፡፡ ባለቀዳዳው ፎቶግራፍ የተወረወረው በፍቅር ሳይሆን በተሻለ ስቃይ ለመደሰት የተደረገ አጸፋ ነው፡፡ ይህ ኢ-ንቁ ልቡናዊ ክስተት ነው፡፡ ምክንያቱም የጥላቻና ማኅበራዊ-ፍንገጣ የሚስተዋልበት ነውና፡፡ ሚስማሩ ደግሞ አልተነቀለም፡፡ በዚህ ውስጥ፣ አንድም የሚስማሩ ጽናት የአደፍርስ ምሳሌ ነው፤ በተሻለ እናት ውስጥ በተፈላጊነቱ የጸና፡፡ አንድም የፎቶግራፉ ተነቅሎ በተሻለ አቅጣጫ መወርወሩ የተሻለን የአጸፋ ተቀባይነት ይጠራል፡፡ የተሻለ አጸፋ መቀበል ሌላው "ሚስማራዊ" "Figuer" (ባዮሎጂካዊ ወንድነቱ) በመሆኑ ነው፡፡ ፎቶግራፉ የተወረወረውም ይህን "ሚስማር" ፍለጋ ነው፡፡ ስለሆነም ብርቱካን ወደ ተሻለ የወረወረችው "ባዮሎጂካዊ" ሴትነቷን ነው፡፡ አንድም የፎቶግራፉ መንገድ ላይ መከስከስና ተሻለን አለመንካቱ አደፍርስን የመበቀል

---

ከማቆየት የሚያግድ "እውክ" ነው፡፡ በዚህም የአገባብ ዝምድና ይነጥፋል (Jackobson & Halle፣1956፣71)፡፡ ይህን መታጎል ላካን "Mytonymy" ሲሉት፣ (በThome፣2003፣36 እና Grosz፣1998፣100 ውስጥ እንደተብራራው) የኢ-ንቁ ልቡና ምኞት(desire) ሰርጓዊ የአገባብ ሚዛንን ባልጠበቀ የ"መወክሎች" ተሰናስሎ የሚገለጥበት ነው፡፡

ኢ-ንቁ ልቡናዊ ፍላጎት እንጂ ተሻለ ታላሚው እንዳልሆነ ልብ ይሏል፡፡ ይሁን እንጂ የብርቱካን ኢ-ንቁ ልቡናዊ የአጸፋ ስልት በተሻለ ሰብዕና ላይ ያስከተለው ተፅዕኖ አለው፡፡ እነሱም የ"ማኅበረ-ልቡና" እና የ"ሳይኮሴክሿል" ሰብዕናዎች ናቸው፡፡ ኋለኛውን በሁለተኛው ንዑስ ክፍል እመለስበታለሁ፡፡

ማኅበረ-ልቡናዊ ተፅዕኖው ከላይ ያነሳኋቸው፣ የፍራት፣ የተጠራጣሪነትና የበታችነት ስሜቶች ናቸው፡፡ እነዚህ የልጅነት ሰብዕናዎች ደግሞ በወጣትነትና በጎልማሳነት (በህይወት ዘመን ሁሉ) ዕድሜው ላይ የሚያስከትሉት ማንነት በባህላዊና ሚታዊ አስተማስሎ ቀርቧል፡፡ ይህም የ"ፀሐይ እየጠለቀች" መሆን ነው (45)፡፡ አስተማስሎውን በማንበቢያነት ብንጠቀመው እንዲህ ይሆናል፡፡

ቴክስቱ በበቀለበት ማኅበረሰብ ዘንድ ስለ ፀሐይ መጥለቅ፣ "የማታ ጀንበርና[10] የእናት ሞት አንድ ናቸው" ተብሏል፡፡ የእናት ሞት የተስፋ ማጣት፣ የብቸኝነትና የጎዶሎነት ስሜቶችን የሚያስከትል አስከፊ ክስተት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የፀሐይ መጥለቅም ከዚሁ ጋር ሲነጻጸር እናስተውላለን፡፡ በሚትም ከዚህ የሚለይ አይደለም፡፡ ለግሪኮች መኖር ፀሐይን ማየት ነው፡፡ የፀሐይ መውጣት የልደት ምንትነታቸው ነው፡፡ መሞት ደግሞ ፀሐይን አለማየት ነው፤ ሞት በጨለማ ተመስሏልና፡፡ በሆሜርና ሄሲዮድ ሞትና "እንቅልፍ" ወንድማማች ናቸው፡፡ ሁለቱም የብቸኝነትና የስግብግበነት መስተማስሎች ናቸውና፡፡ ስለሆነም የፀሐይ መጥለቅ የብቸኝነት ተምሳሌት ነው (Ferber፣54፣137፣209)፡፡ በብሉይ ሚቶሎጂ የ"ፀሐይ መግባት" ፍርሃትና ድንጋጤን ይጠራል (ዘፍጥረት 15÷12)፡፡ የ"ፀሐይ መውጣት" የመባረክና የመጻኢውን መልካምነት ያስተማስላል፡፡ እግዚአብሔር ያዕቆብን የባረከው ሊነጋ ሲል ነው፡፡ ያዕቆብ የተባረከበትን ቦታ ጵኒኤል ብሎ ጠርቶታል፡፡ ፀሐይ የወጣችው ወዲያው ጵኒኤልን ሲያልፍ ነበር (ዘፍጥረት 32÷26-31)፡፡ ሎጥ ከሰዶም ጥፋት ለመዳን ወደ ዞዓር ከተማ ተጉዟል፡፡ ዞዓር በገባ ጊዜም ፀሐይ በምድር ላይ ወጣለች (ዘፍጥረት 19÷23)፡፡ የ"ፀሐይ መውጣት" አሸናፊነትንና ኃያልነትን ይጠራል (መሳፍንት 5÷31፣ 2ኛ ሳሙኤል 2÷24)፡፡ የፀሐይ መግባት የእነዚህን ተቃራኒ ይጠራል፡፡ መጻኢውን "መጥፎ ዕድል"

---

[10] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የአማርኛ መዝገበ ቃላት "ፀሐይ" ይለዋል(487)፡፡

ያስተማስላል (1ኛ ነገስት 22÷26፣ 2ኛ ዜና መዋዕል 18÷34፣ ትንቢተ ሚክያስ 3÷)። ብቸኝነት ነው (ኢዮብ 30÷28)።

የተሻለ አስተዳደግ ዘይቤ ያስከተለበት "አፍራሽ" ሰብዕና በቀጣዩ የዕድገት ደረጃዎች "ማኅበራዊ-ቅቡል" እንደማይሆንና ህይወቱ በሙሉ በ"መጥፎ ዕድል" እንደሚጓዝ የምታሳየው ፀሐይ ገና አልገባችም። ግን ለመግባት እየተንደረደረች ነው (*አለንጋና ምስር*፣45)። ህይወቱ በሙሉ ያልኩት ፀሐይዋ <u>እንደማንኛውም ቀን</u> የማታ ብርሃኗን የምታበራ በመሆኗ ነው (ዝኒ ከማሁ)። ቆየት ብዬ እንደማነሳው፣ ይህ ሰብዕናው በርግጥም በወጣትነቱና በጎልማሳነቱ እንዴት "ጽድቅ" እንደሆነ በታሪኩ ከተዋቀሩት አጨራረሶች በአራተኛው እናስተውላለን።

ተሻለ በአስተዳደጉ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ቅጣት የሚደርስበት በእናቱ ብቻ አይደለም። ዳይሬክተሩና አስተማሪዎቹም በዚህ መልኩ ይቀጡታል።

> "ይሔ ለራሱም ለቤተሰቡም ለአገርም አይሆን" አለ ዳይሬክተሩ ለአስተማሪው……
>
> …
>
> "እጅህን ዘርጋ……" የጨው ውሃ ውስጥ ተዘፍዝፎ የደረቀ ጥቁር ጨርቅ እስኪመስል ገረፈው።
>
> …
>
> "ለእንደዚህ አይነቱ ልጅ ቤተሰቡን አልሰማ ካለ፣ እኛን አልሰማ ካለ ማታ ተማሪዎች ከመበተናቸው በፊት ተማሪው ፊት ይቅርታ እንዲጠይቅ እናደርጋለን" አሉት። (49)

ዳይሬክተሩ ሥነ-ልቡናዊ ቅጣቱን በሁለት መልኩ ሲፈፅሙት እንመለከታለን። የመጀመሪያው ወደ ፊት ማኅበራዊ ኃላፊነቱን የማይወጣ "ትንሽ" አድርገው የሚነግሩት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከ"አቻዊ ግፊት" የሥነ ልቡና ቀውስ እንዲመጣበት ማድረግ ነው። በተማሪዎቹ ፊት ይገርፉታል፤ ይሰድቡታል። እነዚህ ቅጣቶች ተሻለን የበታችነት ስሜት እንዲያዳብር ያስገድዱታል።

የተሻለ የልጅነት አስተዳደግ በወጣትነትና የጎልማሳነት ሰብዕናው ያሳደረበትን ተፅዕኖ የምናስተውልበት ከተዋቀሩት አራት የታሪኩ አጨራረሶች ውስጥ በአንዱ ነው።

በመጨረሻው አጨራረስ ውስጥ ዋና የታሪክ ባለቤት ሆኖ የመጣው “በላይ” ነው፡፡ ይህ ገፀ ባህሪ የተሳለው የተሻለ የልጅነት ሰብዕና ውጤት ሆኖ ነው፡፡ ስለሆነም በታሪኩ ያለው “በላይ” ሳይሆን “ተሻለ” ነው፡፡ ይህንም በሁለት መንገድ መመልከት እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው ከቴክስቱ ጀርባ መሄድ ሳያስፈልግ ከታሪኩ ቀጥታ በመጥቀስ ነው፡፡ ተሻለ ከእናቱ ጋር ሲጣላ የሚሄደው በእግሩ ወደ መርካቶ ነው (28)፡፡ በላይም ከትምህርት ቤት ሲወጣ የሚሄደው ወደ መርካቶ ነው (70)፡፡ “ያልተሰራበት ልጅነት ከተጎዱ አይኖች ጀርባ ትለፋለች፡፡” ሲል በላይን እንሰማዋለን (70)፡፡ “ቲቸር በላይ ግን ያለፈ ታሪኩን አያነሳውም፤ ለመተረት ምላሱ አትቀብጥም፡፡” እና “ከበላይ በስተቀር ተሻለን ያየው አልነበረም” በማለት ደግሞ ተራኪው ይነግረናል (70)፡፡ እነዚህን ነጋሪዎች ይዘን ወደ በላይ ሰብዕና ብንዘልቅ ሃሳባችን ይታሰርልናል፡፡ ይህም ሁለተኛውና የልጅነትና የወጣትነት የዕድገት ደረጃዎችን በማስተያየት የምናገኘው ነው፡፡

የበላይ ሰብዕና “ማኅበራዊ ፍንገጣ” የሚስተዋልበት ነው፡፡ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን አይወጣም፡፡ ማኅበረሰቡ እኩይ የሚላቸውን ድርጊቶች ይፈፅማል፡፡ መጠጥ ያበዛል (69)፡፡ በኪሱ ሲጋራ ይዞ ይዞራል፡፡ ከክፍል አቋርጦ ወጦ ያጨሳል፡፡ ተማሪዎች ሲያጨስ እንዳያዩት ይፈራል (66 እና 68)፡፡ ለተማሪዎቹ አርአያ መሆን አልቻለም፡፡ በእጅጉ ተጠራጣሪም ነው፡፡ ለበላይ ሰዎች ያለመታመን ምሳሌዎች ናቸው፤ *“ሽክላውም እንደሰው ይሸውዳል?”* ሲል እንሰማዋለንና (68-9)፡፡ (ከልጅነት የመከዳትና የመተው ስሜት ጋር እንዲተያይ ልብ ይሏል)፡፡ በተጠራጣሪነቱም “ብቸኝነት”ን ይመርጣል፡፡ እነዚህ ሁሉ ሰብዕናዎች የልጅነት ማኅበረ-ልቡናዊ ዕድገቶችን በሙሉ በ“አፍራሽነት” የጨረሰው ተሻለ የወጣትነትና የጎልማሳነት ተከታታይ ደረጃዎቹም በተመሳሳይ ፈር መሄዳቸውን የሚያስረግጡልን ናቸው፡፡ ስለሆነም በላይ የሚባል ገፀ-ባህሪ የለም፤ ተሻለ እንጂ፡፡ ለዚህም ነው የሥነ ጽሑፍ ጥናት የገፀ-ባህሪ ሳይሆን የአሳሳልና የሃሳብ እንዲሆን የሚጠበቀው፡፡ አሳሳሉን አፍታቶ ትርጉም ማበጀትና “የተዝረከረኩት”ን መሰብሰብ ያሻዋል (Baldick፣2001፣54)፡፡ በጥቅሉ የማኅበረ-ልቡናዊ ዕድገት ደረጃዎች ሃሳቦች በዚች አጭር ልቦለድ የገነኑ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል እነዚህ ሰብዕናዎች (በተለይም ማጨስና መጠጣት) የጨቅላነት “ሳይኮሴክሿል” ማንነት ተራዛሚ ዕድገቶች ናቸው፡፡

### 3.2.2. "ዘላን"፤ የጨቅላነት "ግንትሮሽ" እና የሁለት ሰብዕናዎች መቃየጥ

የአጭር ልቦለዷ ርዕስ በራሱ ጭብጥ ጠሪ ነው፡፡ "ዘላን" የሚለውን ቃል የኢትዮጵያ ጥናት መዝገበ ቃላት፣ "አንድ ቦታ ላይ ቋሚ የሆነ መኖሪያ ቤት የሌለው÷ ለከብቶቹ ሳርና ውሃ ለማግኘት ሲል እንደየወቅቱ ሁኔታ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ የሚኖር ህዝብ፡፡ ተቆጣጣሪና ቋሚ አድርሻ የሌለው÷ በፈለገበት የሚያድር ሰው፡፡" በማለት ያፍታታዋል (1993፣432)፡፡ እዚህ ውስጥ ጉዳዩ "ለማግኘት ሲል" የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡

ተሻለ ከእናቱ የሚለየው በአባቱ መሃከለኛነት አይደለም፡፡ የአባቱን ሚና የምትወስደው እናቱ ናት፡፡ እናቱ የመጀመሪያ የፍትወት ማደሪያ አካል ናት፡፡ ያደገው በእናቱ እንጂ በአባቱ አይደለምና፡፡ እናቱ የአባቱን ሚና እንደወሰደች ትናገራለች፡፡

> "ስንት ጊዜ ልቆጣው……ሴት ኾኜ አጥብቼ አልብሼ ምን ልበል እንደገና <u>እንደ አባት ደብድቤ ነው ያሳደግሁት፡፡</u> ይከብዳል የእኔ እናት" (*ሰለንጋን ምስር*፣29)፡፡ [አጽንኦቱ የእኔ ነው]

ከማኅበረ-ልቡናዊ ሥርዓቶችና ከግብረ ገብ ጋር የምታስተዋውቀው እናቱ ናት፡፡ ከእሷ የምትለየውና ሁለት የተለያዩ አካላት እንደሆኑ የሚያውቀው በእሷ አማካኝነት ነው፡፡ ማኅበራዊ ሚናውን፣ "ባዮሎጂካዊ" ወንድነቱንና ከወንድነቱ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ጉዳዮችን የማስተዋወቅና ከእናት የመለየት ኃላፊነት ግን የአባት ነው፡፡ እናቱ ይህን የአባት ሚና መውሰዷን ስትናገር እንሰማታለን፡፡

> "… ፎቶውን የምሰቅለው ወድጄ መሰለሽ፡፡ <u>ተሻለ አባት እንዳለው እንዲያውቅ</u>፣ እንዳልተደቀለ እንዲያውቅ ብዬ ነበር፡፡" (31) [አጽንኦቱ የእኔ ነው]

ይህ አስረጅ፣ የተሻለ ማኅበራዊ ሚና "ባዮሎጂካዊ" እና "ማኅበራዊ" ፆታን መሠረት ያደረገ እንደሆነ የሚያጠይቅ ነው፡፡ በዚህም "ኦዲፐሳዊ ቅዠት" (Oedipus copmplex) ትኩረት በቴክስቱ ውስጥ አናይም፡፡ "ለምን ቢሉ?" ይህ የጨቅላነት የፀፀትና የሐዘን ስሜት የሚበቅለው፣ ወዲህ ልጆች በ"ባዮሎጂካዊ" ወላጆቻቸው ሲያድጉና አብረው ሲኖሩ፣ ወዲህ ደግሞ ወላጆቻቸው ፆታዊ ግንኙነት ሲያደርጉ የመጋለጥ ዕድል ሲኖራቸው ብቻ ነውና (Bocock፣2002፣40)፡፡ በእነዚህ ሁነቶች መካከል የሚያልፉ

ልጆች በቋንቋ አማካኝነት ማኅበረ-ባህላዊና ግብረ-ገባዊ ስራቶችን በአባታቸው አማካኝነት ስለሚማሩና ከእናታቸው ስለሚለዩ በአባታቸው ላይ በነበራቸው ጥላቻ ይፀፀታሉ፤ ያዝናሉ። ይህም የሚሆነው *ሱፐር ኢጎ* ማኅበረ-ባህላዊና ግብረገባዊ ስራቶችን በልጁ ሰብዕና ውስጥ ሲያፀና ነው። "ኦዲፐሳዊ ቅዠት" የሚፈጠረው በዚህ ወቅት ነው። ተሻለ ግን በዚህ ስርዓት ውስጥ አያልፍም። የአባቱን ሚና ወስዳ እናቱ በተዘዋዋሪ፣ በአባቱ ፎቶ፣ "ዓለሙን" ስታስተዋውቀው እንመለከታለን፤ አባቱ አብሮት አይደለምና። ስለሆነም የተሻለ "ፊክሴሽን" የተፈጠረው በእናቱ የአጸፋ ስልት እንጂ በ"ኦዲፐሳዊ ቅዠት" አይደለም። ይህም በ"Oral stage" ወቅት የተፈጠረ ነው። እናቱ ለአደፍርስ የነበራትን ጥላቻና የበቀል ስሜት ወደ እሱ በማዞሯ የመጀመሪያ የእርካታ ምንጭ (የፍትወት ማደሪያ) የሆነለትን ጡቷን ትከለክዋለች።

> አደፍርስ ያታለላት ትዝ እያላት የወለደችለትን ልጅ ጠላችው። በመንገድ ሲተላለፉ እንደማያውቃት ሁሉ ፊቱን ሲያዞር በብስጭት ተቃጠለች። ተሻለን እንዲህ እያጠባች ስታየው ‹በመድከም› አሳባ ስንቴ ነው ከሚጠባ አፉ ጡትዋን ስባ ያወጣችው? ስንቴስ ነው የጡቶችዋን ጫፎች ግራዋ ጨፍጭፋ ውሃውን የቀባችው። ስንቴ ነው ተሻለ ጨቅላ አፉን ጡት ሊጠባ ወደ ደረትዋ ሲያመጣ ለራስዋና ለእሱም ‹መስሎሻል› ያለችው? ፊቱን ከስክሶ ሲያለቅስስ ከት ብላ አልሳቀችም? (*አለንጋና ምስር*፣41)

ጡቱን የከለከለችው እናቱ በሌሎች ስሜት መጨቆን ደስታን ስለምታገኝ ነው። ተሻለ ደግሞ የዚህ ሰለባ ነው። ተራኪው ይህን ሰለባነቱን በግልፅ፣ "… ምኞቷ ሲደርስላት ኪሳራውን ለምን ልጇ ይክፈል?" ሲል እንሰማዋለን (41)። ስለሆነም የተሻለ የጨቅላነት "ሳይኮሴክሿል" ዕድገት ግንትሮሽ መጥባት ላይ የተመሠረተ ነው። እንደዚህ አይነት ግንትሮሽ በወጣትነትና በጎልማሳነት፣ አንድም መጥባትን የሚጠሩ ሰብዕናዎችን፣ አንድም ኃላፊነትን ለመሸከም ዝግጁ ያለመሆን ስሜትን እንዲያዳብር ያስገድዱታል።

ተሻለ በመጀመሪያው ንዑስ ክፍል እንደጠቆምኩት የጎልማሳነት ሰብዕናው በአራተኛው አጨራረስ ተገልጧል፤ በሌላ ስም። በላይን የምናውቀው በማጨሱና በመጠጣቱ ነው። ሁለቱን የሚያደርጋቸው የመጥባት "ፊክሴሽን"ኡ የሚገኘው ከንፈሩ ላይ በመሆኑ ነው። ይህ እርካታን ከራስ አካል የመፈለግ ወይም በቴዎድሮስ ገብሬ "አፍ" ስጠቀም የ"ራስ

ድሪያ" (Auto-eroticism)[11] ውጤት ነው፡፡ "በላይ" ተራዛሚው የጨቅላነት "ሳይኮሴክሿል" ዕድገት ያስከተለበት የእነዚህ ሰብዕና ባለቤት ነው፡፡ ከላይ እንደጠቆምኩት ጡት ባግባቡ ሳያገኝ ሲቀር እርካታውን ወደ ጣት መጥባት ያዞራል፡፡ እርካታ ስለማያገኝበትም የመጀመሪያው የ"ፊክሴሽን" "ደመ-ነፍሳዊ ቦታ" (erotogenic zone) ከንፈሩ ላይ ይሆናል፡፡ በዚህም በወጣትነት አብዝቶ መጠጣትና ማጨስ በ"ደመ-ነፍሳዊው ቦታ" የራስን ድሪያ መፈፀም ነው፡፡ ሌላው "ስጋዊ" ፍትወትን ማልዘቢያ ከሆኑት የ"auto-eroticism" መገለጫዎች አንዱ "ግብረ-አውናን"[12] ነው (Freud፣1905፣181-2)፡፡ ምናልባት "በላይ" የተቃራኒ ፆታ ጓደኛ የሌለው በዚህ ሰብዕና ወድቆ ይሆን? አይደለም፡፡ ይህ ፍላጎቱ በሌሎች ስቃይ ወደ መደሰት ስሜትና "ዘማዊነት" ስለተቀየረ እንጂ፡፡

> ያልተሰራበት ልጅነት ከተጎዱ ዐይኖች ጀርባ ትለፋለች፡፡ ‹በላነው› ‹ጠጣነው› ‹በዳነው› ከማለት ሌላ ምን ሊል ይችላል? (*ሕለንጋና ምስር*፣67)፡፡

ይህ በተራኪው የተነገረ ያልተሳካ የጨቅላነት "ግንትሮሽ" ያስከተለው የወጣትነት ሰብዕና ነው፡፡ ከመጠጡና ከማጨሱ በተጨማሪ ያበለፀገው "ዘማዊነት" ነው፡፡ "በዳነው" ሲል ከብዙ ሴቶች ጋር ያደረገውን ፍትወት ያመለክታል፡፡ ይህን የሚያስረግጥልን ከታሪኩ አስረጅ ወስደን እንመልከት፡፡

---

[11] ይህ ያልተለመደ ፍትወታዊ ድርጊት ሲሆን "ደመ ነፍሳዊውን"(instinctual) ፍላጎት ወደ ሌሎች ሰዎች የሚመራ ሳይሆን ከራስ አካል እርካታን ማግኘት ወይም "ራስ ድሪያ" ነው (Freud፣1905፣181)፡፡ "eroticism" የሚለው ቃል የተነጠቀው ከግሪክ ሚቶሎጂ ነው፡፡ ኢሮስ (Eros)፣ የጦር አምላክ የሆነው የአሬስ እና የፍቅር አምላኳ የአፍሮዳይት ልጅ ነው፡፡ የሁለቱን ሰብዕና አቃይጦ የተወለደ በመሆኑ "አፍቃሬ-ፍትወት" ነበር፡፡ በአማልክትና በሰዎች ላይ ቀስቱን በመቀሰር በፍቅር እንዲወድቁ አድርጓል፡፡ ባሁኑ ሰዓት "ፍትወታዊ ደመነፍስ"ን (Sexual libido) ያስተማስላል (Manser፣2009፣150-151)፡፡

[12] ይህን ቃል የተገለገልኩት ከቴዎድረሮስ ገብሬ "አፍ" ነጥቄ ነው፡፡ ቴዎድሮስ (2001፣73) በግርጌ ማስታዎሻቸው ቃሉን ስለመጠቀም ሲናገሩ፣ "በራስ ድሪያ ወቅት ከሚከናወኑ ጉዳዮች መሃል አንዱ ዘርን የትም ማፍሰስ ነው፡፡ በዚህ ድርጊቱ የሚታወቀውን አውናንን ወስደን ሚናውን እናስፋውና ዘርን ከማፍሰስ ውጭ ያሉትን የራስ ድሪያ ሂደቶች ጭምር እንዲወክልልን እናድርገው፡፡ እናም ድርጊቱ ‹ግብረ አውናን› ወይም ‹ግብራውናን› ተብሎ ይጠራ፡፡ 'ይሁዳም አውናን፡- ወደ ወንድምህ ሚስት ግባ፣ አግባትም፣ ለወንድምህ ዘርን አቁምለት አለው፡፡ አውናንም ዘሩ ለእሱ እንዳይሆን አወቀ፤ ወደ ወንድሙ ሚስት በገባ ጊዜ ለወንድሙ ዘር እንዳይሰጥ ዘሩን በምድር ያፈስሰው ነበር፡፡ ይህም ሥራው በእግዚአብሔር ዘንድ ክፉ ሆነበት፣ እርሱንም ደግሞ ቀሰፈው' (ዘፍ. 38÷8-10)፡፡" ይላሉ፡፡ እናም ጥምር-ቃሉ ሁሉንም የራስ ድሪያ ሂደቶች የሚወክልልን ከሆነ ከ"masterbation" ይልቅ ለ"auto-eroticism" አቻ የሚሆንልን ይመስለኛል፡፡

> እሱን ያጣጥሉት የነበሩ አስተማሪዎች እንደደከሙ ሁሉ ግድግዳ ተደግፈው መሬት መሬት ያያሉ፡፡ ኢምንት የሆኑ መስሏቸዋል፡፡ <u>የሚያለቅሱ ወጣት ልጃገረዶች አሉ፡፡</u>
>
> <u>*ከአፌ የወጣው ደም እንዴት የሚያምር ቀይ ነው፡፡*</u> (69) [አጽንኦቱ የእኔ ነው፤ *Italics* ከምንጩ]

በዚህ አስረጅ ውስጥ የተደበቀ ስዕላዊ ትረካ አለ፡፡ "የተዘጋ ቤት"፣ "የተዘጋውን ቤት ግድግዳ ተደግፈው የሚተክዙ የድሮ አስተማሪዎቹ፣ ያሁን ባልደረቦቹ"፣ "በተዘጋ ቤት ውስጥ የሚያለቅሱ ልጃገረዶች" እና "ከበላይ አፍ የሚወጣ የሚያምር ቀይ ደም"፡፡ "ደሙ"፣ አንድም ከበላይ አፍ የሚወጣና በሌሎች ስቃይ የመደሰት ስሜት ነው፡፡ ደሙ እንደሚያምርና እንደሚደሰትበት እሱ ይነግረናልና፡፡ አንድም የልጃ ገረዶቹ ድንግልናን የማጣት አካላዊ ፍሰት ነው፤ የብዙ ልጃገረዶች ደም፡፡ ከተጠቀሰው አስረጅ ቀጥሎ ከሚመጣው የታሪኩ ክፍል "እግር" እና "ይሮጣል" የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦችን በመባያነት ወስደን ብንመረምር የተነሳውን ሃሳብ ያጸኑልናል፡፡

> ተሻለ የታለ?
>
> የታለ ተሻለ?
>
> ተሻለ በሩጫ ወደሚሄድበት ይሄዳል፡፡ ጉልበቱ አገጩ እስኪደርስ እግሩን እያነሳ ይሮጣል፡፡ (69)

እግር "ፌቲሻዊ"[13] አካል ነው፡፡ "ይሮጣል" የሚለው ዘይቤያዊ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ከብዙ ሴቶች ጋር ፍትወት የሚፈፅም አባሉን "ተንኾ ነው!"፣ "ይሄዳል!" ወ.ዘ.ተ. በሚሉ አባባሎች ሲገልፅ መስማት የተለመደ ነው፡፡ አንድም ይሄን ቃል በበለጠ "አጽኖ" ለማቅረብ ጥቅም ላይ የዋለ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድም ፍትወታዊነትን የሚገልፀውን ቃል የአገባብም ሆነ የፍቺ ሚና ነጥቆ የመጣና "ዋናውን" (Original) ቃል ወደ "ተወካይነት" ያወረደ ሊሆን ይችላል፡፡ ንቁ ልቡና ከኢ-ንቁ ልቡና ጋር ያለውን "መሰናሰል" የገለጠም ነው፡፡ ይህን የፍቺ ሚናና "ተሰናስሎ" ይዘን ስንጓዝ የበላይን በግብር "ዘማዊነት" ያስረግጥልናል፡፡

---

[13] ፍሮይድ *Fetishism*ን የመጀመሪያዋን የፍትወት ማደሪያ (Sexual object)፣ እናት፣ ምቹ ባልሆነ የእርካታ ማግኛ መተካት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እግር፣ ፀጉር፣ የታላሚዋ ቁራጭ ልብስ ወ.ዘ.ተ. ተተኪዎቹ የፍትወት ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ (Freud፣1905፣153)፡፡

ሌላው በተጓዳኝነት የሚነሳው የጨቅላነትና የወጣትነት ንቁና ኢ-ንቁ ልቡናዊ ርስትን የመጠበቅ ፍላጎት “መቃየጥ” ነው፡፡ ተሻለ አስቀድሞ የራሴ የሚላትን፣ ማኅበረ-ባህላዊ፣ መንፈሳዊና ግብረ-ገባዊ እሴቶች ከዘመድ ጋር የሚኖር ፍትወታዊ ፍላጎትን አይታሰቤ እንደሆነ ካሳወቁት በኋላ ደግሞ የአባቱ የሆነችውን “ርስት”፣ እናቱን፣ ከሌላ ወንድ ሲጠብቅ፣ በፈጠረችውም ግንኙነት ጥላቻን ሲሰንቅ እናስተውላለን፡፡ በተለይም ዳይሬክተሩን የሚጠላቸው የርስት ድንበሩን ስላፈረሱበት ነው፡፡ የሚከተለው አስረጅ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡

*ማስታወቂያ*

1. *የዳይሬክተሩ መላጣ ያስጠላል፡፡ የብርቱካን ውሽማ ናቸው፡፡*
2. *ቲቸር በላይ ሰካራም ናቸው፡፡ የኮታቸው ኪስ ተቀድዶአል፡፡*
3. *የሆም ሩም ቲቸራችን ዐይናቸው በመሸዋረሩ ያስጠላሉ…… (47)*

ከእነዚህ ሶስት ማስታወቂያዎች ውስጥ ተሻለ ጥላቻ ያለበት በሁለቱ ነው፤ በዳይሬክተሩና በሆም ሩም ቲቸሩ ላይ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ለምን እንደሚጠላቸው ምክንያት የሚያቀርበው ግን ለሆም ሩም ቲቸሩ ብቻ ነው፤ ዐይናቸው በመንሸዋረሩ፡፡ ለዳይሬክተሩ ያለው ጥላቻ ግን በምን ምክንያት እንደሆነ አልተገለፀም፡፡ ሁለቱ ተከታትለው የመጡ ዓረፍተ ነገሮችም ቢሆኑ ዝምድና የላቸውም፡፡ ይሁን እንጂ ምክንያት ያላቀረበው በሱፐር ኢጎ ተግዳሮት ይመስላል፡፡ “ለምን ቢሉ?” ማኅበረ-ባህላዊው፣ መንፈሳዊውና ግብረ ገባዊው ስርዓት የሚከለክለው ከዘመድ ጋር የሚኖርን ፍትወት እንጂ ከ“ባዕድ” ጋር የሚደረግን አይደለም፡፡ ስለሆነም በዝምድና አለመኖር ምክንያት የእናቱ እና የዳይሬክተሩ “ፆታዊ ግንኙነት” ይደገፋል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ወዲህ መላጣውን የጠላበት የብርቱካን ውሽማ በመሆናቸው ነው ቢል ማኅበረ-ባህላዊና ግብረ ገባዊ እሴትን ያፈርሳልና አላለም፡፡ ወዲህ ደግሞ ርስትነቷ ለአባቱ በመሆኗና የርስትነት ድንበሩን ስላፈረሰ ጠልቶታል፤ እናቱንም ቢሆን ጠልቷታል፡፡ “እንዴት ቢሉ?” እናትን ባደባባይ ማዋረድ በማኅበረሰቡ ዘንድ የተናቀ ቢሆንም ቅሉ ሲያዋርዳት እንመለከታለን (ውሽማ ይዛለች ብሎ)፡፡ ስለሆነም የዚህ ሥነ ልቡናዊ ቀውስ ለሁለቱ ዓረፍተ ነገሮች አገባባዊ መቃወስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ስለሆነም ባገባባዊ መቃወሱ የኢ-ንቁ ልቡና እስብ መገለጡን ልብ ይሏል፡፡

እናቱ፣ አንድም ማኅበራዊ ቅቡል ያልሆነውን "ውሽማ መያዝ" በመፈፀሟ፣ አንድም ደግሞ ያባቱን ርስት በማፍረሷ ጠልቷታል፤ ከሃዲና የማትታመን አድርጎ ያስባታል፡፡ ይህ ከሃዲነቷ ደግሞ በአንድ ሚታዊ ዘይቤ ታስሮ እንመለከታለን፡፡

*መልመጃ*

*1/ የዩኒቨርሲቲው ዳይሬክተር ለማዳ ውሻ አላቸው*

…. (48)

በዚህ አስረጅ ውስጥ በመባያነት የመጣው ሚታዊ ዘይቤ "ውሻ" ነው፡፡ ውሻ በብሉይና በሐዲስ ፣ በግሪክና በአፍሪካ ሚቶሎጂ የሚታወቀው የማኅበረ-ባህላዊና መንፈሳዊ እሴቶች "አፍራሽ" ድርጊቶች አስተማሳይ ሆኖ ነው፡፡ በበብሉይና በሐዲስ ሚቶሎጂ አስራ ስምንት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ በሁሉም የክህደት፣ የዘማዊነት፣ የርኩሰት፣ የጭካኔ አስተማሳይ ነው፡፡ በኦሪት ዘዳግም (23÷18) እና በኢሳያስ (66÷3) ያለመታመንና የርኩሰት፣ በራዕይ (22÷15) የዘማዊነት፣ በምሳሌ (26÷11) እና በ2ኛ ጴጥሮስ (2÷22) ከስህተት ያለመማርና ወደ ነበረው ስህተት የመመለስ ምሳሌ ሆኗል፡፡ በግሪክ ሚቶሎጂም ከዚህ የተለየ እሳቤን ይዞ አናገኘውም፡፡ ቀናተኛዋን ሔራ ዚየስ "ይሉኝታ የማታውቂ" (Shameless) ሲል "ካንቺ በላይ ውሻን የሚመስል የለም" ብሏታል፡፡ ሔራ በበኩሏ አርጤምስን "የማታፍሪ" ስትል "Brazen dog" ብላ ሰድባታለች፡፡ በ*Odyssey* ሄለን ራሷን "እምነት የለሽ" (Dog-faced) ስትል ተሰምታለች፡፡ ይህንን አጋሜምኖን ለማትታመነው ሚስቱ ክሌምኔስትራ (Clytemnestra) ተጠቅሞበታል፡፡ በኋለኛው የግሪክ ዘመን (ከትሮይ ጦርነት በኋላ) "ውሻ" በሚታዊነቱ "ዘማዊ"(Prostitute) ለሚለው የተመረጠ ቃል ነበር (Ferber፣60)፡፡ በመንዴ(Mende) ኢትዮጵያውያንና በዳጎምባ (Dagomba) ጋናውያን፣ "ውሻ"፣ የዘላለማዊነት መልዕክትን ከሰማዩ አምላክ ለሰዎች ተቀብሎ ሲመጣ በ"አፍቃሬ-ምግብነቱ" ምክንያት ያላደረሰና በሌላ እንስሳ (እንቁራሪቶች ተብሎ ይታሰባል) አስወስዶ መልዕክቱን በሞት የለወጠና የማይታመን ፍጡር ነው (Lynch፣30)፡፡ በአመዛኙ፣ በሀገራችን አንዳንድ ማኅበረሰቦች ውሻ ሲከበር አናስተውልም፡፡ "ውሻ በጅራቷ ትጎዳለች"፣ "ውሻ በጨው አይቀምሳትም"፣ "ውሻ ቀንድ ልታወጣ ሄዳ ጆሮዋን ተቆርጣ ተመለሰች" ወ.ዘ.ተ. የሚሉ የውሻን ክብር ዝቅ የሚያደርጉ ምሳሌያዊ ንግግሮች አሉት፡፡

ብርቱካን ተመስላ የምንመለከታት በ"ውሻ" ነው፡፡ "ውሻ" የሚለው ቃል ደግሞ የተጠቀሱትን ፍቺዎች የሚጠራ ዘይቤ ነው፡፡ ስለሆነም በማኅበረ-ባህላዊውና ግብረ-ገባዊው ስራት የተከበረውን ርስት ያፈረሰች፤ ለባሏ የማትታመን "ዘማዊ" መሆኗን የወከለ ነው፡፡ "ለምን ቢሉ?" ብርቱካን ባል ሳይሆን ውሽማ ነው ያላት፡፡ ይህ ደግሞ፣ በአመዛኙ፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ (በተለይም ቴክስቱ በበቀለበት አዲስ አበባ) እንደ ዘማዊ የሚያሳይ ነው፡፡ ቴክስቱ የጠራውም የውሻ ፍቺ ከላይ የጠቀስኩትን ነው፡፡ ስለሆነም ተሻለ የዚህ ስራት ጠባቂ እንደመሆኑና ለአባቱ ያለው "ቅናት" ርስቱን የደፈረውንና ያስደፈረውን ሲንቅና ሲጠላ እንመለከታለን፡፡ ወዲህም ደግሞ ቅድመ ልሳን ጊዜ እናቱ የመጀመሪያ ታላሚ የፍትወት ማደሪያ (Sexual object) በመሆኗ ኢ-ንቁ ልቡናዊ ቅናቱና ርስት ዕቀባው በራሱ ላይ ያርፋል፡፡ ስለሆነም የሁለቱ ልቡናዎችን ፍላጎት "መቃየጥ" ልብ ይሏል፡፡

### 3.2.2. "አለንጋና ምስር"፤ "Oedipus Complex" እና የልቡና ፍርቅነት

> The Oedipus complex is composed of a child's sexual desire for the parent opposite sex and the related rivalry with and desired death of the parent of the same sex.
>
> (Shannon Sullivan,2004፡198)

አስቀድመን የምናነሳው የ"Oedipus complex"ን እሳቤ ነው፡፡ ስያሜው የተሰጠው የሶፎክለስ "ንጉስ ኦዲፐስ" ከሚለው ትራጀዲ ተወስዶ በፍሮይድ ነው (Freud፣1900፣109)፡፡ በትራጄዲው ውስጥ ኦዲፐስ የቴሲቢያዊው ንጉስ ሌዩስ (Laius) እና የዮካስታ (Jokasta) ልጅ ነው፡፡ ሌዩስ በልጁ እንደሚሞት በነቢይ (Oracle) ይነገረዋል፡፡ በዚህም አባቱ ልጁን ከከተማይቱና ከቤተ-መንግስቱ ርቆ እንዲያድግ ያደርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ ልጁ ካደገ በኋላ ስለማንነቱና ከየትነቱ እርግጠኛ ባለመሆኑ፣ እንደ አባቱ ሁሉ፣ ነብዩን ያማክረዋል፡፡ ይህን ጥያቄውን ቢተው መልካም እንደሆነ፣ ባይተውና ወደሚነግረው የትውልድ ቦታው ቢሄድ ግን ዕጣ ፈንታው አባቱን ገድሎ እናቱን ማግባት እንደሆነ ይነግረዋል፡፡ አንድ ቀን ከቤቱ ወጥቶ ሲጓዝ በመንገድ ላይ ንጉስ ሌዩስን ያገኘውና ድንገተኛ ፀብ ይፈጠራል፡፡ ንጉስ ሌዩስንም ይገለዋል፡፡ በጉዞውም

ወደ ቴሲቢያኖች ምድር ይደርሳል፡፡ የቴሲቢያ ታላላቆችም የጠየቁትን የ“ሲፊክስ” (Sphinx) ወይም የተረት አሞራ (ስለሞቱ ነፍሳት እጣ ፈንታ የሚናገር ነው) እንቆቅልሽ ስለፈታላቸው በጥበቡ ይማረካሉ፡፡ በአባቱ ወንበርም ያስቀምጡታል፤ የካስታንም እጅ መንሻ አድርገው ይሰጡታል፡፡ ከማያውቃት እናቱም ሁለት ሴት እና ሁለት ወንድ ልጆችን ይወልዳል፡፡ ለቴሲቢያኖች ሚስጢሩ በነብዩ አማካኝነት ሲገለጥ ንጉስ ኦዲፐስ በመፀፀት የራሱን አይኖች ነቅሎ ያወጣቸዋል፤ ከከተማይቱም ርቆ ራሱን በግዞት ማኖር ይጀምራል፡፡ እናቱም ራሷን ታጠፋለች፡፡ የኦዲፐስ ተፀፅቶ እናት ሀገሩን መልቀቁና በራሱ ላይ ግብረ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳት ማድረሱ በአማልክትና በሰዎች “ሁሉን የመቻል ፍላጎት” ምክንያት የመጣ ነው፡፡ አንድም ወደ አማልክት ፍላጎት የ“መመለስ” እና ስህተቱ ነው ብሎ ካመነው የመውጣት (Resignation)፣ አንድም ሁሉን የመቻል ኦዲፐሳዊ ፍላጎት ያስከተሉት ልቡናዊ ቀውስ ውጤት ነው፡፡ ዘመነኛ ፀሐፊዎችም በተመሳሳይ ትራጄዲያዊና ሥነ ልቡናዊ ቀውሶች ላይ የተመሠረቱ ታሪኮችን ይፅፋሉ (110)፡፡

በዚህ ንዑስ ክፍል መግቢያ ላይ የጠቀስኩት የሱሊቫን ሃሳብም ይህን ሁነት ከልጆች አንጻር የተነተነ ነው፡፡ ሃሳቡን ወደ አማርኛ ስንገራው “‘Oedipus complex’ በልጆች የተቃራኒ ጾታ ፍትወታዊ ምኞትና ለተቀናቃኙ/ኟ (ተመሳሳይ ጾታ) ሞትን በመናፈቅ/በመመኘት ላይ የሚዳብር ሰብዕና ነው” የሚል ይሆናል፡፡

በምልከታዬ በዚህ አይነት ታሪክ ከተዋቀሩ የአዳም ስራዎች ውስጥ *አለንጋና ምስር* ተጠቃሽ ነው፡፡ በዋና የታሪክ ባለቤትነት የተሳለው ገፀ-ልጅ ፍሬው ነው፡፡ ፍሬውን በሶስት ክፍለን መመልከት እንችላለን፤ ቅድመ፣ ጊዜ እና ድህረ “Oedipus complex” ብለን፡፡

### ሀ. ቅድመ “Oedipus complex”፤

በዚህ ደረጃ ፍሬው በእናቱና በእሱ መካከል ልዩነት እንደሌለና አንድ እንደሆኑ ሲያስብ እንመለከታለን፡፡ የአንድነት ምንጭ የሆኑት ደግሞ የእናቱ ጡትና የእሱ አፍ ናቸው፡፡

> ስምዋ ‹‹ሉል›› የተባለ --- <u>አፍ መሃልና ምላስ ላይ እንደረጠበ ከረሜላ የሚልወሰወሱ፣ የሚያዳልጡ</u> *ፊደላት ያሉት ስም* <u>ያላት እናት ባለቤት እኔ ብቻ ነኝ</u> (አለንጋና ምስር፣ 171)፡፡ [አጽንኦት የራሴ]

በከረሜላ የተመሰለው የእናት ጡት ነው፡፡ የእሱ የእርካታ ምንጭም መጥባት ነው፡፡ ህፃኑ በአፉ፣ እናቱ ደግሞ በጡቶቿ አንድ ይሆናሉ፡፡ ፍሬውም እሱና እናቱ አንድ እንደሆኑ፣ ብቸኛ የእርካታ ምንጩ እንደሆነች፣ ይህቺ የእርካታ ምንጩም ከእሱ አካል የተለየች ሌላ ፍጡር እንዳልሆነች ይገነዘባል፡፡ እርካታው ከመጥባቱ ጋር ፍቅሩም እንዲሁ ይጠነሰሳል፤ "It was the child's first and most vital activity, his sucking at his mother's breast, or at substitutes for it, that must have familiarized him with [first] pleasure (Freud, 1905፡181).

ስለሆነም አፍ/ከንፈር የፍሬው "የፍትወታዊ ደመ-ነፍስ ብልት" ነው፡፡ ከረሜላው ተጨማሪ ጉዳይን እንዲያስተማስል የተመረጠ ይመስላል፡፡ ይህም ቀጣይ "እጣ ፈንታን" ነው፡፡ ከረሜላ ተመጥምጦ እንደሚያልቅ ሁሉ ይህ የእርካታ ምንጭ (ጡት) ቀጣይነት እንደሌለው የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም የፍሬው የመጀመሪያ የፍትወት ማደሪያ የነበረችው እናት ሌላ አካል (Other) እንደሆነች ወደ 'ሚገነዘብበት ደረጃ ይሸጋገራል፡፡

### ለ. ጊዜ "Oedipus complex"፤

ይህ ጊዜ በፍሮይድ ከ"Pleasure Principle" ወደ "Reality Principle"፣ በላካን ደግሞ ወደ "Symbolic Order" መሸጋገር ነው፡፡ በዚህ ደረጃ አዲስ አካል በእናትና ልጅ መካከል ይገባል፡፡ እሱም አባቱ ነው፡፡ አባት የማኅበረ-ባህላዊ ስራቱ ወካይ (agent) ሆኖ ብቅ ይላል፡፡ ለልጁ የማኅበረሰቡን ባህላዊና መንፈሳዊ ህግጋት እንዲያውቅ ያደርገዋል፡፡ ከእናቱ ይለየዋል፡፡

> The father, who comes between mother and child, represents culture and law. He enables the child to enter the Oedipus complex and detach himself/herself from the mother as an object, in order to build his or her own separate subjectivity. (Golan,1979,8)

የፍሬው አባት ልጁን ወደ "ጊዜ ልሳን" ካሸጋገረ በኋላ መጀመሪያ የወሰደው በሀገራችን ልማድ ኃይማኖታዊና ባህላዊ ትምህርቶች በአንድነት ወደሚሰጡበት የቤተ ክህነት ትምህርት ቤት ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት የኃይማኖት ህግጋት፣ ማኅበራዊ ኃላፊነትን ስለመወጣትና ሌሎች ባህላዊ ስራቶችን ይማራል፡፡ አድርግ/ አታድርግ፣ እናት/አባት፣

ጽድቅ/ኩነኔ፣ ባል/ሚስት … የኃይማኖታዊና ማኅበረ-ባህላዊ ስራቶች መቆሚያ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ውስጥ ፍሬው ሚናውን ይለያል፡፡ በዚህም በመጀመሪያው ማንነቱ(እኔና እናቴ አንድ ነን የሚለውና የእርካታ ምንጩ እሷ ብቻ እንደነበረች የሚያስብበት) እና አዲስ በሚተዋወቀው ዓለም መካከል በሚፈጥረው ግንዛቤ ምክንያት ልቡናዊ ቀውስ ይፈጠርበታል፤ ይህም ቀውስ የልቡና ፍርቅነት (Spliting of the ego) ነው፡፡

> ከባልዋ ጋር ተቀምጣ የምትደባብስ እናት ያለኝ እኔ ብቻ ነበርኩ፡፡ ጠይምነትዋ የበግ ጥብስ የመሰለ፣ በመንገድ ላይ ጎረምሳ ገላምጦ የሚያያት(‹‹የፍሬው እናት ደስ ይላሉ አይደል?››) የምትባል የእኔ እናት ብቻ ናት፡፡ (*አለንጋና ምስር*፣171) [አጽንኦቱ የእኔ ነው]

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሁለት ሰብዕናዎችን እንመለከታለን፡፡ አንደኛው የመጀመሪያው አጽንኦት ያረፈበት ነው፡፡ ታሪኩ የቀረበው በኃላፊ ጊዜ የመሆንና የመኖር ግስ "ነበርኩ" በሚለው ነው፡፡ የቀደመው ጊዜ ሰብዕናው አብሮት እንዳለ የሚያጠይቅ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በተከታዩ አጽንኦት የምናስተውለው እሱና እናቱ ሁለት የተለያዩ አካላት እንደሆኑ መገንዘቡን አንድም ከአንደኛ መደብ ወደ ሶስተኛ መደብ በመቀየር፣ አንድም ያሁን ጊዜ የመሆን ግስ "ናት"ን በመጠቀም ሲናገር፣ አንድም ቦታው የአባቱ እንደነበር መረዳቱን በመጀመሪያው አጽንኦት "ከባልዋ ጋር ተቀምጣ የምትደባብስ እናት" ሲል እንሰማዋለን፡፡ በዚህ ቅፅበት ፍሬው የ"ማጣት" (Lack)[14] ስሜትን ያዳብራል፡፡ ይህን

[14] የላካናዊያን ጽንሰ ሃሳብ ሲሆን ጨቅላው ወደ "ጊዜ-ልሳን"(Symbolic Order) ሲሸጋገር የሚከሰት ነው፡፡ ጨቅላው አስቀድሞ እናቱና እሱ አንድ እንደሆኑና ልዩነት እንደሌለ(mother-child unity/wholness) ያስባል፡፡ ይህን ደረጃና ማንነት *The Real/Need* ይሉታል፡፡ ሙሉ በሙሉ "ባዮሎጂካዊ" ማንነት ነው፡፡ ከዚህ የዕድገት ደረጃ ቀጥሎ የሚመጣው *Imaginary* ነው፡፡ ከዚህ ደረጃ ቀጥሎ አባት እናቱንና ጨቅላውን በማለያየት ወደ "ጊዜ-ልሳን" ያሸጋግረዋል፤ ሰብዕናውም በእናቱ "መኖር-አለመኖር"(Presence-Absence) ላይ ይወድቃል፡፡ በዚህ ቅፅበት ጨቅላው ከመጀመሪያ የፍትወት ማደሪያውና የእርካታ ምንጩ በመነጠሉ የ"ማጣት" ስሜትን ያዳብራል፡፡ ይህ የ"ማጣት" ስሜት ደግሞ ለሁሉም አይነት ምኞቶች(Desire) ምንጭ ይሆናል፡፡ የጨቅላው የማጣት ስሜት በሦስት "ቅጦች"(Modes) ህያው ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው ፍርሃት(Frustration) ነው፡፡ ጨቅላው እናቱ የ"ወንዴ ብልት" (Penis) እንደሌላት ሲያውቅ የሚደነግጥበትና አማራጭ የእርካታ ምንጭ እንደሌለ የሚያስብበት ነው፡፡ ሁለተኛው "ግላዊነት"(Privation) ሲሆን ባዮሎጂካዊ ማንነትን የማጣት ስሜት ነው፡፡ የቀደመው የ"እናት-ጨቅላ" አንድነት ስለማይኖር እሷን የማጣት ቅዠት ነው፡፡ ሦስተኛው *Castration* ሲሆን ማጣቱን ከአይታሰቤ ጋር የሚያቆራኝበት ነው፡፡ ይህንም በሚከተለው የተሰናዳ ቀመር መጠቅለል ይቻላል፡፡ *Jouissance*$_1$-*Symbolic -Jouissance*$_2$ ፡፡ $J_1$ በጨቅላው እና እናቱ መካከል ጣልቃ የሚገባ አካል የሌለበትና ጨቅላው እንደ "wholeness" የሚያስብበት ነው፡፡ $J_2$ በአይታሰቤ አማካኝነት የተከለከለችውን እናቱን ምናባዊ ምስል ሰጥቶ የሚደሰትበት (Fantasize የሚያደርግበት) ነው፡፡ ስለሆነም ማኅበረ-ልቡናዊና ግብረ-ገባዊ እሴቶች ይህን በራስ ስቃይ የመደሰት (Masochism)ና የመጀመሪያ የእርካታ ምንጭ የነፈገችውን ለመበቀል ሲባል

ማንነት የፈጠረበት አባቱን እና መሠሎቹን ይጠላቸዋል፤ ይቀናባቸዋል፡፡ በጎረምሶቹና በዶርዜው ሸማኔ ላይ የሚያንፀባርቀውን የቅናት ስሜት ልብ ይሏል፡፡

> እናቴ የተነገረለት ታላቅ ቀሚስ አላት እዛው በሰፈራችን አንድ የዶርዜ ሸማኔ የተሰራ፡፡ ... እሱና አንዳንድ የነበሩ እንደሚናገሩት ከኾነ ትልቅ የዕረፍት ዳንሱን የደነሰው የእናቴን ቀሚስ መገንቢያ ሰርቶ የጨረሰ ዕለት ነው፡፡
>
> "ታዲያስ ወይዘሮ ሉል እንዴት አደረጉህ?" ሲሉት
>
> "የእሳቸውን መስራት ስምንተኛ ሚኒስትሪ እንደመፈተን በለው፡፡ መከራ ነው"
>
> ለዚህ ሳይሆን ይቀራል ብዙ ልጆች በእናቶቻቸው ላይ ሸፍተው እንዳፈለጋቸው ሲሆኑ በእናቴ ስሜት የምገዛው? ማለቴ የቀሚስዋ ሽብሽብ በመብዛቱ እሱን ፈልፍዬ ወደ ውጭ ፀሐይና ብርሃንን፣ ጨረቃና ከዋክብትን የመሳሰሉ ነገሮችን በራሴ ዓይኖች ለማየት ያዳገተኝ?... እና የዚያ የምስር ወጥ ጠረን፡፡ (172)

[አጽንኦቱ የእኔ ነው]

እዚህ ውስጥ አንድ ነገር አተኩሬ አነሳለሁ፤ ስለ "ቀሚሱ"፡፡ ቀሚስ ምንድን ነው? ማኅበረ ባህላዊ ትዕምርትነቱስ? ፍሬው ከቀሚሱ ውስጥ ለመውጣት የተቸገረው ለምንድን ነው? ፍካሬ ልቡናዊ ትዕምርትነቱስ ምን ይሆን? አበው "በጀግኜ" ግጥሞቻቸው ሲፎክሩ እንዲህ አሉ!

ልከህ ስደደኝ ዳገት ለዳገት

ይገፎው ልመለስ ቀሚሱን ከማጀት[15]

ቴክስቱ በሚጠራው ማኅበረሰብ ውስጥ "ቀሚስ" የሚስት ትዕምርት ነው፡፡ "አባዊ ስርዓት"ን በሚከተል በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ "ማጀት" የ"ሴት ስራ" የሚከናወንበት፣ ለ"ሴቶች" የቆመ ትዕምርት ነው፡፡ በፉከራው የተላለፈውም መልዕክት የባልን ልብስ ሳይሆን "ሚስቱን" በጀግንነቱ ልውሰድበት የሚል ነው፡፡ "ቀሚስ" የሴትነት መገለጫ

---

የሚደረግን በሌላ ስቃይ የመደሰት ስሜት(Sadism) ስለሚቃወም ጨቅላው ሌላ የእርካታ ምንጩን ለመተካት ይናውዛል፡፡ ይህም *Desire = Need — Demand* የሚለውን ቀመር ይሰጠናል (Fink1995፣54-60፤ Golan፣59)፡፡

[15] በጎጃምና በጎንደር፡፡

ነው፡፡ ግብሩ አንድም የተፈጥሯዊ ሴቴነትን፣ አንድም ማኅበረሰቡ ባበጀው ሥርዓት የበታቾነትን መግለጥ፣መስበክ፣ መዘመር ነው፡፡ በዚህ አገባቡ ደግሞ የ"ሴትነት" ስጦታዋን መውሰድ፣ "ሴትነቷን መስራት" የሚል ፍቺ አለው፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ ቃሉን ካፍታታባቸው አንዱ፣ "በቅዳሴ ጊዜ ከሌሎች ዲያቆናት ይልቅ ዋናውን የመሪነት ቦታ ይዞ የሚቀድሰው ዲያቆን (ገባሬ ሰናይ ዲያቆን)" ይላል (167)፡፡

ስለሆነም የቀሚሱ ትዕምርትነት ሥነ ልቡናዊ እይታ አንድም ከሁሉም በላይ የእናቱ ባለርስት የሆነው አባቱን ያስተማስላል፤ እንደ ዲያቆኑ ሁሉ፡፡ አንድም እንደ ባህሉ ሁሉ ቀሚስ ሚስትነትን ያስተማስላል፡፡ "ለምን ቢሉ?" "እናቴ የተነገረለት ታላቅ ቀሚስ አላት" ሲል በትዕምርታዊነት ቀሚስ የወንድ ባለርስትነትን ከጠቆመና ባለርስቱ አባቱ ከሆነ ፍሬው እናቱ አባቱን እንዴት እንደገለፀችው ሲናገር የምንሰማበት የታሪኩ ክፍል፣ "ከዘመቻ እንደመጣ አባቴን ስታየው እናቴ ያኔ ባለትዳር ናት ጎምላላነቱ ማርኮአት ትዳሯን ትታ ቤቱ ገባች" ይላልና (*ለ ሰዓንጋና ምስር*፣176)፡፡ የ"ቀሚሱ ታላቅነት" ከ"አባቱ ጎምላላነት" ጋር እንደሚዛመድ ልብ ይሏል፡፡

ስለሆነም፣ ወዲህ ከዚህ ያባቱ ከሆነው ርስት መውጣት አለመቻሉና ቦታው በአባቱ መያዙ፣ ወዲህ ደግሞ አዲስ በተዋወቀው ዓለም ምክንያት፣ ፍሬው፣ አንድም የመጀመሪያ የፍቅሩና የፍትወቱ ማደሪያ የሆነችውን ርስቱን ከእሱ ጋር ለማቆየት፣ አንድም ይህ ስራ በማኅበረሰቡ ዘንድ አይታሰቤ ነው በሚለው አዲስ ሰብዕናው መካከል በሚፈጠር ፀፀትና ሐዘን ሥነ ልቡናዊ ግጭት ሲፈጠርበት እንመለከታለን፡፡ በዚህም ምክንያት የልቡና ፍርቅነት ይፈጠርበታል፡፡ አስቀድሞ የነበረው ማንነት በሚይዘው ጠንካራ አቋም ምክንያት "Melancholic Ego"ን ያዳብራል፡፡ የ"ፋንታሲ" ሰብዕና ባለቤት ያደርገዋል፡፡ ይህ ሰብዕና፣ "Melancholic Ego"፣ አንድም በራሱ ላይ ስቃይን በመናፈቅና በማድረግ፣ አንድም ለእናቱ ኃሳባዊ ምስል (Ideal Image) በመስጠት መደሰት፣ አንድም ያጣውን የሚሞላለት መመኘት ነው፡፡

> Freud's claim that melancholia is a sadistic expression of revenge against a lost object will hence also be certainly interogated [...] first, that in melancholia a strong attachment to an object is transformed in to an identification with the

> object on the part of the ego; and second, that the ego is there up on beset by the super ego, which assails, berates and fortunes it. Revenge, in other words, takes the form of an attack on the ego that now, through identification, has come to resemble the lost object, with the latter the proper target (Zakin,78).

ዛኪን የፍሮይድን ሃሳብ ባብራሩበት በዚህ ጥቅስ ውስጥ፣ "melancholia" የመጀመሪያዋን የፍትወት ማደሪያ አካል የመበቀል ምኞትና በዚህም የመርካት ደስታ ነው። በቀሉ በኢጎ ላይ የሚቃጣና በእናት ምኞት ላይ የሚመሰረት በመሆኑ ከሌላ የሰብዕና መዋቅር (ሱፐር ኢጎ) ወቀሳ ይደርስበታል። በዚህም ያጣትን የመጀመሪያ የፍትወት ማደሪያ ተመሳሳይ "ተፈጥሯዊ"ና ማኅበራዊ ሚና ባላት የፍትወት ማደሪያ ይቀይራል። የመጀመሪያዋን የፍትወት ማደሪያ ማጣት እኔነትን የማጣት ልቡናዊ ቀውስ ይፈጥራል። ስለሆነም ሰብዕናው በ"ምናባዊ ምኞት" (fantasy) የተሞላና ምኞቱም ከላይ የጠቀስኳቸውን ፍላጎቶች በመፈፀምና በመመኘት (በራስ ላይ ስቃይን መናፈቅና ማድረግ፣ ለእናት ኃሳባዊ ምስል (Ideal Image) በመስጠት መደሰት፣ ያጣውን የሚሞላለት መመኘት) ላይ የሚዳብር ይሆናል። ይሁን እንጂ ከዚህ የሰብዕና አይነት ለማውጣት የሚተጋ ሌላ የሰብዕና መዋቅር አብሮ ይዳብራል፤ ሱፐር ኢጐ፡

## ሐ. ድኅረ "Oedipus complex"፤ ቀይ ባህርን መሻገር[16]

ሱፐር ኢጎ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ስራቶችና እሴቶች እንዲከበሩ የሚተጋ የሰብዕና መዋቅር እንደመሆኑ በራስ ላይ የሚደረግን ስቃይና በእናቱ ኃሳባዊ ምስል መናወዝን፣ ከእነዚህም እርካታ መፈለግን፣ ይቃወማል። እናቱ "የተከለከለች" ተፈላጊ ናትና። ስለሆነም፣ ይህ የሰብዕና መዋቅር ሌላ ዘዴ በማምጣት የልቡና ፍርቅነትን ይታደጋል፤ "melancholia"ን ወደ ጥልቁ የልቡና ክፍል በመግፋት ከሰርካዊነቱ ይጋርዳል። ይህ ይዞት የሚመጣው ዘዴ ለባህሉ፣ ለማኅበራዊ ስርዓቶች እንዲሁም ለመንፈሳዊ ልዕልና

---

[16] እስራኤላውያን ቀይ ባህርን ሲሻገሩ፣ አንድም ከኋላቸው የተከተሏቸውን ፈርኦናውያን በረዳቸው እግዚአብሔርና በመሪያቸው ሙሴ አማካኝነት ባህር ውስጥ ጥለዋቸዋል። አንድም ከተሻገሩ በኋላ ወደ ኋላ እንዳያስቡና እንዳይመለሱ ቀይ ባህር ወደ ነበረበት ቦታ ተመልሶ ተጋርዶባቸዋል (ዘፀአት፣14÷11-31።) ይህ አስተማስሎ በዚህ ቴክስት "ስናዘልቀው" በአባቱ መሪነት ከአይታሰቤና ፀረ-ማኅበረ-ባህላዊ የሆኑ እስቦች ከፍሬው ንቃተ ልቡና ተሰውረው ወደ ኢ-ንቁ ልቡና መሄዳቸውንና በ"censorship" መጋረዳቸውን ልብ ይሏል። በየኔታም መሪነት።

የሚቆሙ ጉዳዮችን ለግፊቱ ማምለጫ እንዲውሉ ማድረግ ነው (101)፡፡ ስለሆነም አዲስ ተኪዎችን መለየት ዋና ተግባሩ ነው፡፡ ይህ አዲስ ሰብዕና እና የግንባታ ሒደት ጨቅላውን ባለፈው ማንነቱ ተፀፅቶና አዝኖ ማኅበረ-ባህላዊና ግብረ-ገባዊ ስራቶች በሚፈቅዱት ላይ ሰብዕናውን እንዲመስርት የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ አዲስ የሰብዕና መዋቅር በሐዘንና በፀፀት ላይ በመመስረቱም "mourning Ego" ይባላል፡፡ Zakin እንደሚያስረዱት፣ ይህ ኢጎ ከ"ዓለሙ" ጋር አዲስ ግንኙነት የመፍጠርና ያጣውን ማኅበራዊ ቅቡል በሆኑ ጉዳዮች የመተካት ሒደት ነው፡፡

> Mourning inaugurates a psychic activity intent on working through the loss in order to reestablish a relation to the world of others; through a process of hyper cathexis and detachment the libido arduously labors until it has withdrawn its libidinal cathexes and freed itself from object, there by reestablishing a coherent ego identity capable of interacting in and with the world (83).

ስለሆነም ይህ አይነቱ ማኅበራዊ ቅቡል የሆነ፣ ጤናማና ልቡናዊ መረበሽ የሌለበት የመጀመሪያ የፍትወት ማደሪያን በሌላ የመቀየር አቅም ሲኖረው፣ ልጁ ማኅበራዊነትና የተረጋጋ ልቡናዊ ማንነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

ፍሬው ካለበት የ"melancholic ego" ወጥቶ እንመለከታለን፡፡ ወዲህ የእናቱን ምትክ መንበረን ሲወዳጅ፣ ወዲህ ደግሞ ማኅበራዊነታቸው ከፍ ወዳሉ ስራዎች ያስቀይሳል (sublimate[17] ያደርጋል)፤ ትምህርትና ኳስ ጨዋታ፡፡ ፍሬው እንደሚነግረን (*አለንጋና ምስር*፣179-80)፣ ከመንበረ እና ሌሎች አስር ጓደኞቹ ጋር ቀበና አጋም ሲለቅሙ ከዋሉ በኋላ እነሱ በማያውቁት ሁኔታ እሱና መንበረ ወደ ኋላ ይቀራሉ፡፡ ድሪያቸውንም ያለ ኃፍረት ይፈፅማሉ፡፡ ምንም እንኳ ተተኪ ያላትን ቢያገኝም በኢ-ንቁ ልቡናው ውስጥ የተሰወረው ፍላጎቱና ማጣቱ ሁለቱ ፍተወታዊ ፍላጎታቸውን በሚከውኑበት ቅፅበት በተምሳሌት ሆኖ ብቅ ይላል፡፡ "ጎናችን አንድ የተረገመች ላም ጥላው የሄደች ገና ትኩስ የሚጤስ እበት አለ --- እሱ እዛ ጋ ነው፡፡ ዛሬ ትዝ ይለኛል፡፡ ለመደራረግ እየለፋን

[17] "ደመ-ነፍሳዊ" (instinctual) ግፊቶችን ከንቁ ፍትወታዊ ዓላማቸው ማኅበረ-ባህላዊ ልሂቅና ወዳላቸው ኩነቶችና ድርጊቶች የመለወጥ ሂደት ነው፡፡ የሚለወጡት ግን ግፊቶች (Drives) ሳይሆኑ ፍትወታዊ ዓላማዎች (Sexual Objectives) ናቸው (Golan፣141)፡፡ *Terry Eagleton*ም የተጨቆኑ ፍላጎቶችን ለመበቀል የሚደረግ እርካታን የማላቅ [እብደት] እንደሆነ አትተዋል (2008፣132)፡፡

ነበር፡፡" (180)፡፡ ያቺን የመጀመሪያውን የፍትወት ማደሪያውን አካል ያስባታል፡፡ "ዛሬ" ሲል "በሚደራረግበት" ቅፅበት ያለውን ጊዜ ነው፡፡ "ጥላው የሄደችው ገና ትኩስ የሚጤስ እበት" ሲል ያልነጠፈ፣ ተደብቆ የሚብላላና ለመፈንዳት የሚናፍቅ ምኞቱን፣ "የተረገመች" ሲል ላጣት አካል ያለውን ኦዲፐሳዊ ጥላቻና በቀል የሚገልጽ ነው፡፡

የፍሬው የ"Oedipus copmplex" "ፊክሴሽን" ከሚገለፅባቸው ማኅበራዊ ቅቡል ጉዳዮች አንዱ "ኳስ አበደች" መጫወት ነው፡፡ ኳስን መጠለዝ እጅግ የሚደሰትበት ነገር ነው፡፡ "ለእኔ በመልካም አመታት በእግር ከተጠለዘች ኳስ የበለጠ የሚያምር ነገር አልነበረም" (180)፡፡ በፍሮይድ መከራከሪያ እግር የመጀመሪያ የፍትወት ማደሪያ አካል ተተኪ ነው (1905፣153)፡፡ ፍሮይድ እንደሚሉት ከእስቦችና ንግግሮች ጋር ትዕምርቶችን አዛምዶ "ፊክሴሽን" ያስከተለውን ፍትወታዊ አካል መመርመር የተሻለ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ትዕምርታዊ የኢ-ንቁ ልቡና እስቦች ሲገለጡ እንኳ ግለሰቡ ራሱ አያውቅም፡፡ በተለይም የእግር "ፌቲሽነት" ሚታዊነት እንዳለውና በልበ ሙሉነት መመርመር የሚያስችል እንደሆነ ይመክራሉ (ዝኒ ከማሁ)፡፡ ኳስን በእግር ከመጠለዝም ባሻገር፣ ፍሬው እግሩ የፍትወታዊ ፍላጎቱ ማንፀባረቂያ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ "መሬት በእግሬ እየመታሁ ቀርባ እንዳታናግረኝ ልርቅ እዳዳለሁ" (*ሰለንጋና ምስር*፣182)፡፡ መሬት በእግር መምታት ምንድን ነው? ይህ ድርጊት ከላይ እንዳልኩት "ፌቲሻዊ"አዊ ነው፡፡ ኪዳነወልድ ክፍሌ "መሬት"ን ምድር በሚል አምድ ስር "የቦታ፡ የርስት፡ የመንግስት፡ ክፍለ፡ ሀገር፡... የሰው፡ ባህርይ፣ ስጋ፡ ዐፈር፡ መሬት..." በማለት ያፍታታሉ (1948፣578)፡፡ "መሬት" በሁሉን ቻይነቷ እናት ትመስልባታለች፤ ብዙውን ጊዜም በእንስት ጾታ ትጠራለች፡፡ የፍሬው መሬትን መምታት፣ አንድም ፍትወታዊ እርካታን ማግኛ ኢ-ንቁ ልቡናዊ ግፊት፣ አንድም ወደ ጥልቁ የልቡና ክፍል የተወረወረው ድብቅ ፍላጎት በሱፐር ኢጎ ላይ ያስቀረው የጥላቻና የቅናት ስሜትን እንዲሁም በቀልን የመግለጥ፣ በሰዎች ስቃይ የመደሰት፣ የአጻፋ ስልት ነው፡፡ ስለሆነም "መሬት" የ"አባዊ ዘይቤ" (Paternal Metaphor) ሚናን ይዛ የገባች ቃል ናት፤ የፍሬውን የ"እናት ምኞት" (mother desire) ለመወከል የመጣች፡፡ ለዚህ ጉዳይ ላካን (በFink፣1995፣54-56 እና Thom፣67 ውስጥ እንደተብራራው) የሚከተለውን ቀመር አሰናድተውለታል፡፡

$$\frac{\text{Name-of-the-Father}}{\text{Desire of the Mother}}$$

ይህ ቀመር የ“Signifying Chain” ጣጣ ነው። “አባዊ ህግጋትን” (Name-of-the-Father)ን “$S_2$” እናትን መመኘት (Mother’s Desire)ን ደግሞ “$S_1$” ብለው ሲያስረዱ፣ የፍቺ ሚናው የሚወድቀው በ“$S_2$” ላይ እንደሆነ በመሞገት ነው። “$S_2$” የ“አባዊነት” (Paternal) ፋይዳ ይዞ ቢመጣም ቅሉ ጠሪው ግን የኢ-ንቁ ልቡና ምኞት የሆነው “$S_1$” ነው፤ ከሰርካዊነቱ ይልቅ ትርጉሙ በ“ሜታፈርነቱ” ላይ ይወድቃልና። “$S_1$” ሐራም በመሆኑም የሚገለጠው በ“$S_2$” ተወክሎ ነው። ስለሆነም በዚህ ታሪክ ውስጥ “መሬት” በሰርካዊ ፍቺዋ የገባች አይደለችም፤ የፍሬውን እናት ወክላ የመጣች እንጂ።

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በማሕሌት እና አለንጋና ምስር "ልጅነት" እንዴት ባሉ ሥነ ልቡናዊ እሳቤዎችና ኪናዊ እሴቶች እንደምን ተደርጎ እንደተቀረፀ ለማሳየት ሙከራ የተደረገበት ነው። ከሁለቱ መድበሎች ውስጥ የተመረጡ አራት አጫጭር ልቦለዶች ርዕሰ ጉዳዮች ተበጅተውላቸው ተተንትነዋል። የ"ልጅነት" ጉዳይ በ"ማሞ" እና "ስለ ድልድዩ ልጅ ትዝታ" በአሳዳጊዎች ሚና ላይ የተመሰረተ ሲሆን ያልተረጋጋ የእኔነት ስሜት እና ራስን ከሌሎች አሳንሶ ማየት በጭብጥነት የተነሱ ናቸው። ፍርሃት፣ መጠራጠር፣ ትጋተ ቢስነት፣ በራስ አለመተማመን፣ ተስፋ ማጣት፣ "ጭፍንነት" እና ጥቅል ፍረጃ ተደጋግመው የተነሱ ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው። ወንዝ፣ ሐይቅ፣ ነጭ፣ ጥቁር፣ ወፍ፣ ቁራ፣ ዳክዬ፣ ተራራ፣ ነፋስና ቢራቢሮ ከልዩ ልዩ ሚቶሎጂዎች ተቀድተው ለጭብጥ ማበልፀጊያነት ውለዋል። የልጅነት ማንነቶችም በእነዚህ ሚታዊና ባህላዊ መባያዎች ሰልተው፤ ለትልም ማዋቀሪያነት አገልግለዋል።

ከአለንጋና ምስር በተመረጡት ተረኮች ውስጥ "ልጅነት" የ"ደመ-ነፍሳዊ" ማንነቶችና የማኅበረ-ባህላዊ ሥርዓቶች "መጎራበቻ" ሆኗል። "ዘላን"ን ለመፈተሽ፣ "'ልጅነት'፤ ማኅበረ-ልቡናዊ ፍንገጣ እና የ*sadistic displacement* ማደሪያ" እና "'ዘላን'፤ የጨቅላነት ግንትሮሽና የሁለት ሰብዕናዎች መቃየጥ" የሚሉ ርዕሶች ተበጅተዋል። ልጅ ሆኖ የተሳለው ገፀ-ባህሪ የወላጅ የ"ልቡና" መታወክና ኢ-ንቁ ልቡናዊ ግፊት የአጸፋ ታላሚ በመሆኑ የመተው/የመጣል ፍራትን እና የመከዳት ፍራትን እንዳዳበረ ተመልክቷል። ይህም ማኅበራዊ ሚናውን የሚወጣ እንዳልሆነና እንደማይሆን ደግሞ በ"ፀሐይ መጥለቅ" ተመስሎ እንደቀረበ ተመልክቷል። ስለሆነም "መጥፎ-ዕድል"ና ማኅበራዊ-ፍንገጣ (መጠጣትና ማጨስ) በልጅነት የተመሰረቱና ወደ ወጣትነትና ጎልማሳነት የተራዘሙ ሰብዕናዎች እንደሆኑም ውይይት ተደርጎባቸዋል።

የጨቅላነት "ሳይኮሴክሷል" ዕድገት ጽንሰ ሃሳቦች በግልፅ የተመለከቱበት ተረክ እንደሆነም ተተንትኗል። ለዋና ገፀ-ባህሪው፣ ተሻለ፣ የእናቱ በእሱ ስቃ መደሰት ለ"ፊክሴሽን"ኡ መንስኤው ሲሆንም ተመልክተናል። ግንትሮሹ መጥባት ላይ የተመሰረተ

እንደሆነና በዚህም “የራስ ድሪያ አካሉ”ም ከንፈሩ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ በቀሪ ህይወቱም ድሪያዎቹን ከከንፈሮቹ ሲፈልግ እንደምንመለከትና ይህን ድሪያ ለማሳካት ማኅበራዊ-ፍንገጣ በማድረግ እንደሚያጨስና እንደሚጠጣ ተተንትኗል፡፡ ግንትሮሹ ያስከተለበት ራስ ድሪያም ብቻ ሳይሆን በሌሎች ስቃይ መደሰት ነው፡፡ በሌላ በኩል የእናቱን የ“ሴትነት” ድንበር የሚያፈርሱትን ሲጠላ እንመለከታለን፡፡ ይህም በሁለት መልኩ የመጣ እንደሆነ፣ አንድም የእሱ የመጀመሪያ የፍትወት ማደሪያ በመሆኗ ምክንያት ከኢድ በሚመጣ ግፊት፣ አንድም ወደ ማኅበራዊው ስራት ሲሸጋገር ያወቃትን የአባቱን ርስት የመጠበቅ ንቃት ነው፡፡ ሁለቱም ግን ድንበር ተበጅቶላቸው የመጡ ሳይሆን ባንድ ላይ ተዋህደው የተከሰቱ ናቸው፡፡

በመጨረሻው ክፍል “አለንጋና ምስር”ን ለመተንተን የሞከርኩ ሲሆን ዋና ገፀ-ባህሪው፣ ፍሬው፣ በ“Oedipus complex” ፍሮይዳዊ እስብ ላይ ተመስርቶ እንደተሳለና በታሪኩ ውስጥ ቅድመ፣ ጊዜ እና ድኅረ “Oedipus complex” እስቦች እንደሚስተዋሉም ተመልክቷል፡፡ በጊዜ “Oedipus complex” ሁለት ሰብዕናዎች (Melancholic ego/ Ideal ego እና Mourning/ ego ideal) ይበለፅጋሉ፡፡ እነዚህ እሳቤዎች የፍሬውን ልቡና ለመቅረፅ ያገለገሉ ናቸው፡፡ አስቀድሞ በነበረው እና አዲስ በሚተዋወቀው “ዓለም” ምክንያት የተፈጠረው ቅዡት በሱፐር ኢጎ ልዕልና ተጠናቆ ፍሬው ከ“ዓለሙ” ጋር አዲስ ግንኙነት እንደመሰረተ ተመርምሯል፡፡ አንድም ፍትወታዊ ፍላጎቱን ከእናቱ ማኅበረ-ባህላዊው ሥርዓት ወደ ሚፈቅደው እንዳዞረ፣ አንድም “ፋንታሲውን” ማኅበራዊነት ወዳላቸው ኳስ ጨዋታና ትምህርት እንዳስቀየሰ (Sublimate እንዳደረገ) ተጠኗል፡፡ የእግር ፍሮይዳዊ “ፌቲሻዊነት”ም የተቀመረ ሃሳብ እንደሆነ ተትንትኗል፡፡

በአጠቃላይ አዳም በታላሚ ቴክስቶቹ ሥነ ልቡናዊ ጽንሰ ሃሳቦችን እያለመደ እንደሚፅፍ፣ እነዚህን ጽንሰ ሃሳቦች ለማልመድ ባህላዊና ሚታዊ አስተማስሎዎችን እንደ ኪናዊ “ተውህቦ” ማላቂያ እንደሚጠቀም፣ የሚስላቸው ገፀ-ልጆችም የኢሪክሰንን “ማኅበረ-ልቡናዊ” እና የፍሮይድን “ሳይኮሴክሿል” የዕድገት ደረጃዎች በ“አፍራሽ” ጎኑ የሚያጠናቅቁ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ የዕድገት መታጎልና አሉታዊ መሆን ከአሳዳጊ ማንነት የሚመጣና ሰብዕናቸውም በዚሁ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም፣ ወዲህ ልጆቹ “ማኅበረ-ባህላዊ ፍንገጣ” የሚስተዋልባቸው፣

ለማኅበራዊ ኃላፊነቶች ብቁ ያልሆኑ፣ በራሳቸውም ሆነ በከባቢያቸው የማይተማመኑ እንደሆኑና የቀቢፀ-ተስፋ፣ ብቸኝነትን የመምረጥና የበታችነት ስሜቶች የሚስተዋሉባቸው፣ ወዲህም የጨቅላነት "ፊክሴሽን"አቸውን ወደ ተለያዩ ማኅበራዊ ቅቡልና "ውጉዝ" (ራስ ድሪያ) ወደ ሆኑ ጉዳዮች ያስቀየሱ (Sublimate ያደረጉ) ናቸው።

በምልከታዬ እንዳስተዋልኩት፣ የአዳም ልቦለዶች ገና ለተለያዩ ጥናቶች ክፍት የሆኑ ይመስሉኛል። በቴክስቶቹ ውስጥ ታሪካዊ ክስተቶች፣ እጅግ የገነኑ ማኅበራዊ ጉዳዮችና ስዕል ሰርካዊ ናቸው። ስለሆነም፣ ወዲህ ሥራዎቹን ከ"ባህል ጥናት"፣ ከሥነ ማኅበረሰብ (እና ከ"ታሪክ" አንጻሮችን አልምደው፣ ወዲህ ደግሞ ከሌላኛው ኪን፣ ከስዕል ጋር አዛምደውና የጋራ በሚሏቸው ኪናዊ ላይ መሥርተው ቢያጠኗቸው አዋጭነታቸው ላቅ ያለ ይመስለኛል። እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች የታመቁባቸው ከሆነ ደግሞ ከሁሉም በተሻለ በይነ ዲሲፕሊናዊ ጥናት ይበጃቸዋል።

# ዋቢ ጽሑፎች


ማንያዘዋል እንደሻው፡፡ "የአዳም ልጆች ንፅፅር"፡፡ በ *ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዜና መጽሔት*፡ ቁ.5፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1985፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ፡፡ *የአማርኛ ሥነ ግጥም*፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 1999፡፡

ታደሰ ሺበሺ፡፡ "*ሚቶሎጂያዊ* ጥናት በ*እቴሜቴ ሎሚ ሽታ* እና *ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ*"፡፡ ቴሲስ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2005፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ *በይነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ*፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001፡፡

------------፡፡ "ውስጣዊ ግለወግ÷ እንደወረደ እና ሕልም በትረካ ብልሃትነት፤ በ'ኤልዛቤል'"፡፡ በ *ቋንቋዎች ጥናት ተቋም አስራ ሁለተኛው አመታዊ ጉባኤ* ዩኒቨርሲቲ፣ 1992፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1962፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር፡፡ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993፡፡

አዳም ረታ፡፡ *ማሕሌት*፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1981፡፡

-----------፡፡ *አለንጋና ምስር*፡ አዲስ አበባ፣ ርኆቦት አታሚዎች፣ 2004፡፡

እንዳለጌታ ከበደ፡፡ “አሊጎሪ በአማርኛ ዘመናዊ አጫጭር ልቦለዶች”፡፡ ቴሲስ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2004፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ *መጽሐፈ፡ሰዋስው፡ወግስ፡ወመዝገበ፡ቃላት፡ሐዲስ*፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948፡፡

ገብረሥላሴ ብርሃኑ፡፡ *መዝሙር ዘዳዊት*፡፡ ለ6ኛ ጊዜ የታተመ፡፡ አዲስ አበባ፣ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 2000፡፡

Abrhams, M.H. *A Glossary of Literary Terms.* 7th ed. Heinle & Heinle: Cornell University, 1999.

Aklilu Desalegn. “Exstentialism in the Selected Creative Works of Adam Reta.” MA Thesis, Departmenet of Foreign Language & Lieterature, Addis Ababa University, 2010.

Baldick, Chris. *Oxford Concise Dictionary of Literary Terms*. Oxford: Oxford University Press, 2001.

Barker, Chris. *The SAGE Dictionary of Cultural Studies*. London: SAGE Publications Ltd, 2004.

Bocock, Robert. *Sigmund Freud*. Rev. ed. New York: Routledge, 2002.

Darely, John, et al. *Introduction to Psychology*. New York: Prentice Hall, 1986.

Eagleton, Terry. *Literary Theory: An Introduction.* Ann. (ed). Minnesota: University of Minnesota Press, 2008.

Easthope, Anthony. *The Unconscious*. London and New York: Routledge, 2003.

Edel, Leon. "Literature and Psychology." In *Comparative Literature: Method and Perspective*. Newton P. Stallknecht and Horts Frenz (eds.). Carbondale: southern Illinois University Press, 1961.

Endeshaw Letera. "Stream of Consciousness as Reflected in Adefris and 'ke' Legitwa'". MA Thesis, Departmenet of Foreign Language & Lieterature, Addis Ababa University, 2005.

Erikson, Erik. *Identity and the Life Cycle*. New York: International University Press, Inc, 1959.

------------. *Childhood and Society*. n.p., Norton, 1963.

Ferber, Michael. *A Dictionary of Literary Symbols*. 2nd ed. Cambridge: Cambridge University, 2007.

Fink, Bruce. *The Lacanian Subject: Between Language and Jouissance*. New Jersey: Princeton University Press, 1995.

Freud, Sigmund. *Dream Psychology: Psychoanalysis For Beginners*. Trans. M.D. Eder. New York: The James A. McCann Company, 1920.

---------. *The Interpretation of Dreams*. n.p., 1900.

------------. *Three Essays on The Theory of Sexuality.* Trans. James Strachey. (1905) 1949.

Golan, Ruth. *Loving Psychoanalysis: Looking at Culture with Freud and Lacan*. London and New York: Karnac, 2006.

Grosz, Elizabeth. *Jacques Lacan: a Feminist introduction.* London and NewYork: Routledge, 1998.

Guerin, Wilfred, et al,. *A Hand Book of Critical Approaches to Literature.* 5th ed. NewYork and Oxford: Oxford University Press, 2005.

Habib, Rafey. *A History of Literary Criticism: from Plato to the Present.* Oxford: Blackwell Publishing Ltd, 2005.

Hiwot Wallelign. "Narrative Technique of Adam Reta's *Gracha Qachiloch*: Stream-of-Consciousness in Focus". MA Thesis, Departmenet of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 2012.

Jakobson, Roman and Morris Halle. *Fundamentals of Language.* Mouton: Co. 's-Gravenhage, 1956.

Jenks, Chris. "Constructing Childhood sociologically". In *An Introduction to Childhood Studies*. 2nd ed. Mary Jane Kehily. (ed). Open University: Open University Press, 2009. 93-111.

Jossylen, Irene M. *Psychosocial Development of Children*. 15th ed. New York: Family Association of America, 1964.

Jursied, J. *Child Psychology*. Englewood Cliffs: Prentice Hall, 1954.

Kehily, Mary Jane. "Understanding Childhood: An Introduction to some Key Thems and Issues". In *An Introduction to Childhood studies*. 2nd ed. Mary Jane Kehily. ed. Open University: Open University Press, 2009. 1-16.

Klein, Thompson. *Humanities, Culture, and Interdisciplinarity: the Changing American Academy*. New York: State University of New York Press, 2005.

Krishnaswamy and et'al. *Contemporary Literary Theory: a Student's Companion.* Macmillan: Macmillan India Ltd, 2004.

Loo, Hannah. "Children in Postmodern Literature: A Reconstruction of Childhood". In *HOHONU*. Vol. 10, University of Hawai'I at Hilo, 2012. 59-61.

Lynch, Patrcia A. *African Mythology A to Z*. New York: Facts on File Inc, 2004.

Manser, Martin. *Dictionary of Allusions*. New York: Facts on File, 2009.

Moran, Joe. *Interdisciplinarity*. London and New York: Routledge, 2002.

Parkin-Gounelas, Ruth. *Literature and Psychoanalysis: Intertextual Reading*. New York: Palgrave, 2001.

Rose, H. *A Handbook of Greek Mythology*. London and New York: Routledge, 2005.

Smadja, Claude. "Fixation". In *International dictionary of Psychoanalysis.* Alain Mijolla. (ed.). Trans. Philip Beitchman, et al. Vol. 1. New York: Thomson Gale, 2005.

Sullivan, Shannon. "The Unconscious Life of Race: Freudian Resource for Critical Race Theory." In *Reading Freud: Psychoanalysis through Philolososphy.* Jon Mills. (ed.). New York: State University of New York Press, 2004.195-218.

Tewodros Gebre. "*Mahilet*: A Laboratory of Stylistic Experimentation". In *Reading Contemporary African Literature*: *Critical Perspectives*. Makayiko, R, C. and Makokha. (ed.). New York: Rodopi, 2013. 68-89.

Thom, Martin. "The Unconscious Structured as a Language." In *Jacques Lacan: Critical Evaluations in Cultural Theory.* Slavoj Zizek (ed). Vol. 1: London and NewYork: Routledge, 2003. 33-70.

Tyson, Lois. *Critical Theory Today: a User-Friendly Guide.* 2nd ed. NewYork & London: Routledge, 2006.

Walkerdine, Valerie. “Developmental Psychology and The Study of childhood”. In *An Introduction to Childhood Studies*. 2nd ed. Mary Jane Kehily (ed). Open University: Open University Press, 2009. 112-123.

Wellek, Renne and Austin Warren. *Theory of Literature.* New York: Harcourt, Brace And Company Inc., 1949.

Wolfreys, Julian, et al. *Key Concepts in Literary Theory.* 2nd ed. Edinburgh: Edinburgh University Press Ltd, 2006.

Woodhead, Martin. “Childhood studies: Past, Present and Future”. In *An Introduction to Childhood studies*. 2nd ed. Mary Jane Kehily (ed). Open University: Open University Press, 2009. 17-31.

Zakin, Emly. “The ‘Alchemy of Identification’: Narcism, Melancholia, Feminity.” In *Reading Freud: Psychoanalysis through Philosophy.* Jon Mills (ed). New York: State University of New York Press, 2004. 77-102.